# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWU MOOTIMMA SIDAAMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሲዳማ አፊኒ ጋዜጣ

1kki Diro Kiiro ---
Hawaasa Barra ------2012 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Amaale Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho
በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1ኛ ዓመት ቁጥር…
ሀዋሳ
ቀን………………../፪፻፲፪ ዓ.ም


## Fulo

**Wodho kiiro** **08/2012**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Poolisete Galte Wodho**

## Bitima

**Federaaletenna qoqqowu bayriidi seeri hattono bayriidi seerigarinni fultanno seerrubba ayirrissawotanna ayirrisiissawota woyyitinota poolisete wolqa kalaqate lallawu kiiro 7/2012 garinni qoqqowu poolisete komishiine uurritino**.

Konne lallawa gumulsiisate wodho fushsha hasiisannota ikkite leeltinohura,

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete Komishiine uurrisate lallawi kiiro 7/2012** quwa 31 garinni qoqqowu gashshooti amaale mini tenne wodho fushshino.

ደንብ ቁጥር **08/2012**

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ

**መግቢያ**

የፌደራል እና የክልሉን ሕገ-መንግስት እንዲሁም ሕገ-መንግስቱን መሰረት አድርገው የሚወጡ ሕጎችን የሚያከብርና የሚያስከብር የተሻለ የፖሊስ ኃይል ለመፍጠር አዋጅ ቁጥር ፯/፪፻፲፪መሠረት የክልል ፖሊስ ኮሚሽን ተቋቁሟል፡፡

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፯/፪፻፲፪ አንቀጽ ፴፩መሠረት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

# GAFA MITTO

# XAPHOOMA

## 1. Harancho Borrote Umo

Tini wodho Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete miilla galtete wodho kiiro 08/2012 yine xawisa dandiinanni.

## 2. Tiro

Lallawu kiiro 7/2012 aana uynoonni tiro agarantino gedeenni heedheenna tenne wodho giddo qaalu eo wole tiro uysiissannota ikka hoogguro;

**2.1.Handaaru Sooreessa:** yaa hundasiinni no dayrekterootanna babbaxxitino loosu kifilla massaganno sooreessaati.

**2.2.Dayrekitoreete woy Divizhiine:** yaa aantete garinni Zoonetenna Hawaasi Quchumi Poolisete Biddishshi woy Woradu, Quchumunna Sinu quchumi gashshooti borro mineeti.

**2.3.Sivilete Loosaasincho:** yaa Sivil-serviisete lallawi garinni qaxarame poolisete uurrinshira teese/quwaamete/ loosanno sivilete loosaasinchooti.

**2.4. Gutu Songo:** yaa poolisete uurrinshubba sooreeyye gutu songooti.

**2.5. Yannate Geeshshi Loosaasincho:** yaa uurrinshate giddo teese loosate akati noosikkiha ikke loossa woy huneetta/ikkito/ qarrissuro loosu madawe aana yaannate geeshsha qaxarame loosanno loosaaainchoti.

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭርርዕስ

ይህ ደንብ ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ አባላት መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር -------/፪፻፲፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ፤

በአዋጅ ቁጥር -------/፪፻፲፪ የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፤

2.1. **የዘርፍ ኃላፊ**;- ማለት በሥሩ ዳይሬክቶሬቶችንና የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን የሚመራ ኃላፊ ነው፡፡

2.2. **ዳይሬክቶሬትወይምዲቪዥን**; ማለት እንደቅደም ተከተሉ የዞኖችና የሀዋሳ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ወይም የወረዳ፣ የክፍለ ከተማና የከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጽ/ቤት ነዉ፡፡

2.3. **ሲቪል ሰራተኛ**; ማለት በሲቪል ሰርቪስ አዋጅተቀጥሮ በፖሊስ ተቋማት ዉስጥ በቋሚነት የሚሰራ ሲቪል ሰራተኛ ነዉ፡፡

2.4. **የጋራ ጉባኤ**; ማለት የፖሊስ ተቋማት ኃላፊዎች የጋራ ጉባኤ ነዉ፡፡

2.5. **ጊዜያዊ ሰራተኛ**; ማለት በተቋሙ ዉስጥ የዘላቂነት ባህሪይ በሌለዉ ስራዎች ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የስራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ ነዉ፡፡

2.6. **Dayroktereete:**yaa poolisete uurrinshubba giddo bande uynoonni looso loossanno loosu kifileeti.

2.7. **Xaginnatu Uurrinsha:** yaa Federaalete Poolisete Komishiine Riferaalete Hospitaale woy Poolisete uurrinshi fayyimmate mereershi/xaawi/ woy woloota poolisete xaginate uynanniwaati.

2.8. **Looosu Aana Iillitanno Gawajjo:** yaa loosu aana iillitanno dano woy loosu korkaatinni daanno dhibbaati.

2.9. **Poolisete Suusa:** yaa Konistaabiletenni kayse Komishiineerete geeshsha no biillonyu qeechaatinna su'maati.

2.10. **Suusu Lopho:** yaa mittu poolisete miili amadino suusinni aananno suusu dirima lossate uyinanni poolisimmate biillonyeetinna sooreessimmaati.

2.11. **Sooreessimmate Lopho:** yaa mitte loosu kifile massagate, gashshatenna qorqorate uynanni poolisete massagoshshu biillonyeetinna sooreessimmaati.

2.12. **Koffeenya macciishshate Komite:** yaa miillatenni shiqanno koffeenya buuxxe gumulo uytanno komiteeti.

2.13. **Uurrinshate Aliidi Sooreessa:** yaa poolisete uurrinsha sooreessati.

2.14. **Kaimu Poolisete Qajeelsha:** yaa kaimu suusu diriminni umi suusa aate poolisete kolleejera uynanni qajeelshati.

2.15. **Poolisete Sayinse Qajeelsha:** yaa mereerimu suusi woy jawiidi suusi diriminni kaimu suusa aate poolisete kolleejjenni poolisete masssaganchimma aana uynanni qajeelshaati.

2.6. **ዳይሬክቶሬት**; ማለት በፖሊስ ተቋማት ዉስጥ ተለይቶ የተሰጠን ስራ የሚከናወንበት የስራ ክፍል ነዉ፡፡

2.7. **የህክምና ተቋም**;ማለት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ሪፈራል ሆስፒታል ወይም የፖሊስ ተቋማቱ ጤና ጣቢያ ወይም ሌሎች የፖሊስ ህክምና መስጫ ነው፡፡

2.8. **በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት**; ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነዉ፡፡

2.9. **የፖሊስ ማዕረግ**; ማለት ከኮንስታብል እስከ ኮሚሽነር ድረስ ያለ የማዕረግ ተዋረድና ስያሜ ነው፡፡

2.10. **የማዕረግ ዕድገት**; ማለት አንድ የፖሊስ አባል ከያዘው ማዕረግ ወደ ቀጣዩ የማዕረግ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚሰጥ የፖሊስነት ሥልጣንና ኃላፊነት ነው፡፡

2.11. **የኃላፊነት ዕድገት**;ማለት አንድን የሥራ ክፍል ለመምራት፣ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚሰጥ የፖሊስ አመራርነት ስልጣንና ኃላፊነት ነው፡፡

2.12. **ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ**; ማለት በአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ዉሳኔ የሚሰጥ ኮሚቴ ነዉ፡፡

2.13. **የተቋሙ የበላይ ኃላፊ**; ማለት የፖሊስ ተቋም ኃላፊ ነው፡፡

2.14. **መሰረታዊ የፖሊስ ስልጠና**; ማለት የጀማሪ ማዕረግ ዕርከን መነሻ ማዕረግ ለመስጠት በፖሊስ ኮሌጅ የሚሰጥ ስልጠና ነዉ፡፡

2.15. **የፖሊስ ሳይንስ ስልጠና**; ማለት የመካከለኛ ማዕረግ ወይም የከፍተኛ ማዕረግ ዕርከን መነሻ ማዕረግ ለመስጠት በፖሊስ ኮሌጅ ለፖሊስ አመራርነት የሚሰጥ ስልጠና ነዉ፡፡

2.16. **Istiraateejike Suusu Dirima:** yaa Komishiineretenni kayse Komishiinerete Jeneraale geeshsha no suusu dirimaati.

2.17. **Jawa suusu Dirima:** yaa qara Inispekterenni kayse 2[nki]Komishiinere geeshsha no suusu dirimaati.

2.18. **Mereerima Suusu Dirima:** yaa Kaa'laanchu inispekterenni kayse Insipekterete geeshsha no suusu dirimaati.

2.19. **Kaimu Suusu dirima:** yaa Konistaabiletenni kayse qara saajine geeshsha nosuusu dirimaati.

2.20. **Kaampe:** yaa Komishiinete afanshi nooha ikke poolisete soqqansho wonshate Birgeedetenni woy Shaalaqunni woy Shaambelletenni woy Gaantunni woy Tiimetenni tantanamantino poolisete miilla heedhanno kaampeeti.

2.21. **Giddeetu Baycho:** yaa ga'labbote qarri woy kalaqamu dano kalaqamate korkaatinni qarra qorqortawo gede poolisete miilla gaamantanno dargaati.

2.22. **Keeshshate Yanna:** yaa mittu poolisete miili aane no suusu deerrira sa''ara albaanni amade no suusu deerrinni xawunni afaminoha duushshanno guma abbisiisanni keeshshanno yannate seendilleeti.

### 3. Gumulamate Danna

Tini woddho Konistaabiletenni kayseKomishiinerete suusi noonsari Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete miilla aana gumulamannoha ikkanno.

## 4. Koo-tee Xawishsha

Kuni lallawi "Koo" akatinni xawinsoonnihu"Tee" akatano hanqafanno.

2.16. **ስትራቴጂክ የማዕረግ ዕርከን**; ማለት ከኮሚሽነር እስከ ኮሚሽነር ጄነራል ያለው የማዕረግ ዕርከን ነዉ፡፡

2.17. **ከፍተኛ የማዕረግ ዕርከን**; ማለት ከዋና ኢንስፔክተር እስከ ምክትል ኮሚሽነር ያለዉ የማዕረግ ዕርከን ነዉ፡፡

2.18. **መካከለኛ የማዕረግ ዕርከን**; ማለት ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር ያለዉ የማዕረግ ዕርከን ነዉ፡፡

2.19. **ጀማሪ የማዕረግ ዕርከን**; ማለት ከኮንስታብል እስከ ዋና ሳጂን ያለዉ የማዕረግ ዕርከን ነዉ፡፡

2.20. **ካምፕ**; ማለት የኮሚሽኑ እዉቅና ያለዉ ሆኖ የፖሊስን ተልዕኮ ለማሳካት በብርጌድ ወይም በሻለቃ ወይም በሻምበል ወይም በጋንታ እና በቲም ተደራጅቶ የሚገኙ የፖሊስ አባላት የሚኖሩበት ካምፕ ነዉ፡፡

2.21. **ግዳጅ ቦታ**; ማለት የፀጥታ ችግር ወይም የተፈጥሮ አደጋ በመከሰቱ ምክንያት ችግሩን እንዲቆጣጠሩ የፖሊስ አባላት የሚሰማሩበት ስፍራ ነዉ፡፡

2.22. **የመቆያ ጊዜ**; ማለት አንድ የፖሊስ አባል ወደ ቀጣዩ የማዕረግ ደረጃ ከመሸጋገሩ በፊት በያዘው የማዕረግ ደረጃ በግልጽ የሚታወቅ አጥጋቢ ውጤት እያስመዘገበ የሚቆይበት የጊዜ ርዝማኔ ነው፡፡

### ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ከኮንስታብል እስከ ኮሚሽነር ማዕረግ ባላቸዉ ሲዳማ ክልል መንግስት ፖሊስ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

### ፬.የፆታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ይመለከታል፡፡

## GAFA LAME

## Poolise Fila, Qajeelshanna Gaama Lainohunni

### 5. Fila

1. Poolise ikkate hasatto noohu aye manchino:
   a) Qansiichimma Itiyophiyaawicha ikkinoha
   b) Federaaletenna Qoqqowu Aliidi Seerira ammanamaanchonna hajajamaancho
   c) Daga, Dagoomunna Mannu taalleenyinni ammannoha
   d) Ammanote taalleenyinni ammanannoha
   e) Danchu amanyooti nooha
   f) Adhinokkihanna ooso ilinokkiha
   g) Diro 18 ajinokkihanna 25 sainokkiha
   h) Aye politiku uurrinshi miila ikkinokkiha,
   i) Ajaa ajeenna 10 kifile roso gudinoha,
   j) Poolisimmate ikkitannoti mannimmate guuntenna wo'ma keeraanchimma nooha,
   k) Jaddote qorichinni borreessine maareekkinoonnikkiha
   l) Uynanniha eote fonqolo sainoha ikka noosi,
   m) Konni albaanni gargarooshshunna poolisete miila ikkinokkiha,
2. Konni quwira gufo(1) aana worroonnihu noogede hee'reennanni komishiine babbaxxitino poolisete ogimma qajeelshubbarafilate heewisiishshubixxillootira tittirshu wodhofushsha dandiitanno.
3. Konniquwira gufo (1) nna (2) aana worroonnihu noogede hee'reennanni komishiine hasiisanno garinni baxxitino sokka loosu aana hosiisaate baxxino garinni rosu dirima woyyeessa dandaanno.

## ክፍል ሁለት

## ስለፖሊስ ምልመላ፣ሥልጠናና ምደባ

### ፭. ምልመላ

፩. ፖሊስ ለመሆን ፍላጎት ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ፡-

ሀ. ዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ. ለፌዴራልና ለክልሉ ሕገ-መንግስት ታማኝና ተገዥ፣

ሐ. በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት የሚያምን፣

መ. በሐይማኖቶች እኩልነት የሚያምን፣

ሠ. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣

ረ. ያላገባና ልጅ ያልወለደ፣

ሰ. ዕድሜዉ ከ18 ዓመት ያላነሰ እና ከ25 ዓመት ያልበለጠ፣

ሸ. የማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፣

ቀ. ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀ፣

በ. ለፖሊስነት የሚያበቃ አካላዊ ብቃትና የተሟላ ጤንነት ያለው፣

ተ. የወንጀል ቅጣት ሪከርድ የሌለበት፣

ቸ. የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተናዎች ያለፈ መሆን አለበት፡፡

ነ. ቀደም ሲል የመከላከያና የፖሊስ አባል ያልነበረ፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለተለያዩ የፖሊስ ሙያ ስልጠናዎች የመመልመያ መስፈርቶችን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ እንዳስፈላጊነቱ የተለየ ተልዕኮ ለማስፈፀም ሲል በልዩ ሁኔታ የትምህርት ደረጃውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

4. Poolise filate egenshiishshinna gumulshi Sidaamu Poolisete kolleejenniqixxawanno gumulshi garinni loosu aana hosanno.
5. Konni quwira gufo(1) aana worroonnihu agaramino gede hee’reennanni poolisimmate assinanni fila meentoho addi irko uytanno.

## 6. Rosonna Qajeelsha

1) Mokkonninimmate suusira filamannohu aye manchino woy poolisete miili poolisete kolleeje fushshitanno heewisiishshu bixxille garinni heewisamanno gede assinanni.
2) Ayno poolisete miili loosu aana woy loosu gobbaa here komishiine injeessitannote rosu kaayonni heewisame sairo ho’rammeessa ikkanno.
3) Konni quwira gufo (2) aana ofoshshiinshoonnihu agaramino gedeenni heereennamittu qajeelaanchi qajeelsha gudanni heere loosisi aana heere ha’runsino roso qajeelsha adhino yanna geeshsha woy erote owaante aate gaddado noosi.
4) Aye pooliseno komishiinete mixo garinni rosu kaayyo gobbate giddo woy gobbaanni (baara wido) rosanno gede gumultasira dandiitanno Rosu aana hee’reenna damoozu baatooshshi tittirshu jirtetenni /mammarunni/ gumulamanno.

፬. □□ሊስ ምልመላ ማስታወቂያና አፈፃፀም በሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅ በሚዘጋጀዉ የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፖሊስነት የሚደረገው ምልመላ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## ፮. ትምህርትና ሥልጠና

፩. ለዕጩ መኮንንነት የሚመለመል ማንኛ□ ም ሰ□ ወይም የፖሊስ አባል ፖሊስ ኮሌጅ በሚያወጣዉ መስፈርት መሰረት እንዲወዳደር ጁ□ረ□ል፡፡

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል በሥራ ላይ ወይም ውጭ ሆኖ በኮሚሽኑ በሚመቻች የትምህርት ዕድል ተወዳድሮ ካለፈ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሠልጣኝ ስልጠናዉን እንዳጠናቀቀ በመደበኛ ስራ ላይ ሆኖ የተከታተለዉ ትምህርት ወይም ስልጠና የወሰደዉን ጊዜ ያህል ወይም ከመደበኛ ስራ ውጭ ሆኖ የተከታተለዉ ትምህርት ወይም ስልጠና የወሰደዉን ጊዜ እጥፍ የማገልገል ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛዉም ፖሊስ በኮሚሽኑ ዕቅድ የትምህርት ክትል በሀቹር ውስ□ ወጁም በው፡□ ሀቹር እንዲማር ሊወሰንለት ይችላል፤ በትምህርት ላይ እያለ የደመወዝ አከፋፈለል በመመሪያ ይወሰናል፡፡

5) Aye poolisete miilirano gaamamino loosi aana guuta assannoha loosu aani qajeelsha uynannisi.

6) Ayno Sidaamu Poolisete Kolleeje qajelaanchi qajeelshu yannara:

   a) Gaammannisi qajeelshu pirogiraame garinni beeqqate gadacho noosi

   b) Gallannita kolleejete jirte ayirrisa noosi

   c) Qajeelsha ei barrinni hanafe qajeelsha gude fula geeshsha poolisete kolleeje jirtenni galanno; qoosssosino hatte jirte garinni agarantannosi.

7) Sidaamu Polisete Kolleeje gobbaanni wolootu aye Kolleejotinna Yuniverisitootira Komishiine sokke rosiissannohu poolisete miili gaamaminoha qajeelshu roso uurrisate, soo'rirate woy seedisate hasiriro komishiinete fajjo afira noosi.

8) Qajeelshu aana noohu aye filamino poolisichi woy poolisimmate dooramino mokkonninichi poolisete miilimmara qaxaramasira albaanni kaima woy poolisete sayinse rosonna qajeelsha adhanna uyinoonni fonqolo sa''a noosi.

9) Qajeelshu aana heerannohu aye poolisete miilino woy poolisimmate dooramino mokkonninichi:

   a) Sagale, gonxanniwa, qajeelshu uddanna, borrote uduunnichonna kiisete woxe uynannisi.

   b) Iillitannosi xissora woy danora hasiissannoha xaginatu owaante afiranno.

   c) Qajeelshu yannara loosu rosiishshi aana iillitannosi jaddote xama'mooshshira umisiha higgete ogeessa gaa'matenni woy xawaqaqaxadhatenni mulla xawaqu owaante afiranno.

፭. ማንኛውም የፖሊስ አባል በተመደበበት ሥራ ላይ ብቁ የሚያደርገው የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጠዋል፡፡

፮. ማንኛውም ሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅ ሰልጣኝ በስልጠና ወቅት፡-

   ሀ. በሚመደብለት የስልጠና ፕሮግራም የመሳተፍ ግዴታ አለበት፡፡

   ለ. የሚተ□□ርበትን የኮሌጁን መመሪያ ማክበር አለበት፡፡

   ሐ. ወደ ማሰል□ኛ ከገባበት ቀን ጀምሮ ስልጠናዉን ጨርሶ እስኪወጣ ድረስ በ□ሊስ በኮሌፃ መመሪ□ ጁተ□□ራል፤ መብቶቹም በዚሁ መመሪያ ይከበሩለታል፡፡

፯. ከሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅ ዉጪ በሌሎች ማንኛዉም ኮሌጆችና ዩንቨርሲቲዎች ኮሚሽኑ የሚያስተምረዉ የፖሊስ አባል የተመደበበትን የስልጠና መስክ ለማቋረጥ፣ ለመቀየር ወይም ለማራዘም ሲፈልግ የኮሚሽኑን ፍቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፰. በስልጠና ላይ የሚገኝ ማንኛዉም ምልምል ፖሊስ ወይም ለፖሊስነት የታጨ ዕጩ መኮንን በፖሊስ አባልነት ከመቀጠሩ በፊት መሰረታዊ ወይም የፖሊስ ሳይንስ ትምህርትና ስልጠና መዉሰድና የሚሰጠዉን ፈተና ማለፍ አለበት፡፡

፱. በስልጠና ላይ የሚገኝ ማንኛዉም ምልምል ፖሊስ ወይም ለፖሊስነት የታጨ ዕጩ መኮንን፡-

   ሀ) ምግብ፣ መኝታ፣ የስልጠና አልባሳት፣ የጽህፈት መሳሪያና የኪስ ገንዘብ ይሰጠዋል፣

   ለ) ለሚደርስበት ህመም ወይም አደጋ አስፈላጊዉን የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፣

   ሐ) በስልጠና ወቅት የተግባር ልምምድ ላይ ለሚደርስበት የወንጀል ተጠያቂነት የራሱን የህግ ባለሙያ በመመደብ ወይም ጠበቃ በመቅጠር ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፡፡

10) Ayno mokkonninimmate dooraminohu woy harancho yanna qajeelshira Sidaamu poolisete kolleeje einohu poolisete miili:

a) Sagale, goxannowa, borrote uduunnicho, damooza, hasiisi garinni qajeelshu uduunne uynannisi.

b) Hasi'nannisiha womaashshu fulora gutame baatooshshe guutisanno.

c) Tenne wodhonni aye poolisete miilirano xaginatu woy higgete/seeru/ owaante aate worroonni garinni owaante afiranno gede assinanni.

11) Ayno filanchu poolisichi woy poolisimmate dooramino mokkonninichi qajeelsha gude maasamihu gedensaanni owaantete gaddado yanna gooffara albaanni agurannoha ikkiro konni quwira gufo (8) nna (9) worroonni garinni qajeelshu yannara kolleeje fushshitinoha qajeelshaho fulino woxe baatanno gede assinanni.

## 7. Qaalu-Xaaro

1. Ayno poolisete miili kaima woy poolisete sayinse qajeelsha gudaa heerenni looso hanafara albaanni konninni aante noota qaalu xaaro wonshanno:

"Ani………………..Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete miilimma'yanni Federaaletenna Qoqqowu bayriidi seera, woloota seerubbanna mootimmate/mengistete/ polise ayirrise ayirrisiisate, higgetenni/seerunni/ woy loosunni fojo dinbe amandanni gede gumullonni hajubba la'annonsakki bissira fushsheemmokki gede, jaddo mudhe gargaratenna dagate mallande nookkiha halaalunni, ammanamooshshunninna sumbetenni owaatate qaale e''eemmo."

2. Qaalu-xaaro miilunni malaatisante umisi fayle (mahider) giddo ofoltanno.

፲. ማንኛዉም ለዕጩ መኮንንነት ወይም ለአጭር ጊዜ ስልጠና ሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅ የሚገባ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) ምግብ፣ መኝታ፣ የጽህፈት መሳሪያ፣ ደመወዝ፣ እንዳስፈላጊነቱ የስልጠና አልባሳት ይሰጠዋል፣

ለ) የሚፈለግበትን የወጪ መጋራት ክፍያ ይፈጽማል፣

ሐ) በዚህ ደንብ ለማንኛዉም የፖሊስ አባል የህክምና ወይም የህግ አገልግሎት ለመስጠት በተደነገገዉ መሰረት አገልግሎቱን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

፲፩.ማንኛዉም ምልምል ፖሊስ ወይም ለፖሊስነት የታጨ ዕጩ መኮንን ስልጠናዉን አጠናቆ ከተመረቀ በኋላ የግዴታ አገልግሎት ጊዜዉ ከማለቁ በፊት የሚለቅ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ፰ እና፱ በተደነገገው መሠረት በስልጠና ወቅት ኮሌጁ ያወጣው የስልጠና ወጪ እንዲከፍል ይደረጋል፣

## ፯.ቃለ-መሐላ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል መሠረታዊ ወይም የፖሊስ ሳይንስ ስልጠና እንዳጠናቀቀ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሚከተለውን ቃለ መሀላ ይፈጽማል፡፡

‹‹እኔ ------------------------- በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ አባልነቴ የፌዴራልና የክልሉን ሕገ-መንግስት፣ ሌሎች ሕጐችንና የመንግስት ፖሊሲዎችን አክብሬ ለማስከበር፣ በህግ ወይም በአሠራር በሚስጢርነት እንዲያዙ የተወሰኑ ጉዳዮችን ለማይመለከተው ወገን ላለመግለጽ፣ ወንጀልን በቁርጠኝነት ለመከላከልና ሕዝቡን ያለአድልዎ በእውነት፣ በታማኝነትና በቅንነት ለማገልገል ቃል እገባለሁ››፡፡

፪. ቃለ መሐላው በአባሉ ተፈርሞ በግል ማህደሩ ውስጥ ይቀመጣል፡፡

## 8. Qaxara

1. Haaru qaxaraminohu poolisete miili miilimate borreessamannohu woy owaantesi kiirama hanaffannohu kaimu woy poolisete sayinse qajeelsha gude qaalu-xaaro wonshe qaxaramate sheemaate malaatisi barrinni hanafe ikkanno.
2. Poolisete miila ikke qaxaramanno manchi lamala diro owaante aani keeshshate gaddado (giddeetu) noosi.
3. Lamala diro owaante aate gaddadosi gudikkinni looso aguranno miili qajeelshu yannara fulino woxe owaante uynokki yanna shallangeenna baata noosi.

## 9. Gaama

1. Aye poolisete miilano loosoho gaammannihu:
   a) Mannu wolqa mixo;
   b) Loosu xa'mannoha rosu deera, egennonna dandoo;
   c) Loosu gumulshi guma,
   d) Owaantete diro/yanna,
   e) Amadino suusanna
   f) Amanyoote kaima assatenni ikkanno.
2. Ayno poolisete miili hasiisiha ikkiro qoqqowu giddo heedhanno poolisete uurrinshuwara loosu gaamooshshe uynisiro loosate gaddado(giddeetu) noosi.
3. Konni quwira gufo (2) kaiminni ayno poolisete miili gaamooshshu woy soorrote korkaatinni baychunni baycho haranno woyte miilu maatesinna uduunnesi hogophannohanna hodhishshunniha wo'ma woxu fulo adhannosi uurrinshi dandaanno.
4. Miilu xa'monni assinanni soorrora harannoha wo'ma womaashshu fulo miilu umisi dandaanno.

## ፰.ቅጥር

፩. አዲስ ተቀጣሪ የፖሊስ አባል በአባልነት የሚመዘገበዉ ወይም አገልግሎቱ መቆጠር የሚጀምረው መሠረታዊ ወይም የፖሊስ ሳይንስ ሥልጠና ጨርሶ ቃለ መሐላ በመፈጸም የቅጥር ዉል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

፪. በፖሊስ አባልነት የሚቀጠር ሰው ሰባት ዓመት የማገልገል ግዴታ አለበት፤

፫. የሰባት ዓመት የአገልግሎት ግዴታውን ሳያጠናቅቅ ሥራ የሚለቅ አባል በስልጠናው ወቅት የወጣውን ወጪ አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## ፱.ምደባ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ምደባ የሚፈፀመው፡-

ሀ) የሰው ሀይል ዕቅድን፣

ለ) ሥራው የሚጠይቀውን የትምህርት ደረጃ ዕውቀትና ክህሎት፣

ሐ) የሥራ አፈጻጸም ውጤት፣

መ) የአገልግሎት ዘመን፣

ሠ) የያዘው ማዕረግ እና

ረ) ሥነ-ምግባሩን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል እንደአስፈላጊነቱ በክልል ባሉ የፖሊስ ተቋማት የስራ ምደባ ሲሰጠዉ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ማንኛዉም የፖሊስ አባል በምደባ ወይም ዝዉዉር ምክንያት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲጓጓዝ የአባሉ፣ የቤተሰቡና የጓዝ ማጓሻ እና የትራንስፖርት ሙሉ ወጪ በተቀባዩ ተቋም ይሸፈናል፡፡

፬. በአባል ጥያቄ የሚደረግ ዝዉዉር የመጓጓዣ ሙሉ ወጪ በአባሉ በራሱ ይሸፈናል፡፡

## 10. Qaxara, Gaamooshshenna Soorro

1. Ayno poolisete miili qaxarama qoqqowu poolisete komishiinenni gumulantannno.
2. Jawu suusi noosi poolisichi mitte loosu kifilenni wole loosu kifilera qole gaamate woy soorrate dandaannohu komishiinere jeneraaleetinna Kolleejete dayrekitereeti.
3. Federaaletenninna wolootu qoqqowubbanni qoqqowinkera woy qoqqowinkenni hakka woloota qoqqowubba qolle assinanniti poolisete soorro uytannorinna adhitanno bissa sumuu yaatenni (simiimmenni) Federaalete poolisete komishiine widoonni gumulamantanno.
4. Jawatennikayse kaimu suusi geeshsha noosihu poolisete miili qoqqowu giddo heedhanno uurrinshubba mereero assinanni soorro uytannonna adhitanno kifilla simiimmenni gumulamanno.
5. Konni quwira gufo (4) aana xawinsoonnihu heerirono loosoho hasiisannota ammanniro Komishiinete jeneraalichi woy layinki komishiinere jeneraalichi gumulonni riqiwonookkiha soorro assa dandiinanni.
6. Mereerimunni kayse hanafote suusi dirimi geeshsha qoqqowoho no uurrinshubbara assinanni soorrote loosira loosu gaamooshshe woy soorro Komishiinete, Zoonetenna Hawaasi katami gashshooti poolisete Mannu Jiro Gashshooti Dayroktoreetenna Divizhiinete widoonni gumulamantanno.
7. Konni quwira gufo (2) aana xawinsoonnihu guutisamihu gedensaanni uynanni gaamooshshe agurranna ayno konni quwira gufo 6$^{te}$ garinni uynoonni gaamooshshe woy soorro gaantino kifile afukkinni kaysa woy soorra didandiinanni.

## ፲.ቅጥር፣ ምደባና ዝውውር

፩. የማንኛውም ፖሊስ አባል ቅጥር በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ይፈፀማል።

፪. ከፍተኛ ማዕረግ ያለው ፖሊስ ከአንድ የስራ ክፍል ወደ ሌላ የስራ ክፍል ለመመደብ ወይም ለማዛወር የሚቻለው በኮሚሽነር ጄነራል፤ በኮሌጅ ዳይሬክተር ይፈፀማል።

፫. ከፌዴራልና ከሌሎች ክልል ወደ ክልላችን ወይም ከክልላችን ወደ ፌዴራል ወይም ወደ ሌሎች ክልሎች የሚደረግ የፖሊስ ዝዉዉር በሰጪና በተቀባይ ክፍሎች ስምምነት በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በኩል ይፈፀማል።

፬. ከከፍተኛ እስከ ጀማሪ ማዕረግ ያለው የፖሊስ አባል በክልሉ ባሉ ተቋማት መካከል የሚደረግ ዝዉዉር በሰጪና በተቀባይ ክፍሎች ስምምነት ይፈፀማል።

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ የተጠቀሰዉ ቢኖርም በስራዉ አስፈላጊነት ከታመነ በኮሚሽነር ጄነራል ወይም በምክትል ኮሚሽነር ጄነራል ውሳኔ ያለምትክ ዝውውር ሊፈፀም ይችላል።

፮. ከመካከለኛ እስከ ጀማሪ ማዕረግተኛ እርከን ድረስ በክልሉ ባሉ ተቋማት የሚደረግ የዉስጥ የስራ ምደባ ወይም ዝዉዉር በኮሚሽን፣ በዞንና በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ የሰዉ ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬትና ዲቪዥን ይፈፀማል።

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀዉ ከተፈፀመ በኋላ የሚሰጥ ምደባ ካልሆነ በስተቀር ማንኛዉም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሰረት የተሰጠ ምደባ ወይም ዝውውር የመዳቢው አካል እውቅና ሳይኖር ማንሳት ወይም ማዛወር አይቻልም።

8. Ayno poolisete miili mittu baychinni hakka wole qarqara soorramate gaamamino baycho aja ajeenna mittu diri loosu guutishsha keennanni yanna geeshsha loosate gaddado(giddeetu) noosi
9. Konni quwira gufo (8) aana xawinsoonnihu heerirono konni quwi garinni deerru deerrunni soorro assate roorrimma uynoonninsa bissanni hasiisannoha ikkasi ammanamiha ikkiro lewu aganita loosu gumulshita keenote yanna haransa dandiinanni.

**11. SoorrotenniWoyAgadhaanchimmatenni Gaama**

1. Ayno poolisete miili qoqqowu giddo baychunni baycho soorrame loosa dandaanno.
2. Poolisete uurrinshubbara loosoho hasiisannoha ikkiro poolisete miila uurrinshu giddo taalo loosu deerrinna damoozira mitte loosu madawera taalo dirimi noowa wole taalo madawe woy mittu loosu baychinni hakka wole loosu baychira soorratenni loosiisa dandiinanni.
3. Konni quwira gufo 2 garinni giddoodi soorro wonsha dandiinannihu fanu loosu baychira loosa hasidhanno miilla heedhuro soorro heewotenni assinanni.
4. Konni quwira gufo 3 worroonnihu heerirono ollaa agurranna woolotu poolisete uurrinshubba gadachannorichi heeriro loosu ba’’annokki gede mittu poolisete miili damooza lendikkinninna xeinsikkinni taalanno deerriranna sooreessimmara lee agana roorinokki yannara adadhaanchimmatenni loosisa dandiinanni.
5. Ayno poolisete miili xissote/gogu gajaajjo/ korkaatinni amadino loosu baycho loosara dandaa hoogasi fayyimmate tajenni buunxiro:

፰. ማንኛውም የፖሊስ አባል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ አካባቢ ለመዛወር በተመደበበት ቦታ ቢያንስ የአንድ ዓመት የስራ አፈፃፀም የሚመዘንበት ጊዜን ያህል የመስራት ግዴታ አለበት።

፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) ላይ የተጠቀሰዉ ቢኖርም በዚህ አንቀጽ በየደረጃዉ ዝዉዉር ለመፈፀም ኃላፊነት በተሰጣቸዉ አካላት አስፈላጊነቱ ሲታመንበት በስድስት ወር የስራ አፈፃፀም የምዘና ጊዜን ማሳጠር ይቻላል፡፡

## ፲፩. በዝውውር ወይም በተጠባባቂነት ስለመመደብ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል በክልሉ ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውሮ ሊሰራ ይችላል፡፡

፪. በፖሊስ ተቋማት ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፖሊስ አባሉን በተቋሙ ውስጥ በተመሳሳይ የስራ ደረጃ እና ደመወዝ በአንድ የሥራ መደብ እኩል ደረጃ ወዳለው ሌላ ተመሳሳይ የስራ መደብ ወይም ከአንድ የስራ ቦታ ወደ ሌላ የስራ ቦታ በማዛወር ሊያሰራ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በውስጥ ዝውውር ሊሟላ በሚችል ክፍት የሥራ ቦታ ላይ መስራት የሚፈልጉ አባሎች ሲኖሩ ዝውውሩ በውድድር ይፈፀማል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ከቀበሌ በስተቀር ሌሎች የፖሊስ ተቋማት ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ሥራው እንዳይበደል የአንድ ፖሊስ አባል ደመወዝ ሳይጨመርና ሳይቀነስ በሚመጥነው ደረጃና ኃላፊነት ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ በተጠባባቂነት ማሠራት ይቻላል፡፡

፭. ማንኛውም የፖሊስ አባል በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የስራ ቦታ ሊሠራ አለመቻሉ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፡-

a) Taalu deerrira gaamama dandaannowa fanu loosu baychi heeriro gaamame loosanno;
b) Taalu dirimira gaamama dandaannotera fanu loosu baychi hoogiro miilu injaannosi loosu baycho gaamame loosanno; loosate sumuu yaa hoogiha ikkiro owaantesi uurritanno.

6. Aye sooreessino babbaxxino korkaatinni loosisi baycho heerannokkiha ikkiro sase agana roortinokki yannara biilloonyu riqiwo aa dandaanno; riqiwo aannohuno worosiinni issinni aane balaxeno sooreessira ikkanno.
7. Konni quwira gufo 6 garinni biilloonyu riqiwo uyno sooreessi loosoho higikkinni sasu agani aleenni keeshshiha ikkiro uynoonnisi riqiwo seedinse sooreessimmate baychira baatisiisa dandaanno baatooshshe riqiwamaanchu afiranno gede assinanni.
8. Mittu poolisete miili loosu dargi gatiha ikkiro uurrinshate giddo taalo deerra afi'rino loosu dargira soorrame loosanno; iikeennano taalu baychi hee'rannokkiha ikkiro damoozisi noowinni xeikkinni wole fano ikkitino loosu basera gaammanni; sumuu yaannokkiha ikkiro, tenne wodho garinni afi'ra hasiissannosi ho'ro agaranteennasi geegiissamanno.
9. Mitto poolise lewu aganni aleenni riqiwotenni woy agadhaanchimmatenni loosiisa didandiinanni.
10. Mittu poolisete miili xurataho lamu dirinna hakkuy wori gatannosi woyte hasirino qarqara soorrama dandaanno.

ሀ. በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የስራ ቦታ ካለ ተመድቦ ይሰራል፣

ለ. በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የስራ ቦታ ከሌለ አባሉ በሚስማማዉ የሥራ ቦታ ተመድቦ ይሰራል፣ለመስራት ፍቃደኛ ካልሆነም አገልግሎቱ ይቋረጣል፣

፮. ማንኛውም ኃላፊ በተለያየ ምክንያት በስራ ገበታው ላይ የማይኖር ከሆነ ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የሥልጣን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣ውክልና የሚሰጠውም ከወካዩ ቀጥሎ ወደታች በኃላፊነት ቀደምትነት ላለው ኃላፊ ይሆናል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሰረት የስልጣን ዉክልና የሰጠዉ ኃላፊ ወደ ስራዉ ሳይመለስ ከሦስት ወር በላይ የቆዪ ከሆነ የተሰጠዉን ዉክልና በማራዘም የኃላፊነት ቦታዉ ሊያስገኝ የሚችለዉን ክፍያ ተወካዩ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

፰. የአንድ ፖሊስ አባል የሥራ ቦታ የታጠፈ እንደሆነ በተቋሙ ውስጥ ተመሳሳይ ደረጃ ወደ አለው የሥራ ቦታ ተዛውሮ ይሠራል፣ሆኖም ተመሳሳይ ቦታ የማይገኝ ከሆነ ደመወዙ ሳይቀነስ ክፍት በሆነ የሥራ ቦታ ይመደባል፣ፈቃደኛ ካልሆነ በዚህ ደንብ መሠረት ሊያገኝ የሚችለው ጥቅም ተከብሮለት ይሰናበታል፡፡

፱. አንድን ፖሊስ ከስድስት ወር በላይ በውክልና ወይም በተጠባባቂነት ማሰራት አይቻልም፡፡

፲. አንድ የፖሊስ አባል ለጡረታ ሁለት ዓመት እና ከዝያ በታች ስቀረው ወደሚፈልግበት አከባቢ መዛወር ይችላል፡፡

## GAFA SASE

## Siivil-Serviisete Loosaasine Gashshooti Daafira

### 12. Siivil-Serviisete Loosaasine Lainohunni

1. Uurrinshu siivilete loosaasinenni loosantanno loossa badatenni siivilete loosaasine siivil-serviisete lallawi, wodhonna jirte garinni qaxaranno, gashshannono.
2. Qowaaminatu woy yannate geeshshi qaxara qoqqowoho no uurrinshubbara mannu jiro gashshooti sooreessinni gumulamantanno.
3. Siivilete loosaasincho ikki baali uurrinshate progiraamma, loossanna jirtubba ayirrisate gadde noosi.

### 13. Yannate Geeshshira Qaxarranni Loosaasinchire Lainohunni

Uurrinsha fano ikkitino loosu madabbara deerru lophonni, soorrotenni woy quwaametey qaxarate poolisete ogeessa woy siviilete loosaasincho afi'rate dandiitinokkita buuxxuro yannate geeshshira qaxara dandiitanno.

## GAFA SHOOLE

## Suusu Lophonna Sooreessimmate Dargi Gaamooshshe

### 14. Alaama

Suusu lopho woy sooreessimmate dargi gaamooshshi alaama:

1. Komishiine suusunna sooreessimmate dirimi deerrinni hasiissannota mannu wolqa hasatto wonshate woy
2. Poolisete miilla jawaachishatenni komishiinete loosu gumulsha woyyeessate ikkanno.

## ክፍል ሦስት

## ስለ ሲቪል ሠራተኞች አስተዳደር

### ፲፪. ስለ ሲቪል ሠራተኞች

፩. ተቋሙ በሲቪል ሠራተኞች የሚሰሩ ሥራዎችን በመለየት ሲቪል ሠራተኞችን በሲቪል ሰርቪስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪. የቋሚ ወይም የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር በክልሉ ባሉ ተቋማት የሰዉ ሀብት ስራ አመራር ኃላፊ የሚከናወን ይሆናል፡፡

፫. ማንኛውም ሲቪል ሠራተኛ የተቋሙ ፕሮግራሞች፣ አሠራሮችና መመሪያዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፲፫. ጊዜያዊ ሠራተኛ ስለመቅጠር

ተቋሙ ክፍት በሆኑ የሥራ መደቦች በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቋሚ ቅጥር የፖሊስ ባለሙያ ወይም ሲቪል ሠራተኛ ለማግኘት አለመቻሉን ሲያረጋግጥ በጊዜያዊነት ቅጥር ሊፈጽም ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የማዕረግ ዕድገትና የኃላፊነት ቦታ ምደባ

### ፲፬. ዓላማ

የማዕረግ ዕድገት ወይም የኃላፊነት ቦታ ምደባ ዓላማ፡-

፩. ኮሚሽኑ በየማዕረጉና የኃላፊነት ደረጃዉ የሚያስፈልገዉን የሰዉ ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ወይም

፪. የፖሊስ አባላትን በማበረታታት የኮሚሽኑን የስራ አፈፃፀም ለማሻሻል ይሆናል፡፡

## 15. Suusu Lopho

1. Ayno poolisete miili suusu lopho hooltanno coyibba hooggaata agurranna tenne wodho garinni suusu keeshshanno yanna gooffuronna loosu gumulshira duushshawo guma abbiro suusu lopho afiranno.
2. Kunni quwira gufo (1) aana ofoshshiinshoonnihu agaramino gedeenni hee’reenna:
   a) 2ki Saajiinenni kayse Qaru Saajiine geeshsha no suussa aamantannohu heewotenni ikkanno;
   b) Qara Saajiinenni Kaa’laanchu Insipekterimmara, Insipekteretenni Qara Insipekterimmara assinanniti suusu lopho aamantannohu heewotenni, fonqolunninna qajeelshunni ikkanno.
   c) Komaanderetenni Kaa’laanchu Komishiinere ikkate assinanni suusu lopho qixxeessinanni bikkaano garinni heewisiisatenni ikkanno.
3. Ayno poolisete miili suusu lopho afira dandaannohu amade no suusinni aane no suusaati.
4. Ayno poolisete miili suusu lopho woy dirimu lexxo keeshshate yanna amandannihu miilu poolisete uurrinsha giddo uyno owaantenniiti.
5. Kunni quwira gufo(1) nna (3) ofoshshiinshoonniri hee’rirono:
   a) Poolisete miili luphi yitino worbimma/ጀብዱ/ woy luphi yino loosu guma abbiro woy baxxino coye kalaqiro rahotenni suusu lopho uynasira dandiinanni.
   b) Owaante uyno yanna lame dironna hakkuy ale ikkinohu lexxitewota heewisiisate bixxilloota wonshannohanna dooramate fonqolo sa’’annoha aye kaimu suusu dirimi aana hee’rannohu poolisete miili kaa’laanchu Insipekterimmate suusira heewisama dandaanno.

## ፲፭. የማዕረግ ዕድገት

፩.ማንኛውም የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገትን የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር በዚህ ደንብ መሰረት የማዕረግ ቆይታ ጊዜ ሲያጠናቅቅ እና በስራ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ዉጤት ሲያስመዘግብ የማዕረግ ዕድገት ያገኛል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ/ ከምክትል ሳጂን እስከ ዋና ሳጂን ድረስ ያሉት ማዕረጎች የሚሰጡት በውድድር ይሆናል፡፡

ለ/ ከዋና ሳጂን ወደ ረዳት ኢንስፔክተር፣ ከኢንስፔክተር ወደ ዋና ኢንስፔክተር የሚደረጉ የማዕረግ ዕድገቶች የሚሰጡት በውድድር፣ በፈተና እና በስልጠና ይሆናል፡፡

ሐ/ ከኮማንደር ወደ ረዳት ኮሚሽነር የሚደረጉ የማዕረግ ዕድገቶች በሚዘጋጁት መስፈርት መሠረት በውድድር ይሆናል፡፡

፫. ማንኛዉም የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገት ማግኘት የሚችለዉ ከያዘዉ ማዕረግ ቀጥሎ ያለዉን ማዕረግ ነዉ፡፡

፬. የማንኛዉም የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገት ወይም የዕርከን ጭማሪ የቆይታ ጊዜ የሚያዘው አባሉ በፖሊስ ተቋም ውስጥ በሰጠው አገልግሎት ነዉ፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ድንጋጌዎች ቢኖሩትም፡-

ሀ/ የፖሊስ አባል የላቀ ጀብዱ ወይም የስራ ዉጤት ሲያስመዘግብ ወይም ልዩ የፈጠራ ስራ ሲሰራ የተፋጠነ የማዕረግ ዕድገት ሊሰጠዉ ይችላል፡፡

ለ/ አገልግሎቱ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ተጨማሪ የማወዳደሪያ መስፈርቱን የሚያሟላና የመምረጫ ፈተናዉን የሚያልፍ በማንኛዉም ጀማሪ የማዕረግ ዕርከን ላይ የሚገኝ የፖሊስ አባል ለረዳት ኢንስፔክተርነት ማዕረግ መወዳደር ይችላል፡፡

6. Tenne wodho quwa (22) gufo (1) aana ofoshshiinshoonnihu suusu keeshshanno yanna heedhurono Kaa’laanchu Insipekterimmara fulannoha heewisiishshu bixxillootanna kolleeje eate fonqoli bikkaano wonshannoha aye miilino heewisama dandaanno;ikkirono qaru Saajiine suusa amadde heewisantanno miillara kayinni balanxe uynanni.
7. Tenna wodho quwa 5(b) garinni heewisante taalo gumanna dandoo afidhino poolisete miilla heedhuro, badate mehaate poolisete miila balaxisiinsanni.
8. Aye poolisete miili poolisete loosi ledo xaadooshshu noonsa loosu handaarranni afanshu noonsa rosu woy qajeelshu uurrinshanni maassammoha ikkasi suusu lopho diuysiissannosi; ikkirono suusu lopho heewora ikkiwo guma uysiisasira dandaanno.
9. Suusu lopho afira callase sooreessimmate base uysiisa hooggara dandiitanno.
10. Suusu lopho woy dirimu lexxo diroho Arfaasu woy Maaju aganira uynanni.
11. Qoqqowu Poolisete Komishiine Mannu Jiro Gashshooti Dayroktereete yanna yannatenni suusu lopho uynansara hasiisannonsata poolisete miilla taje buuxxe Qoqquwu Polisete Komishiine Komishiinerete Jeneraalera shiqishshe gumulsiisatenni suusu lopho aamantanno assitanno. Suusu lopho aanniha tittirshu wodho fushshitanno.

## 16. Suusa Kayse(Faaqe)Hoola Lainohunni

Ayehuno fajjinoonni suusi:

1. Kaphu tajenni afaminoha ikkasi buunxiro woy

፮.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው የማዕረግ ቆይታ ጊዜ ቢኖርም ለረዳት ኢንስፔክተርነት የሚወጣውን የማወዳደሪያ መስፈርትና የኮሌጅ የመግቢያ ፈተና መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውም አባል መወዳደር ይችላል፤ ሆኖም የዋና ሳጂን ማዕረግ ይዘው ለሚወዳደሩ አባላት ግን ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፭ (ለ) መሠረት በውድድሩ ተመሳሳይ ውጤትና ብቃት ያላቸው የፖሊስ አባላት ሲኖሩ ለመለየት ለሴት የፖሊስ አባል ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፰. ማንኛውም የፖሊስ አባል ከፖሊስ ሥራ ጋር ግንኙነት ባላቸው መስኮች ዕውቅና ካላቸው የትምህርት ወይም ማሰልጠኛ ተቋም የተመረቀ መሆኑ የማዕረግ ዕድገት አያስጠዉም፣ ሆኖም ለማዕረግ ዕድገት ዉድድር የተወሰነ ነጥብ ሊያስጠዉ ይችላል፡፡

፱. የማዕረግ ዕድገት ማግኘት ብቻዉን የኃላፊነት ቦታ ላያሰጥ ይችላል፡፡

፲. የማዕረግ ዕድገት ወይም የዕርከን ጭማሪ በዓመቱ ጥር ወይም ሐምሌ ወር ይሰጣል፡፡

፲፩. በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የሰዉ ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በየጊዜዉ የማዕረግ ዕድገት ሊሰጣቸዉ የሚገባቸዉን የፖሊስ አባላት መረጃ መርምሮ ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጄነራል አቅርቦ በማስወሰን የማዕረግ ዕድገት እንዲሰጥ □□ር□ል፡፡ስለማዕረግ ዕድገት አሰጣጥ ዝርዝር መመሪያ ይወጣል፡፡

## ፲፮. ማዕረግን ስለመሰረዝ

ማንኛዉም የተፈቀደ ማዕረግ፡-

፩. በሀሰተኛ ማስረጃ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም

2. Seera sa''atenni uynoonniha ikkiro aye yannarano kaynse hoollanni.
3. Kunni quwi gufo (1) nna (2) aana ofoshshiinshoonnihu agarammo gedeenni hee'reenna afantino(afi'rino) suusu lophonni baantoonni baatooshshi hee'riro shallange woxe qolanno gede assinanni.
4. Ayno poolisete miili suusu lopho afiranno gede afanni hee're seera sa''atenni kaa'lino sooreessi woy heewisiisaanchi amanyoote hunasinni hasiisawo garinni jaddotenni xa'mamawoha ikkanno.

## 17. Sooreessimmate Base Gaamooshshe

Ayno poolisete miili:

1. Babbaxxitino heewisiishshu bixxillootinni heewisame sooreessimmate basera gaamame loosanno gede assa dandiinanni.
2. Mimmito roorte yitinokki dandoo noonsa miilla mereero doorante shiqqinote mehaa poolisete miilara balanxe uynannise.
3. Ayno poolisete miili sooreessimmate basera heewisama dandaannohu amade no sooreessimmate basenni mitto dirima gotti yino sooreessimmate dargira callaati, ikkirono baxxinohu ogimmate dandoo noosita buunxironna uurrinshate gashshootu(massagaanote) gaamo fajjituro amade no sooressimmate darginni lame dirima gotti yino sooreessimate dargira heewisama dandaanno.
4. Sooreessimmate dargi gaamooshshe uynannihu base xa'mitannoha rosu deerra, loosu gumulshi ikkadimma/dandoo/, dancha loosu amanyoote, owaantete diro wonshe hasiisawo garinnino qixxeessinoonniha fonqolo sairo ikkanno.
5. Sooreessimmate baatooshshe baatisiissawo basera gaamame loosanna sooreessimmate baatooshshe/damooza/ baantannisiha ikkanna, sooreessimmasinni kairo sooreessimmate baatooshshisino uurranno.

፪.ህግን በመተላለፍ የተሰጠ ከሆነ በማንኛዉም ጊዜ ይሰረዛል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በተገኘዉ የማዕረግ ዕድገት የተፈፀመ ክፍያ ካለ ታስቦ ገንዘቡን እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

፬. ማንኛዉም የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገት እንዲያገኝ ሆን ብሎ ህግን በመተላለፍ የረዳ የሥራ ኃላፊ ወይም አወዳዳሪ በዲሲፕሊን እንዳስፈላጊነቱ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፲፯. የኃላፊነት ቦታ ምደባ

ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

፩. በተለያዩ መስፈርቶች ተወዳድሮ በኃላፊነት ቦታ ተመድቦ እንዲሰራ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪. ተቀራራቢ ብቃት ባላቸዉ አባላት መካከል በዕጩነት የቀረበች ሴት የፖሊስ አባል ቅድሚያ ይሰጣታል፡፡

፫. ማንኛዉም የፖሊስ አባል ለኃላፊነት ቦታ መወዳደር የሚችለዉ ከያዘዉ ኃላፊነት ቦታ አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ላለዉ የኃላፊነት ቦታ ብቻ ነዉ፣ ሆኖም የተለየ ሙያዊ ብቃት እንዳለዉ ሲረጋገጥና የተቋሙ ማኔጅመንት ሲፈቅድ ከያዘዉ የኃላፊነት ቦታ በሁለት ደረጃ ከፍ ላለዉ የኃላፊነት ቦታ ሊወዳደር ይችላል፡፡

፬. የኃላፊነት ቦታ ምደባ የሚሰጠው ለቦታው ተፈላጊውን የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ አፈጻጸም ብቃት፣መልካም ሥነ-ምግባር፣ የአገልግሎት ዘመን አሟልቶ እንዳስፈላጊነቱም የተዘጋጀዉን ፈተና ሲያልፍ ይሆናል፡፡

፭. የኃላፊነት ደመወዝ በሚያስከፍል ቦታ ተመድቦ ሲሰራ የኃላፊነት ደመወዝ የሚከፈለው ሲሆን ከኃላፊነቱ ሲነሳ የኃላፊነት ደመወዙም ይቋረጣል፡፡

6. Sooreessimmate baychi gaamooshshi suusu lopho diuysiisanno, ikkirono suusu lopho heewora mitte bikkaancho bixxille gede assine hedo uynasira dandiinanni.
7. Sooreessimmate baychi gaamooshshira dooraante shiqqinoti poolisete miilla mittu dani heewote guma abbituro, suusu balaxe aamaminosihura balanxe uynanni.

## 18. Suusu Dirimi Lopho Fajjatenna Hoolate(Faaqate) Biilloonye

1. Komishiinerchu woy $2^{nki}$ Komishiinerchi woy Kaa’laanchu Komishiinerchi suusu lopho Komishiinere Jeneraalenni shiqqeenna Qoqqowu Pirezidaantichinni gumulantanno.
2. Qara Insipekterenni Komaanderete geeshsha nooti suusu lopho Komishiinete Mannu Jiro Gashshooti Dayrektoreete widoonni shiqqe Komishiinere Jeneraaletenni gumulantanno.
3. $2^{nki}$ Insipekterenni Insipekterete geeshsha nooti suusu lopho Komishiinete Mannu Jiro Gashshooti Dayrektoreete widoonni shiqqe $2^{nki}$ Komishiinere Jeneraalenni gumulo afidhanno.
4. Kaa’laanchu Saajiinenni Qara Saajiine geeshsha nooti suusu lopho Komishiinete Mannu Jiro Gashshooti Dayroktereete Dayrekterenni gumulantanno.
5. Amanyootu kissera uynanni gumulo agarantewo gedeenni heedheenna ayetino suusu lopho fajjo afidhu yannara kalaqantino soronni hoolate(faaqate) gumulo uynannihu kunni quwi garinni suusu lopho fajjote(gumulate) biilloonye uynoonnisi bisinni callaati.

፮. የኃላፊነት ቦታ ምደባ የማዕረግ ዕድገት አያሰጥም፣ ሆኖም ለማዕረግ ዕድገት ውድድር እንደ አንድ መስፈርት ግምት ሊሰጠዉ ይችላል፡፡

፯. ለኃላፊነት ቦታ ምደባ በዕጩነት የቀረቡ የፖሊስ አባላት ተመሳሳይ የውድድር ዉጤት ካስመዘገቡ የማዕረግ ቀደምትነት ላለዉ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

## ፲፰. የማዕረግ ዕድገት የማጽደቅና የመሰረዝ ሥልጣን

፩. የኮሚሽነር ወይም የምክትል ኮሚሽነር ወይም የረዳት ኮሚሽነር የማዕረግ ዕድገት በኮሚሽነር ጄነራል አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይፀድቃል፡፡

፪. ከዋና ኢንስፔክተር እስከ ኮማንደር ያለዉ የማዕረግ ዕድገት በኮሚሽኑ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት አቅራቢነት በኮሚሽነር ጄነራል ይፀድቃል፡፡

፫.ከምክትል ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር ያለዉ የማዕረግ ዕድገት በኮሚሽኑ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት አቅራቢነት በምክትል ኮሚሽነር ጄነራል ይፀድቃል፡፡

፬. ከረዳት ሳጅን እስከ ዋና ሳጅን ያለዉ የማዕረግ ዕድገት በኮሚሽኑ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ይፀድቃል፡፡

፭. በዲሲፕሊን ክስ የሚሰጥ ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የማዕረግ ዕድገት በተፈቀደበት ወቅት በተፈጠረ ስህተት የመሰረዝ ውሳኔ የሚሰጠዉበዚህ አንቀጽ መሠረት የማዕረግ ዕድገቱን ለማጽደቅ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ይሆናል፡፡

## 19. Sooreessimmate Basera Mootoo’manna Gaamama Lainohunni

### 1. Komishiinete:

Komishiinete uurrinshshi lallawu kiiro 7/2012 quwa 11 gufo (1) nna quwa 13 gufo 2(A nna B) garinni ikkanno.

**2. Zoonetanna Hawaasi Quchuminna Woradaho**

a) Zoonetenna Hawaasi Quchumi Gashshooti Poolisete Sooreessa poolisete mokkonninooti mereerinni dandoo noosiha poolisete koomishiinete Komishiinere Jeneraale gaamtanno.

b) Zoonetenna Hawaasi Quchumi Gashshooti Poolisete 2nki dayrek teroota poolisete mokkonninooti mereerinni dandoo noonsare Zoonetenna Hawaasi Quchumi Gashshooti Poolisete Sooreeyye shiqishsheenna Qoqqowu Poolisete Komishiinete Komishiinere Jeneraale gaamtannonsa.

**3. Woradaho woy Quchumu Gashshootira woy Sinu Quchumira**

a) Woradu woy quchumu gashshooti woy sinu quchumi poolisete sooreessa Zoonete woy Hawaasi Quchumi Poolisete Sooreessi shiqishsheenna poolisete mokkonninooti mereerinni Qoqqowu Poolisete Komishiinete Komishiinere Jeneraale gaamtannonsa.

b) Woradu woy Quchumu gashshooti woy sinu quchumi poolisete qineessate sooreeyyepoolisete mokkonninootinna miilla mereerinni Zoonete woy Hawaasi Quchumi Poolisete loosu massagaano komite gaamtanno.

## ፲፱. በኃላፊነት ቦታ ስለመሾምና ስለመመደብ

### ፩.በኮሚሽን፡-

በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፯/፪፻፲፪ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሀ እና ለ) መሰረት ይከናወናል፡፡

**፪. በዞን ወይም በሀዋሳ ከተማ፡-**

ሀ) የዞን እና የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኃላፊ ከፖሊስ መኮንኖች መካከል ብቃት ያለዉ በፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል ይመደባል፡፡

ለ) የዞን ወይም የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ምክትል ዳይሬክተሮችን ከፖሊስ መኮንኖች መካከል ብቃት ያላቸዉ በዞን እና በሀዋሳ ከተማ ፖሊስ ኃላፊዎች አቅራቢነት በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል ይመደባሉ፡፡

**፫.በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ ከተማ፡-**

ሀ) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ ከተማ ፖሊስ ኃላፊ በዞን ወይም በሀዋሳ ከተማ ፖሊስ ኃላፊ አቅራቢነት ከፖሊስ መኮንኖችና አባላት መካከል በፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል ይመደባሉ፡፡

ለ) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ ከተማ ፖሊስ ማስተባበሪያ ኃላፊዎችን ከፖሊስ መኮንኖችና አባላት መካከል በዞን ወይም በሀዋሳ ከተማ ፖሊስ የስራ አመራር ኮሚቴ ይመደባሉ፡፡

### 4. Sooreessimate Mootimma Kaysa/hoola/

Kunni quwira sooreessimmate baychi gaamooshshe uynoonniha poolisete mokkonnine sooreessimmate baychinni kaysannohu tenne wodhonni sooreessimmate dargira gaamate biilloonye uyinoonnisi bisooti.

## 20. Suusu Lophonna Sooreessimmate Baychi Gaamooshshe Uysiissannokki Coyibba

Ayno poolisete miili:

1. Tenne wodho quwa (60) garinni amanyootunni kassasamme kissesi ha’rinshote aana noohu woy amanyootunni qorichi gumulo uynoonnisi miili qorchisi dannunni/yirgunni/ gata hoogiro woy dannu/yirgu/ yannasi iillitukkinni balaxe faaqama hoogisiro woy woyyeessama hoogisiro,
2. Owaante tenne wodho garinni seeddannosikkiha ikkiro xurata fulate mittu diri woy hakkuy wori gatisiro,
3. Aye dani jaddonni kassanseenna biilloonye afi’rinohu yoote mini qorichishinohu woy gumulo uyinosihu qorichasi woy uynoonnisi yoo gude loosoho higi yannanni kayse lame diro wo’minoosikkihu,
4. Higgaawe biillonyi noosi bisi qorichu gumulo aasira dandaanno hunonni huluullaammeennasi buuxote woy kissete ha’rinsho aana noohu poolisete miili suusu lophora woy sooreessimmate baychi gaamooshshira heewisama didandaanno.

## 21 Suusu Su’mubba

Qoqqowu Poolisete suusu su’mubba:

1. Konsitaable;
2. Kaa’laancho Saajine;
3. Layinki Saajine;
4. Saajine;
5. Qara Saajine;
6. Kaa’laancho Insipekitere;

### ፬. ከኃላፊነት ምደባ ስለማንሳት፡-

በዚህ አንቀጽ የኃላፊነት ቦታ ምደባ የተሰጠዉ የፖሊስ መኮንን ከኃላፊነት ቦታ የሚነሳዉ በዚህ ደንብ የኃላፊነት ቦታ ለመመደብ ስልጣን በተሰጠዉ አካላት ይሆናል፡፡

## ፳.ለማዕረግ ዕድገትና ለኃላፊነት ቦታ ምደባ የማያበቁ ሁኔታዎች

ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ((፳)) መሠረት በዲሲፒሊን ተከሶ ክሱ በሂደት ላይ የሚገኝ ወይም የዲሲፕሊን ቅጣት የተወሰነበት አባል ቅጣቱ በይርጋ ቀሪ ካልሆነ ወይም ከይርጋ ጊዜው ቀድሞ ካልተሰረዘለት ወይም ካልተሻሻለለት፣

፪. አገልግሎቱ በዚህ ደንብ መሰረት የሚራዘምለት ካልሆነ በስተቀር ጡረታ ለመውጣት አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በታች የቀረዉ፣

፫. በማንኛውም ዓይነት የወንጀል ድርጊት ተከሶ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተቀጣ ወይም የተፈረደበት ቅጣቱን ወይም ፍርዱን ፈጽሞ ወደ ስራ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያልሞላዉ፡፡

፬. ሕጋዊ ሥልጣን ባለው አካል የቅጣት ውሳኔ ሊያሰጥበት በሚችል ጥፋት ተጠርጥሮ በምርመራ ወይም በክስ ሂደት ላይ ያለ የፖሊስ አባል ለማዕረግ ዕድገት ወይም ለኃላፊነት ቦታ ምደባ መወዳደር አይችልም፡፡

## ፳፩.የማዕረግ ስያሜዎች

የክልሉ ፖሊስ የማዕረግ ስያሜ፡-

፩. ኮንስታብል፣

፪. ረዳት ሳጅን፣

፫. ምክትል ሳጅን፣

፬. ሳጅን፣

፭. ዋና ሳጅን፣

፮. ረዳት ኢንስፔክተር፣

7. Layinki Insipekitere
8. Insipektere;
9. Qara Insipekitere;
10. Layinki Komaandere;
11. Komaandere;
12. Kaa’laancho Komishiinere;
13. Layinki Komishiinere;
14. Komishiinere;
15. Layinki Komishiiner Jeneraale;
16. Komishiiner Jeneraaleti

## 22. Suusu Deerra, Keeshsha, Lophonna Dirima Lainohunni

1. Qoqqowu poolisera konni woroonni shaete giddo worroonniri suusu deerri, keeshshawo yanna, lophonna dirimu noose.

| Suusu Dirima | Suusu Deerra | Keeshshan no yanna Dirunni |
|---|---|---|
| Kaimu Suusi Dirima | Konstaable | 3 |
| | Kaa’laancho Saajine | 2 |
| | Layinki Saajine | 2 |
| | Saajine | 2 |
| | Qara Saajine | 2 |
| Mereerimu Suusi Dirima | Kaa’laancho Insipekitere | 2 |
| | Layinki Insipekitere | 3 |
| | Insipekitere | 3 |
| Jawiidi Suusu Dirima | Qara Insipekitere | 3 |
| | Layinki Komaandere | 3 |
| | Komaandere | 4 |
| | Kaa’laancho Komishiinere | 4 |
| | Layinki Komishiinere | 4 |
| Istiraateejikete Suusi Dirima | Komishiinere | - |
| | Layinki Komishiiner Jeneraale | - |
| | Komishiiner Jeneraale | - |

፯. ምክትል ኢንስፔክተር፣
፰. ኢንስፔክተር፣
፱. ዋና ኢንስፔክተር፣
፲.ምክትል ኮማንደር፣
፲፩. ኮማንደር፣
፲፪. ረዳት ኮሚሽነር፣
፲፫. ምክትል ኮሚሽነር፣
፲፬. ኮሚሽነር
፲፭. ምክትል ኮሚሽነር ጄነራል
፲፮. ኮሚሽነር ጄነራል ናቸው፡፡

## ፳፪. ስለማዕረግ ደረጃ፣ቆይታ፣ዕድገት እና ዕርከኖች

፩.የክልሉ ፖሊስ ከዚህ በታች በሠንጠረዡ የተመለከቱት የማዕረግ ደረጃ፣ ቆይታ ጊዜ፣ ዕድገት እና እርከኖች ይኖሩታል፡፡

| የማዕረግ ዕርከኖች | የማዕረግደረጃዎች | የቆይታ ጊዜ በዓመት |
|---|---|---|
| የጀማሪ ማዕረግ እርከን | ኮንስታብል | 3 |
| | ረዳት ሳጅን | 2 |
| | ምክትል ሳጅን | 2 |
| | ሳጅን | 2 |
| | ዋና ሳጅን | 2 |
| የመካከለኛ ማዕረግ እርከን | ረዳት ኢንስፔክተር | 2 |
| | ምክትል ኢንስፔክተር | 3 |
| | ኢንስፔክተር | 3 |
| የከፍተኛ ማዕረግ እርከን | ዋና ኢንስፔክተር | 3 |
| | ምክትል ኮማንደር | 3 |
| | ኮማንደር | 4 |
| | ረዳት ኮሚሽነር | 4 |
| | ምክትል ኮሚሽነር | 4 |
| የስትራቴጂክ ማዕረግ እርከን | ኮሚሽነር | - |
| | ምክትል ኮሚሽነር ጄነራል | - |
| | ኮሚሽነር ጄነራል | - |

2. Aye poolisete miili heewote shiqqara albaanni amadinosuusinni konni aleenni shaete aana mittu mittunku suusira murroonnita keeshshate yanna guda noosi.

## 23. Suusu Malaate

Aye poolisete miili loosu/wodhote/ uddano ledo wodhinannihanna suusu deerrasi leellisha dandaannoha suusu malaate wodhanno.

# GAFA ONTE

## Damoozanna Addi Addi Barru Hoshsho

## 24. Damoozu Baatooshshi Gumulsha

1. Aye poolisete miilira:
   a) Gaamamino loosira mangiste murtinoha(gumultinoha) aganu damooza baantannisi;
   b) Damoozu baatooshshe assinannihu aganu aganu goofimarchiraati.
2. Baxxino gari xaada hoogi geeshsha, damooza loosu barranna loosu darga woy uurrinsha murtanno(gumultanno) wole basera baantanni.
3. **3.** Seeru (higgete) woy wolu garinni gumulama hoogi geeshsha, damoozu baatamannohu miilaho angasira woy miilu borrotenni riqiwino manchira callaati.
4. Qoqqowu Womaashshunna Miinju Latishshi Biiro mangistete loosaasinera damoozu liqoo baantay gari woy damoozunni murre qolsiinsay gari aana fushshitino jirte poolisete miilla aana guutisamantannota ikkitanno.

## 25. Damoozu Lexxo Daafira

1) Loosu gumulshi keeno gumi duushshawohanna hakkuy ale ikkinosi poolisete miili amadino suusinni lamu lamu dirinni dirimu lexxo afi’ranno.

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል ለውድድር ከመቅረቡ በፊት በያዘው ማዕረግ ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ ላይ ለእያንዳንዱ ማዕረግ የተወሰነውን የቆይታ ጊዜ መሸፈን አለበት፡፡

## ፳፫.የማዕረግ ምልክት

ማንኛውም የፖሊስ አባል ከደንብ ልብሱ ጋር የሚደረግ ፖሊስነቱን እና ማዕረጉን ሊያሳይ የሚችል የማዕረግ ምልክት ያደርጋል፡፡

# ክፍል አምስት

## ስለደመወዝና ልዩ ልዩ አበል

## ፳፬.ስለደመወዝ ክፊያ አፈጻፀም

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) ለተመደበበት ሥራ በመንግስት የተወሰነ የወር ደመወዝ ይከፈለዋል፣

ለ) የደመወዝ ክፍያ የሚደረገው በየወሩ መጨረሻ ነው፡፡

፪. የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ደመወዝ በሥራ ቀንና በሥራ ቦታ ወይም ተቋሙ በሚወስነው ሌላ ቦታ ይከፈላል፡፡

፫. በሕግ ወይም በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር ደመወዝ የሚከፈለው በቀጥታ ለአባሉ ወይም አባሉ በጽሁፍ ለወከለው ሰው ብቻ ነው፡፡

፬. የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ብድር አከፋፈል ወይም አመላለስ ያወጣው መመሪያ በፖሊስ አባላትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፳፭.ስለደመወዝ ጭማሪ

፩.የስራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ አጥጋቢና ከዚያ በላይ የሆነ የፖሊስ አባላ በያዘው ማዕረግ በየሁለት ዓመቱ የዕርከን ጭማሪ ያገኛል፡፡

2) Duushshawoha, luphi yiinoha woy hakkuy aliha loosu gumulshi guma afi’rinohu poolisete miili loosu gumulshisi garinni dirimu lexxo afi’rawo gede assinanni. Tittirshu jirtetenni gumulamanno.
3) Duushshawoha loosu gumulshi guma afi’rinokkihu poolisete miili suusu lophonna damoozu dirimi lopho(lexxo) diafi’ranno.
4) Sooreessimmate basera gaamamannohu aye sooreessira baantannisihu sooreessimmate dargi baatooshshi amadino suusinni baatooshshu suusu qaccenni roorannokkiha(sa’’annokkiha) ikkiro suwashsho(medewanya) lamu diri dirimu baatooshshe wonshinannisi.
5) Mittu poolisete miilira luphi yinoha sooreessimmate gaamooshshe uynisiro, haaru baychira murroonniha(fajjinoonniha) kaimu damooza afi’ranno;ikkirono gaamooshse afirara albaanni afi’ranni keeshshino damoozi haaru baychira fajjinoonnihu kaimu damoozi aleenni woy taalo ikkewoha ikkiro, mittu dirimi damoozu lexxo afi’ranno.
6) Mittu poolisete miili suusu lopho afi’rara albaanni, afi’ranni keeshshino damoozu suusu lopho afi’rewo deerrinni murroonni kaimu damoozi aleenni woy taalo ikkewoha ikkiro amadino suusinni damoozu qacce saikkinni haaro damooza afi’rara albaanni afi’ranni keeshshino damoozinni aane nooha dirimu damooza afi’ranno. Ikkirono, tini dirimu lexxo dhaaddu dirimi gede (እንደመደበኛእርከን)kiiranteenna aane daanno dirima dihoollanni.

## 26. Damoozu Baatooshshe Amadanna Mure Ajisha Lainohunni

1. Aye poolisete miili damoozi:
   a) Seeru woy Yoote mini hajajo garinni ikka hoogiro woy miilu borrote aana sumuu yaa hoogiro xeinsara woy asalunni amadamara woy dandee gatara didandaanno.

፪. አጥጋቢ፣ ከፍተኛ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ያገኘ የፖሊስ አባል እንደ ሥራ አፈጻጸሙ ዕርከን ጭማሪ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. አጥጋቢ የስራ አፈጻጸም ውጤት ያላገኘ የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገትና የደመወዝ ዕርከን ጭማሪ አያገኝም።

፬. ኃላፊነት ቦታ ላይ የሚመደብ ማንኛውም አመራር የሚከፈለው የኃላፊነት ቦታ ክፍያ በያዘው ማዕረግ ክፍያው ከማዕረጉ ጣሪያ የማይበልጥ ከሆነ መደበኛ የሁለት ዓመት የዕርከን ክፍያ ይፈጸምለታል፡፡

፭. አንድ አባል ከፍ ያለ የኃላፊነት ቦታ ምደባ ሲሰጠው ለአዲሱ ቦታ የተመደበውን መነሻ ደመወዝ ያገኛል። ሆኖም ምደባውን ከማግኘቱ በፊት ያገኝ የነበረው ደመወዝ ለአዲሱ ቦታ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ የአንድ ዕርከን ደመወዝ ጭማሪ ያገኛል።

፮. አንድ የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገት ከማግኘቱ በፊት ያገኝ የነበረው ደመወዝ የማዕረግ ዕድገት ካገኘበት ደረጃ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ በያዘዉ ማዕረግ የደመወዝ ጣሪያዉን ሳያልፍ አዲሱን ደመወዝ ከማግኘቱ በፊት ያገኝ ከነበረው ደመወዝ ቀጥሎ ያለውን የዕርከን ደመወዝ ያገኛል፡፡ ሆኖም ይህ የዕርከን ጭማሪ እንደ መደበኛ እርከን ተቆጥሮ ቀጣይ ዕርከን አይከለከልም፡፡

## ፳፮.የደመወዝ ክፍያ ስለመያዝና መቀነስ

፩. የማንኛውም የፖሊስ አባል ደመወዝ፦

ሀ) በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ካልሆነ ወይም አባሉ በጽሁፍ ካልተስማማ በስተቀር ሊቀነስ ወይም በዕዳ ሊያዝ ወይም ሊቻቻል አይችልም፡፡

b) Mitte hinge miilu damoozi aaninni xaphoomunni muramara dandaannohuwomaashshu bikki aye doogonnino xalalu damoozisi (angara eanno damoozisi) aaninni 1/3 sa"a dinosi.

c) Mittu miili 21 barri ale loosisi aana leella hoogiro, gumulo uynaysi yanna geeshsha damoozasi baantannikki gede ittisa dandiinanni. Gatino karkaati ammansiisawoha ikkiro, kayinni damoozisi qallo noyikkiha baatamasira dandaanno.

2. Aye poolisete miili loosanni keeshshino uurrinshanni liqii'rinoti harancho woy faynaansenni seeda yanna liqoo asali hee'risiro, soorri're marino uurrinsha uynoonnise mashalaqqe garinni asalesi baychonkonni murte(xeisse) haadhanni loosanni keeshshiwo uurrinshara sokkanno.

## 27. Addi Addi Barru Hoshshonna Baxxewo Baatooshshe (Various Allowances and Special Payment)

1. Aye poolisete miilira Koomishiinetelooso garunni wonshate hasiisannoha ikkiro barru hoshsho baantanni.
2. Aye poolisete miilira uynanni barru hoshsho womaashshu barru hoshsho baatooshshi jirte garinni ikkanno.
3. Uurrinsha kokkete (qallawu) nna hodhishshu barru hoshsho hasiissewo yannara baatooshshe assitanno.
4. Addi wolqa poolisete miilira loosisi akatinna hee'rawo garinni la'ne addi sagalete (qallawu) kaa'lo assinannisi.
5. Ayno poolisete miili poolisete uurrinshubba xaginatu kifilla wolqa aleenni ikkitino xisso xaaddeennassi Federaale Poolisete Riferaale Hospitaale ha'rawo gede ogeessunni gumulliro, Addisabeba iille higannota hodhishshu fulonna ha'rannotanna higannota barru hoshsho fulo baantannisi.

ለ)በአንድ ጊዜ ከአባሉ ደመወዝ ላይ በአጠቃላይ ሊቆረጥ የሚችል የገንዘብ መጠን በምንም አኳኋን ከተጣራ የወር ደመወዙ አንድ ሶስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

ሐ) አንድ አባል ከ21 ቀን በላይ በስራዉ ላይ ካልተገኘ ውሳኔ እስከሚሰጠዉ ጊዜ ድረስ እንዳይከፈል ማገድ ይቻላል፡፡ የቀረበት ምክንያት አሳማኝ ከሆነ ግን ደመወዙ ያለወለድ ሊከፈለዉ ይችላል፡፡

፪. ማንኛዉምየፖሊስ አባል ሲሰራበት ከነበረዉ ተቋም የአጭር ወይም ከፋይናንስ የረጅም ጊዜ ብድር ዕዳ ካለበት የተዛወረበት ተቋም በሚሰጠዉ መረጃ ዕዳዉን ወዲያዉኑ እየቀነሰ ለነበረበት ተቋም ይልካል።

## ፳፯.ስለ ልዩ ልዩ አበሎችና ልዩ ክፍያ

፩. ለማንኛውም የፖሊስ አባል የኮሚሽኑን ሥራ በሚገባ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አበል ይከፈላል፡፡

፪. ለማንኛውም የፖሊስ አባል የሚሰጠው አበል በፋይናንስ የአበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

፫. ተቋሙ የቀለብና የመጓጓዣ አበል አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፬. □ል□ ኃዱል □ሊስ አባል ከስራዉ ባህሪና አኗኗር አንፃር ልዩ የቀለብ ድጎማ ጁ□ረ□ለታል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፭. ማንኛ□ም የፖሊስ አባል ከፖሊስተቋማት የህክምና ክፍሎች አቅም በላይ የሆነ ህመም አጋጥሞት ወደ ፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስ□ታል□እንዲሄድ በባለሙያ ሲወሰን አዲስ አበባ የደርሶ መልስ የትራንስፖርት እና የመሄጃና የመመለሻ ቀን አበል ወጪ ይከፈለዋል፡፡

## GAFA LEE

### WODHOTE UDDANO, QODHO, SUMUDANNA AYIMMATE DAFTARA LAINOHUNNI

### 28. Wodhote Uddanonna Qadho

1. Koomishiinete loosunna ayyaanu barri wodhote uduunni hee’rannose.
2. Wodhote uddano woy qodhote aana hee’ranno armi daninna kuuli qoqqowonna uurrinsha xawissawota ikkite koomishiine fushshitanno jirtenni gumulamantanno.
3. Addi soqqansho wonshate koomishiinetenni uurritino loosu kifilla wodhote uddannonna qodhote dananna kuulla koomishiine fushshitawo jirtenni (wodhote tittirshinni) gumulamantanno.

### 29.Qodhotenna Wodhote Uduunni Beehaache

1. Koomishiine loosoho hasiisannoha wodhote uddanonna qodho shiqishanno.
2. Aye poolisete miili afi’rannota wodhote uddanonna qodho lainohunni koomishiine fushshitanno jirtenni (wodhote tittirshinni) gumulamanno.

### 30. Sumudu Amado

Koomishiinete sumudi seeru hunda gala, seera ayirrisiisanna dagate owaante aa xawisanno.

### 31. Sumudunna Baajete Ho’roonsirama

1. Koomishiinete sumudi poolisete ayimmate daftaari, kooffinyaho (mallayyote), wodhote uduunni woy poolisete kaameeli woy Koomishiine murtannowa (gumultannowa)woloota baychubba aana worama dandaano.
2. Ayeranno poolisete miila ikkinohura ayimmasinna loosu dilaalasi(qeechasi) xawissanno baaje heedhannosi.

## ክፍል ስድስት

### ስለደንብ ልብስ፣ ትጥቅ፣ ዓርማና መታወቂያ

### ፪፰.ደንብ ልብስና ትጥቅ

፩. ኮሚሽኑ የሥራና የክብረ በዓል የደንብ ልብሶች ይኖሩታል፡፡

፪. በደንብ ልብስ ወይም በትጥቅ ላይ ስለሚያርፉ ዓርማዎች ዓይነትና ቀለማት ክልሉንና ተቋሙን ገላጭ ሆኖ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. ልዩ ተልዕኮ ለመፈፀም በኮሚሽኑ የሚቋቋሙ የስራ ክፍሎች የደንብ ልብስና ትጥቅ ዓይነትና ቀለማት ኮሚሽኑ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፪፱.ትጥቅና የደንብ ልብስ ዕደላ

፩. ኮሚሽኑ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የደንብ ልብስና ትጥቅ ያቀርባል፡፡

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል ስለሚያገኘው የደንብ ልብስና ትጥቅ በኮሚሽኑ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፴.የዓርማው ይዘት

የኮሚሽኑ ዓርማ ለህግ ተገዥነትን፣ ሕግ አስከባሪነትና የሕዝብ አገልጋይነትን የሚያንጸባርቅ ይሆናል፡፡

### ፴፩.የዓርማና ባጅ አጠቃቀም

፩. የኮሚሽኑ ዓርማ በፖሊስ መታወቂያ ካርድ፣ በመለዮ፣በደንብ ልብስ ወይም በፖሊስ ተሽከርካሪ ወይም በፖሊስ ተቋማት እና ኮሚሽኑ በሚወስነው ሌሎች ቦታዎች ላይ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል ማንነቱና የሥራ ድርሻውን የሚገልጽ ባጅ ይኖረዋል፡፡

3. Addi addi loosu kifillara loosinsa akati garinni Koomishiinete sumudi gobbaanni wolu uminsa badooshshu sumudi hee’ransara dandaanno.
4. Sumudunnihu kuulu poolise leellanno garinno dagate giddo baxxitanno gede assanno.

## 32. Badooshshu Kiironna Ayimmate Kaarde Lainohunni

1. Ayno poolisete miili qoqqowu poolise miila ikkewota xawissannoti koomishiinetenni qixxaabbannotinna aamantannoti ayimmate kaarde heedhannosi.
2. Poolisete miiliti ayimmate kaarde qoqqowu poolise sumuda, miilu foto, wo’ma su’ma, suusa, dana, hojja, mundeete dananna baxxate kiiro amaddanno.
3. Ayno poolisete mila ikkinohu:
   a) Seera agarsiisawo woyte ayimmate kaarde rahotenni afi’ra dandaanno baycho woranna leellisha noosi.
   b) Wolootunni baxxe leellannoti badooshshu kiiro heedhannosi; kiirono wodhote (uniform) aana xawunni leeltanno garinni gagasoho gura widoonni wodhinanni.

## GAFA LAMALA

## Loosu Sa”aatenna Addi Addi Fajjo

## 33. Loosu Sa”aate

1. Poolisete owaante barrunni 24 sa”aate, lamalatenni 7 barra, agaunni 30 barranna dirunni 365/6 barra uurrisikkinni aamatanno.
2. Aye poolisete miilira worroonniti loosu sa”aate barrunni sette sa”aate ikkitanno.
3. Kunni quwira gufo (2) aana ofoshshiinshoonnihu agarammo gedeenni hee’reenna ikkito gaddadduro miilu tirfe sa”aate loosara uurrinsha hajajiuro loosate gaddado noosi.

፫. ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች እንደሥራ ፀባያቸው ከኮሚሽኑ ዓርማ በተጨማሪ የራሳቸው መለያ ዓርማ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

፬. ዓርማው የሚይዛቸው የቀለም ዓይነቶች ፖሊስ በቀላሉ በሕብረተሰቡ ዘንድ እንዲለይ የሚያደርጉ ይሆናል፡፡

## ፴፪.ስለመለያ ቁጥር እና መታወቂያ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል የክልሉ ፖሊስ አባል መሆኑን የሚገልጽ በኮሚሽኑ የሚዘጋጅ እና የሚሰጥ የመታወቂያ ካርድ ይኖረዋል፡፡

፪. የፖሊስ አባል መታወቂያ ካርድ የክልሉ ፖሊስ ዓርማ፣የአባሉ ፎቶግራፍ፣ሙሉ ስም፣ ማዕረግ፣መልኩ፣ቁመቱ፣የደም ዓይነት እና መለያ ቁጥር ይይዛል፡፡

፫. ማንኛውም የፖሊስ አባል

ሀ) ሕግ ሲያስከብር የመታወቂያ ካርዱን በፍጥነት ሊያገኝ በሚችልበት ቦታ ማስቀመጥና ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ለ) ከሌሎች ተለይቶ የሚታወቅበት መለያ ቁጥር ይኖረዋል፣ቁጥሩም በዩኒፎርሙ ላይ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ በደረቱ በግራ በኩል ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የሥራ ሰዓትና ልዩ ልዩ ፈቃዶች

## ፴፫.መደበኛ የሥራ ሰዓት

፩.የፖሊስ አገልግሎት በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት፣ በወር 30 ቀናት እና በዓመት 365/6 ቀናት ያለማቋረጥ ይሰጣል፡፡

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን ስምንት ሰዓት ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁኔታዎች ሲያስገድዱ አባሉ የትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲሰራ በተቋሙ ሲታዘዝ የመሥራት ግዴታ አለበት፡፡

4. Tirfe sa”aate looso loosino poolisete miilira foliishsho lende kiinsannisi.
5. Kunni quwira gufo (3) aana xawinsoonnihu hee’rirono, koomishiine gama loossara tirfe sa”aate baatooshshe assate tittirshu wodho fushshitara dandiitanno.

## 34. Diru Fooliishsho Fajjo

1. Diru fooliishsho fajjo uynannisihu poolisete miili murantewo yanna geeshsa fooliishshi’re owaantesi haaroo’mitino giddonni sufisanno gede dandaanno gede assateeti.
2. Ayno haaru qaxaraminohu poolisete miili 11 agana owaante aara albaanni diru fooliishsho fajjo afi’rate qoosso dinosi.
3. Diru fooliishsho fajjo woxeho disoorrinanni.

## 35. Diru Fooliishsho Fajjo Barrubba

1. Mitto diro owaante uynohu poolisete miili lemuu loosu barri diru fooiishsho fajjo afi’ranno.
2. Mittu diri ale owaante uynohu poolisete miilira mittu mittunku lexxawo dirira mitto loosu barra lendanni diru fooliishsho fajjo uynannisi. Ikkirono uynannisiti mittu diri fooliishshote fajjo 30 loosu barrubba sa”a dinose.
3. Ayno poolisete miili konni albaanni wole mangistete uurrinshara uyno owaante kunni quwi gufo (2) gumulshira hedote e’annota ikkitanno.

## 36. Diru Fooliishsho Fajjo Uynay Gara

1. Diru fooliishsho fajjo uurrinshate mixo aana kaima assine miilu hasatto garinni la’ne qixxeessinoonni progiraame garinni baajeettete diri giddo uynanni.
2. Mittu poolisete miili diru fajjo uynannisi wote, mittu agani damoozasi balaxe adha dandaanno.
3. Poolisete miili diru fooliishsho fajjosi babbande(beenke) uynasira x’mi’riro, muli sooreessisi sumuu yiiro babbandenna(bebbeenkeenna) adha dandaanno.

፬. የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሰራ የፖሊስ አባል የማካካሻ እረፍት ይሰጠዋል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተጠቀሰው ቢኖርም ኮሚሽኑ ለተወሰኑ ሥራዎች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስለሚፈፀምበት ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፴፬.የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚሰጥበት መርህ

፩. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚሰጠው የፖሊስ አባሉ ለተወሰነ ጊዜ በማረፍ አገልግሎቱን በታደሰ መንፈስ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው፡፡

፪. ማንኛዉም አዲስ የተቀጠረ የፖሊስ አባል አስራ አንድ ወር አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የዓመት ዕረፍት ፍቃድ የማግኘት መብት የለዉም፡፡

፫. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በገንዘብ አይለወጥም፡፡

## ፴፭.የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ቀናት

፩. አንድ ዓመት ያገለገለ የፖሊስ አባል ሃያ የሥራ ቀናት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፤

፪. ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ የፖሊስ አባል ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው የአንድ ዓመት የዕረፍት ፈቃድ ከሠላሳ የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም፤

፫. ማንኛዉም የፖሊስ አባል ቀደም ሲል በሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት የሰጠው አገልግሎት ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አፈጻጸም የሚታሰብ ይሆናል፡፡

## ፴፮.የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ

፩. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በተቋሙ ዕቅድ ላይ ተመስርቶ የአባሉን ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጅ መርሀ ግብር መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ይሰጣል፡፡

፪. አንድ የፖሊስ አባል የዓመት ፍቃድ ሲሰጠዉ የአንድ ወር ደመወዙን በቅድሚያ ሊወስድ ይችላል፡፡

፫. የፖሊስ አባሉ የዓመት ፈቃድ ተከፋፍሎ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የቅርብ ኃላፊዉ ከተስማማ ተከፋፍሎ ሊወስድ ይችላል፡፡

4. Kunni quwira gufo (2) garinni diru fooliishsho fajjo adhe baajeettete diri goofara albaanni owaantesi umisi fajjonni uurrisinohu pooliisete miili, owaante uynokki yanna shallangeenna fajjote aana hee’reenna baantoonnisi damooza qolanno.

## 37. Diru Fooliishsho Fajjo Saysiisi’ra

1. Loosu gaddadisewo daafo poolisete miilira diru fooliishsho fajjo baajeette diri giddo aa hoongiro, muli sooressisi aane no baajeettete dirira saysasira dandaanno.
2. Poolisete miili ho’roonsi’rinokkita diru fooliishsho fajjo sayikki baajeettete diro uynannisi.
3. Kunni quwira gufo (2) aana ofoshshiinshoonnihu hee’rirono, uurrinshannihu aliidi (qaru) sooreessi diru fooliishsho fajjo murantewokki yanna geeshsha uynayki gede assa dandaanno.
4. Loosu gaddadisiro fajjote aana noohu poolisete miili fajjosi gudikkinni agure higawo gede assa dandiinanni.
5. Kunni quwira gufo (4) yitawo garinni koomishiinete hasattonni fajjosi gudikkinni agure loosoho higinohu poolisete miilira hodhishshunna barru hoshsho baantannisi.

## 38. Horoonsi’noonnikki Diru Fooliishsho Fajjo Daafira

1. Tenne wodhora quwa (37) gufo (1) yinoonniri hee’rirono, poolisete miili owaante uurrase kaiminni ho’roonsi’nokkiti diru fooliishsho fajjo woy tenne wodhora quwa (37) gufo (4) garinni saynsoonniti diru fooliishsho fajjo sayikki baajeettete diri giddo aa hoongisironna koomishiine ammanturo loosu barrubba shallange woxeho qolle soorrinasira dandiinanni.

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የዓመት ፍቃድ ወስዶ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት አገልግሎቱን በፍቃዱ ያቋረጠ የፖሊስ አባል አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ በፍቃድ ላይ እያለ የተከፈለዉን ደመወዝ ይመልሳል፡፡

## ፴፯.የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ስለማስተላለፍ

፩. በስራ አስገዳጅነት ለፖሊስ አባሉ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በበጀት ዓመቱ መስጠት ካልተቻለ የቅርብ ኃላፊው ለሚቀጥለው የበጀት ዓመት ሊያስተላልፈው ይችላል፡፡

፪. የፖሊስ አባሉ ያልተጠቀመበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በሶስተኛው በጀት ዓመት ይሰጠዋል፡ ፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የዓመት ፈቃድ ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬.በሥራው አስገዳጅነት በፈቃድ ላይ ያለ የፖሊስ አባል ፈቃዱን አቋርጦ እንዲመለስ ማድረግ ይቻላል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በኮሚሽኑ ፍላጎት ፈቃዱን አቋርጦ ወደ ስራ የተመለሰ የፖሊስ አባል የመጓጓዣና የውሎ አበል ይከፈለዋል፡፡

## ፴፰.ስላልተወሰደ የዓመት እረፍት ፈቃድ

፩. የዚህ ደንብ አንቀጽ (፴፯) ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የፖሊስ አባሉ አገልግሎት በማቋረጡ ምክንያት ያልተወሰደ የዓመት እረፍት ፍቃድ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ (፴፯) ንዑስ አንቀጽ (፬)መሰረት ተላልፎ የነበረ የዓመት እረፍት ፈቃድ በሦስተኛዉ የበጀት ዓመት ካልተሰጠው እና ኮሚሽኑ ካመነበት የስራ ቀኖቹ ታስበዉ በገንዘብ እንዲለወጥ ይደረጋል፡፡

2. Kunni quwira gufo (1) aana yinoonniti wole mangistete (mootimmate) loosu minira agure`ha'rewo poolisete miilira loosu aana dihossanno. Ikkirono ho'roonsi'noonnikkiti diru fooliishsho fajjo ha'rino mangistete looosi minira saysantannosi.

## 39. Ilate Fajo

1. Godowinni nooti poolisete miila:
   a) Godowase ledo amadaminohunni laisiisidhara xagisaanchu(hakime) hajajewo garinni damoozabaantannise fajjo uynannise.
   b) Ilate albaanni fooliishsho assidhawo gede xagisaanchu (hakimichu) hajajiro, damoozabaantannise fooliishsho uynannise.
2. Iltannoti yanna gambissuro ileemma barraati yite heddino barri albaanni 30 aantete no barrubba fooliishshote ilate fajjo uynannise, hattono ilate gedensaanni iltu barrinni hanafe 120 aantete no fajjote barrubba damoozu ledo uynannise.
3. Konni quwi gufo (2) garinni poolisete miilara uynoonniseti ilate albiidi fajjo gooffara albaanni ilturo, ho'roonsidhukkinni gattino barrubba iltu gedensaanni ho'roonsidhanno gede assinanni.
4. Adhitinoti ilate albiidi fajjo iltukkinni gooffuro, iltanno barri geeshsha noota loosu barrubba baajeette diri giddo noose diru fooliishsho fajjonni woy baajeettete diri giddo diru fooliishsho fajjo noosekkita ikkituro aane no baajeettete diritenni baajeettete diri fooliishshote fajjo adha dandiitanno.
5. Konni quwira gufo (2) aana ofoshshiinshoonnita ilate fajjo guddu gedensaanni dhiwanturonna fajjote barri ledamasera hasiisawoha ikkasi xagisaanchunni(hakimetenni) buuxamiro, tenne wodhora quwa (40) aana ofoshshiinshoonni garinni xissotenni fajjo adha dandiitanno.

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ለሄደ የፖሊስ አባል ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ሆኖም ያልተወሰደዉ የዓመት እረፍት ፈቃድ ወደ ሄደበት የመንግስት መስሪያ ቤት ይተላለፍለታል፡፡

## ፴፱.የወሊድ ፈቃድ

፩. ነፍሰጡር የሆነች የፖሊስ አባል፡-
   ሀ. ከእርግዝናዋ ጋር በተያያዘ ምርመራ ለማድረግ ሀኪም በሚያዘው መሠረት ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጣታል፡፡
   ለ. ከመውለዷ በፊት ዕረፍት እንድታደርግ ሐኪም ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት ዕረፍት ይሰጣታል፡፡

፪. መውለጃዋ ሲደርስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት ሰላሳ ተከታታይ ቀናት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ እንዲሁም ከወሊድ በኋላ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ መቶ ሀያ ተከታታይ ቀናት የወሊድ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጣታል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የፖሊስ አባሏ የተሰጣት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከማለቁ በፊት ከወለደች ያልተጠቀመችበትን ቀሪ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከወለደች በኋላ እንድትጠቀም ይደረጋል፡፡

፬. የወሰደችው ቅድመወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከ ምትወልድበት ቀን ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት የምትቆይበት ዕረፍት በበጀት ዓመቱ ካላት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት ዓመቱ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሌላት እንደሆነ ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት የዕረፍት ፈቃዷን መውሰድ ትችላለች፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተወሰነውን የወሊድ ፈቃድ ከጨረሰች በኋላ ብትታመምና ተጨማሪ ፈቃድ የሚያስፈልጋት መሆኑ በሐኪም ከተረጋገጠ በዚህ ደንብ አንቀጽ (፵) በተደነገገው መሠረት በሕመም ፈቃድ መውሰድ ትችላለች፡፡

a

6. Poolisete miili minaamasi iltawo woyte galtesi amadate(soorate) damooza murrannikkiha onte loosu barri fajjo uynannisi.

## 40. Xissote Fajjo

1. Ayno poolisete miili xissote korkaatinni looso loosa dandiinokkiha ikkiro, xagisaanchu(hakimete) taje heedhuro xissote fajjo uynannisi.
2. Konni quwira gufo (1) garinni poolisete miilira uynanniti xissote fajjo lambe lambe woy babbaxxitewo yannara uynoyta ikkiturono, xisso iillitinohu umi barrinni kayse no tonaa-lamu agani yanna giddo sette agana woy shoolu diri giddo tonaa-lame agana sa”a dinosi.
3. Konni quwira gufo (2) garinni uynanniti xissote fajjo umi lee agannara wo’mu damoozi ledonna aantanno lame agannara bocu damoozi ledo ikkanno.
4. Konni quwi gufo (2) aana la’noonnihu yannate danni HIV/AIDS vayrese mundeensa giddo no poolisete miilla aana diassamanno.
5. Ayno poolisete miili xissamiro, wolqate aleenni ikkanno karkaati xaada hooda hoogisiro ikkinnina dandii geeshsha rahotenni xissamasi muli sooreessisira afisiisa(egesiisa) noosi.

## 41. Loosu Aana Iillitanno gawajjo Korkaatinni Uynanni Fajjo

1. Loosu korkaatinni gawajjo iillitinosi poolisete miili iillitinosi gawajjonni gate woy hure loosisira higawo geeshsha woy gawajjote korkaatinni sufise konni ka’ano loosa dandawokkita xaginatu(fayyimmate) tajenni buunxa geeshsha xissote fajjo wo’mu damoozisi ledo uynannisi.

፮. የፖሊስ አባሉ የትዳር ጓደኛው ስትወልድ ባለቤቱን ለመንከባከብ ደመወዝ የሚከፈልበት አምስት የሥራ ቀን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## ፵. የሕመም ፈቃድ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል በሕመም ምክንያት ሥራ መስራት ያልቻለ እደሆነ በሐኪም ማስረጃ ሲደገፍ የህመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለፖሊስ አባሉ የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወሰድም ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የአሥራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከስምንት ወር ወይም በአራት ዓመት ውስጥ ከአስራ ሁለት ወር መብለጥ የለበትም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)መሰረት የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር እና ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ከግማሽ ደመወዝ ጋር ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተዉ የጊዜ ገደብ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸዉ ዉስጥ ባለባቸዉ የፖሊስ አባላት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፭. ማንኛውም የፖሊስ አባል ሲታመም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለቅርብ ኃላፊዉ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፵፩. በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ስለሚሰጥ ፈቃድ

፩. በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የፖሊስ አባል ከጉዳቱ ድኖ ወደ ስራው እስኪመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታው መሥራት ያልቻለ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ እስኪረጋገጥ የሕመም ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

2. Gawajjote fajjo aana no poolisete miili:
   a) Xaginateho shiqate giwannoha ikkiro woy dunneessannoha ikkiro woy aye garinni afay hee’renni xagisaanchunni la’nannita(fayyimmate buuxo) gufisiro woy ikkadu korkaati nookkiha goshooshiro,
   b) Gawajjotenni gatanno yanna keeshshiishate hede xaginate garunni ha’rusiwokkiha ikkiro,
   c) Federaale woy Qoqqowu Poolise Koomishiine fushshitannoha xaginatunnita tittirshu wodho sairo, fajjote aana hee’re afi’ranno damoozi ittisamanno.
3. Kunni quwira gufo (2) garinni damoozu baatooshshi uurrate korkaata ikkitino coyibba gattanni(ba’anni) heedheenna baatooshshu wirro sufamanno (baatamanno); ikkirono ittishshu yannara baatammokki baatooshshe afi’ra didandaanno.
4. Kunni quwira ofoshshiinshoonniri doorantino poolisete qajeelaanorano loosu aana hossanno.

## 42. Hojji Hajora Uynanni Fajjo

1. Ayno poolisete miili galte adhawo woyte doogote hasiisannosiha ha’ratenna higate barrubba ledikkinni onte loosu barriha adhammete fajjo damoozu ledo uynannisi.
2. Aye poolisete miili galte, ila, ama/annu woy lame deerra badheeginse kiirrannihu maalu fiixi woy balluwu (adhamate) fiixi reysiha ikkiro, doogote ha’ratenna higate barrubba kiirrikkinni damooza murrannikkiha sasu aane no barriha shii’rote fajjo uynannisi.
3. Ayno poolisete miili uurrinshate loosi aana hee’re tirfe yannanni rosanno rosira rosanno rosu uurrinshanni shiqishanno taje garinni fonqolo adhanno yanna damoozasi murrannikki fajjo uynannisi.

፪. በጉዳት ፈቃድ ላይ ያለ የፖሊስ አባል፡-

   ሀ) ለህክምና ምርመራ ለመቅረብ እምቢተኛ ከሆነ ወይም ቸል ያለ እንደሆነ ወይም በማናቸዉም ሁኔታ ሆነ ብሎ ምርመራዉን ያደናቀፈ ወይም ያለበቂ ምክንያት ያጓተተ እንደሆነ፣

   ለ) ከጉዳት የሚድንበትን ጊዜ ለማዘግየት በማሰብ ህክምናዉን በተገቢዉ መንገድ ያልተከታተለ እንደሆነ፣ ወይም

   ሐ) በፌዴራል ወይም በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የሚወጣዉን የህክምና መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ በፈቃድ ላይ ሆኖ የሚያገኘዉ የደመወዝ ክፍያ ይታገዳል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሐ) መሰረት ለደመወዝ ክፍያ መታገድ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎች እንደተወገዱ ክፍያዉ እንደገና ይቀጥላል፣ሆኖም እገዳዉ ፀንቶ ለቆየበት ጊዜ ያልተከፈለዉን ክፍያ ማግኘት አይችልም፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ለምልምል የፖሊስ ሰልጣኝም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ፵፪. ለግል ጉዳይ የሚሰጥ ፈቃድ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ትዳር ሲመሰርት ለጉዞ የሚያስፈልገዉን የመሄጃና የመመለሻ ቀናትን ሳይጨምር አምስት የሥራ ቀናት የጋብቻ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

፪. ማንኛውም የፖሊስ አባል ትዳር ጓደኛ፣ ተወላጅ፣ ወላጅ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ የሞተበት እንደሆነ ለጉዞ የመሄጃና የመመለሻ ቀናት ሳይጨምር ደመወዝ ሚከፈልበት የሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፫. ማንኛዉም የፖሊስ አባል መደበኛ ስራዉ ላይ ሆኖ በትርፍ ጊዜዉ ለሚማረዉ ትምህርት ከትምህርት ተቋሙ በሚያቀርበዉ ማስረጃ መሰረት ፈተና የሚወስድበት ጊዜ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 43. Damoozu Ledo Uynanni Addi Fajjo

Ayno poolisete miili:

1. Yooote mininni woy wolootu biilloonye uynoonninsa bissanni woshshatto iillitusiro, woshshaminora hajo adhitinosi yanna; woy
2. Koomishiinete mixo garinni gobbate giddo woy gobbate gobbaanni uynanni roso ha'runsate, damoozisi muramikkinni fajjo uynannisi.

## 44. Damooziweelo Uynanni Addi Fajjo

Ayno poolisete miili ikkado korkaata shiqishironna loosu mini ho'ro gawajjawokkiha ikkiro, sooreessi fajjiro damoozu baantayikkita addi fajjo uynasira dandiinanni.Gumulshu tittirshu wodhonni gumulamanno.

## GAFA SETTE

## Xaginatunna Dagoomu Owaante Lainohunni

## 45. Xaginatu Owaante

1. Ayno poolisete miili, seeru galtesi woy lemiina mitto diro wo'minonsakki oososi woy manniha adhe lossi'rino beetti xaginatu owaante mulla afi'ranno.
2. Xuratunni woy boordetenni woy ayirrinyunni fushshinoonnihu(geegiissinoonnihu) poolisete miili, seeru galtesi, lemiina mitto diro wo'minonsakki oososi woy manniha adhe lossi'rino qaaqqi(beetti) xaginatu owaante mulla(baatooshshiweelo) afi'ranno.
3. Kunni quwira gufo (1) xawinsoonnihu hee'rirono, hunotenni loosunni shorraminohu woy umisi muronni agurrohu poolisete miili xaginatu owaante ho'raameessa di"ikkanno.
4. Poolisete miilihu 21 diro ale ikkinosi beetti, annu, ama, rodoonna roduu baatooshshunni xaginatu owaante afidhawo gede assinanni.

## ፵፫.ከደመወዝ ጋር ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

፩. ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ስልጣን ከተሰጣቸዉ አካላት መጥሪያ ሲደርሰዉ የተጠራበት ጉዳይ ለወሰደዉ ጊዜ፤

፪. በኮሚሽኑ ዕቅድ መሰረት በሀገር ዉስጥ ወይም በዉጪ ሀገር የሚሰጥ ትምህርት ለመከታተል ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## ፵፬.ያለደመወዝ ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛዉም የፖሊስ አባል በቂ ምክንያት ሲያቀርብና የመስሪያ ቤቱን ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን በኃላፊው ሲፈቀድለት ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ ሊሰጠዉ ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለህክምና እና ማህበራዊ አገልግሎቶች

## ፵፭.የህክምና አገልግሎት

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል፣ሕጋዊ ሚስት ወይም ባል፣ ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ነጻ የህክምና አግልግሎት ያገኛሉ፡፡

፪. በጡረታ ወይም በቦርድ ወይም በክብር የተሰናበተ የፖሊስ አባል፣ሕጋዊ ሚስት ወይም ባል፣ ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ነጻ የህክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም በጥፋት ከሥራ የተሰናበተ ወይም በራሱ ውሳኔ የለቀቀ የፖሊስ አባል የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

፬.የፖሊስ አባሉ ከ21 ዓመት በላይ የሆነ ልጅ፣ አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም በክፍያ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

5. Uurrinsha wolqate aleenniikkino xaginatira poolisete miili seeru galtesira, 21 diro wo’minonsakki oososira woy wolu manniha adhe lossi’no beettira Federaalete Poolise Riferaalete Hospitaalera rifere assineenna mulla(baaatooshshiweelo) xagisidhawo gede assinanni.
6. Koomishiine qarqaru teessaanora baatooshshuni xaginatu owante uytara dandiitanno. Gumulshu tittirshu wodhonni gumulamanno.
7. Ayno poolisete miili bisi gawajjo Federaalete Poolisete Riferaalete Hospitaalera xaginatu boorde murturo(gumulturo) haa’nanniha ikkanno.

## 46. Galtete Mininna Hodhishshu Shiqishsha

1. Polisete uurrinsha wolqa assitu geeshsha poolisete miilla hodhishshu owaante afidhawo gede assate wo’naaltanno.
2. Minu hoonginna dikkote waagi hello giddiwo quchummara gaamantanno polisete miillara uurrinsha la’annonsa bissa ledo hasaabbe miilla galtawo mine afidhawo gede assate wo’naaltanno.
3. Loosu akati korkaatinni kaampete heedhannoti polisete miilla galtanno kaampe, waayinna caabbichu owaante mula afidhanno.
4. Ayno poolisete miili aanno owaante uurrituro afi’ray keeshshewooti heeshshote mini, wayinna caabbichu owaante uurritannosi.
5. Kunni quwira gufo (3) xawinsoonnihu hee’rirono, poolisete miili owaante uurritinohu:
   a) Gaddadote aana kakkalamasinni woy gaddadote darga xaadinosirichi afaminokkiha ikkinoha ikkiro lamu diri geeshsha;
   b) Xuratu karkaatinni ikkiro mittu diri geeshsha, woy

፭. ተቋሙ ከአቅም በላይ ለሆነ ሕክምና ለፖሊስ አባሉ ሕጋዊ ሚስት ወይም ባል፣ ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ወይም የጉዲፈቻ ልጅ በፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል በሪፈር በነፃ እንዲታከሙ ያደርጋል፡፡

፮. በኮሚሽኑ ለአካባቢዉ ነዋሪዎች በክፍያ የሕክምና አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፯. ማንኛዉም የፖሊስ አባል የአካል ጉዳት በፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል ህክምና ቦርድ ሲወሰን ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## ፵፮.የመኖሪያ ቤትና የትራንስፖርት አቅርቦት

፩. የፖሊስ ተቋም አቅም በፈቀደ መጠን የፖሊስ አባላት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ጥረት ያደረጋል፡፡

፪.የቤት እጥረትና የዋጋ ንረት ባለባቸዉ ከተሞች ለሚመደቡ የፖሊስ አባላት ተቋሙ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመነጋገር አባላት የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፡፡

፫. በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በካምፕ የሚኖሩ የፖሊስ አባላት መኖሪያ ካምፕ፣ የውኃና የመብራት አገልግሎት በነጻ ያገኛሉ፡፡

፬. የማንኛዉም የፖሊስ አባል አገልግሎት ሲቋረጥ የመኖሪያ ቤት፣የዉሃና የመብራት አገልግሎቶች ይቋረጣሉ፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተገለፀዉ ቢኖርም የፖሊስ አባሉ አገልግሎት የተቋረጠዉ፡-
   ሀ) በግዳጅ ላይ በመሰዋቱ ወይም በግዳጅ ቦታ የደረሰበት ሁኔታ ያልታወቀ ከሆነ እስከ ሁለት ዓመት፣
   ለ) በጡረታ ምክንያት ከሆነ እስከ አንድ ዓመት፣ ወይም

c) Aye wolu korkaatinni ikkiro mittu agani geeshsha poolisete miilirawoy maatesira tenne owaante afi’rate qoosso agarantannonsa.

## 47. Madaarshu Adawo(amanyooti) Owaante

1) Ayno poolisete miili loosunni daggino gawajjonni reynoha ikkiro, madaarsha gumulsiisate hajora hossanno fulo uurrinsha baattanno. Hattono madarshu adawo suusisi deerrinni poolisete madaarshu amanyootinni gumulamanno.
2) Kunni quwira gufo (1) aana noohu agarammo gedeenni hee’reenna, jawa suusa afi’nohu polisete miili reyro madaarshu poolisete madaarshu adawonni (manyootinni) gumulamanno.
3) Uurrinsha reyosi gara, xagisaanchu woy fayyimmate ogeessi muro(gumulo), madaarshu base, barranna malaate baala giddose amaddinota guuta odeesso(rippoorte) la’anno loosu kifilera yannatenni soya noose.
4) Qajeelshu aana hee’re reyno qajeelaanchira tittirshu gari Kolleejete wodho garinni gumulamanno. Madaarshu adawo lainohunni tittirshu gumulshshi tittirshu wodho(mammari) garinni gumulamanno.

## GAFA HONSE
## Poolisete Miilla Amanyootenna Wolqa Ho’roosi’ra Lainohunni

## 48. Amanyootu Jirte

Aye poolisete miili:

1. Uynoonnisi biilloonyinna sooreessimma garinni:

a) Dagate dagoomunna mannu mereero sirchunni, koo-teenni, ammanotenni, afuunni, danunni, poletiku laooshshinni, jirotenni, ilamatenni woy wolu aye korkaatinnino mallaandenna badooshshe assikkinni seeru qoossonsa ayirrisatenna ayirrisiisate;

ሐ) በማንኛዉም ሌላ ምክንያት ከሆነ እስከ አንድ ወር የፖሊስ አባሉ ወይም ቤተሰቡ እነዚህን አገልግሎቶች የማግኘት መብት ይጠበቅላቸዋል፡፡

## ፵፯.የቀብር ሥነ-ስርዓት አገልግሎት

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ከሥራ በመጣ ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለቀብር ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚውል ወጪ በተቋሙ ይሸፈናል፣እንዲሁም የቀብር ስነ ስርዓቱ እንደ ማዕረግ ደረጃዉ በፖሊሳዊ የክብር የቀብር ስነ ስርዓት ይፈፀማል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዲንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ማዕረግ ያለዉ የፖሊስ አባል ከሞተ ቀብሩ በፖሊሳዊ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ይፈፀማል፡፡

፫. ተቋሙ የሚችን የአሟሟት ሁኔታ፣የሐኪም ወይም የጤና ሙያተኛ ውሳኔ፣ የቀብር ቦታ ቀንና ምልክቱን ያካተተ የተሟላ ሪፖርት ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በወቅቱ መላክ አለበት፡፡

፬. በስልጠና ላይ እያለ ህይወቱ ያለፈ ሰልጣኝ ዝርዝር ሁኔታ በኮሌጁ አሰራር ደንብ መሰረት ይፈፀማል፡፡ የቀብር ሥነ-ሥርዓትን በተመለከተ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## የፖሊስ አባላት ሥነ-ምግባርና የኃይል አጠቃቀም

## ፵፰. የሥነ-ምግባር መርሆዎች

ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

፩. በተሰጠዉ ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት፡-

ሀ) በህዝቦች መካከል በዘር፣በፆታ፣በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በቀለም፣በፖለቲካዊ አመለካከት፣በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ማንኛዉም ምክንያት አድልዎ ሳያደርግ ሕጋዊ መብታቸውን የማክበር እና የማስከበር፣

b) Bayriidi Seera, Itophiyu adhinota kalqete mannimmate qoosso konvenshiinootanna woloota seerubba ayirrisatenna ayirrisiisate;

c) Aye dani jaddote assooshshe ga’mire gargaratenna umisino jaddo loosatenni xeerti’ra noosi.

2. Looso wodanchatenni, shaqqillunni, cincatenninna lowo qorophonni wonshate;

3. Dancha amanyoote xeissanno qarqarrara ganye hosa hoogate, umisinna uurrinshate ayirrinye agarate;

4. Loosu sa”aate ayirrisatenni wolootaho lawishsha ikkate;

5. Seeru doogonni fultino seerubba agarantino gedeenni heedheenna, gobbatenna mannu (dagate) keeraanchimma la’anno mashalaqqe maaxooshshunni agarate;

6. Biilloonyu noosi sooreessi garunni hajanjoha agurranna woy loosu akati xaadisawosi daafo hajo afa hasiissawosi mancho agurranna, poolisennita loosu millimillo, loosoho fulansa, qodhonsanna wole labbanno tajubba(mashalaqe) la’annosikki manchira xawisa hoogate;

7. Loosu ledo amadamewo korkaatinni uyno woy aanno owaantera baraarsha, woy wole ho’ro suwashsho woy suwashshiweelo doogonni hajamaanchu woy wolu aye bisiwiinni adha hoogate;

8. Go’le loosa hoogate woy umisino woleho golo ikke shiqa hoogate;

9. Hasiissawosikki ho’ro afi’rate woy afisiisate biilloonyesinna ayirrinyesi uduunnicho asse ho’roonsi’ra hooga;

10. Umisi woy fiixisi woy baxillaanchisi ho’ro ledo amadantinonna loosu sooreessinatisi ledo kipho kalaqqannosi hajo xaaddusiro, sooreessisira borrotenni afisiisanna ho’rote kiphama hoolate sooreessisi aannosi hajajonni loososi gumulate;

ለ) ህገ-መንግቱን፣ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ኮንቬንሽኖች እና ሌሎች ህጎችን የማክበር እና የማስከበር፣

ሐ) ማንኛውንም ዓይነት የወንጀል ድርጊት በጽናት የመከላከል እና ራሱም ከወንጀል ድርጊት መራቅ አለበት፡፡

፪. ስራዉን በማስተዋል፣በትህትና፣በታጋሽነት እና በከፍተኛ ጥንቃቄ የማከናወን፣

፫. መልካም ስነ ምግባርን የሚያጓድሉ አካባቢዎች አለማዘወተር፣የራሱን እና የተቋሙን ክብር የመጠበቅ፣

፬. የሥራ ሰዓት በማክበር ለሌሎች አርአያ የመሆን፡፡

፭. አግባብነት ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገርንና የሕዝብን ደህንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን ምስጢርነት የመጠበቅ፡፡

፮. ሥልጣን ባለው ኃላፊ በአግባቡ ከታዘዘ ወይም ከስራዉ ባህሪ አንፃር ጉዳዩን እንዲያውቀው የሚገባው ሰው ካልሆነ በስተቀር የፖሊስን የሥራ እንቅስቃሴ፣ ስምሪት፣ትጥቅና ተመሳሳይ መረጃዎችን ለማይመለከተዉ ሰዉ አለመግለጽ፡፡

፯. ከሥራው ጋር በተያዘ ምክንያት ለሰጠው ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት ስጦታ፣ ወይም ሌላ ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከባለጉዳይ ወይም ከሌላ ማንኛውም አካል ላይ አለመቀበል፡፡

፰. በአማላጅ አለመሥራት ወይም ራሱም በአማላጅነት አለመቅረብ፡፡

፱. የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ሥልጣኑንና ክብሩን መሳሪያ በማድረግ አለመጠቀም፡፡

፲. ከራሱ ወይም ከዘመዱ ወይም ከወዳጁ ጥቅም ጋር የተያያዘና ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር ግጭት የሚፈጥርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ለኃላፊው በጽሁፍ ማሳወቅ እና የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ ከኃላፊዉ በሚሰጠዉ መመሪያ ስራዉን የማከናወን፡፡

11. Kunni quwira gufo (10) ofoshshiinshoonni gari xaadiro, hajo xawinsoonnisi sooreessi ho’rote kiphama hoolate dadiissiisanno garinni loosu gumulamanno gede assate;
12. Gaamammoha uurrishate looso egennosinna dandoosi wo’munni wo’ma ho’roonsi’re gumulate;
13. Jaddote seeri fulinohu agaramino gedeenni hee’reennanni, sooreessisi aannosita ayetano seeru garinni aannosi hajajo wonshate;
14. Mimmitunniwa ayirrisamate;
15. La’annosihu aliidi sooreessi fajjikkinni aye dani fushsho gamba assa hoogate.

## 49. Wolqa Ho’roonsi’nay Gara Lainohunni

1. Aye poolisete miili sooreessinatesi fulanno yannara faajjetenni di”ikkanno yaannosi (hoolannosi) bisi xaadisironna woloota doorshubba hoogiro taaltanno wolqa ho’rosi’rara dandaanno.
2. Aye poolisete miili kunni quwira gufo (1) garinni bagado (olu uduunnicho) ho’roonsira dandaannohu:
   a) Umosi woy wole mancho rewotenni woy bisu aana lowo gowajjo iillishshawo assooshshinni gargarate;
   b) Amadama giwe xooqay nooha buutaamo jaddote huluullamamaancho seeru aliidimma woroonni hosiisate woy usuru mininni luxuphe xooqay no huluullamamaacho woy yoote gumulo uynoonnihu luxuphe xooqannoha uurrisate olu uduunnichi gobbaanni adhinayri wolootu qaafo ikkado ikkitawokkiha ikkiro callaati.
3. Kunni quwira gufo (2) garinni olu uduunnicho ho’roonsi’rewohu poolisete miili:
   a) Gawajjo iillitinosi manchi wiinamu xaginate afi’rawo gede assa noosi.
   b) Kalaqantino hajora la’annosihu aliidi sooreessira dargankonni odeessa (rippoorte assa)noosi.

፲፩.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) የተደነገገው ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩ የተገለፀለት ኃላፊ የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ በሚያስችል መልክ ሥራው እንዲከናወን የማድረግ፡፡

፲፪. የተመደበበትን መደበኛ ሥራ ዕውቀትና ችሎታውን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም የመፈጸም፡፡

፲፫. በወንጀል ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከኃላፊ የሚሰጠውን ማንኛውንም ሕጋዊ ትዕዛዝ የመፈጸም፡፡

፲፬. እርስ በእርስ የመከባበር፡፡

፲፭. የሚመለከተዉ የበላይ ኃላፊ ሳይፈቀድ ማንኛዉንም ዓይነት መዋጮ ያለማሰባሰብ፣

## ፵፱. የኃይል አጠቃቀም

፩. ማንኛዉም የፖሊስ አባል ኃላፊነቱን በሚወጣበት ጊዜ ግልጽ ተቃዉሞ ካጋጠመዉና ሌሎች አማራጮች ሲያጣ ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፡፡

፪. ማንኛዉም የፖሊስ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የጦር መሳሪያ ሊጠቀም የሚችለዉ፡-

   ሀ) በራሱ ወይም የሌላ ሰው ሞት ወይም ከፍተኛ የአካል ጉዳት ከሚያደርስ ጥቃት ለመከላከል፤

   ለ) በማምለጥ ላይ ያለ አደገኛ የወንጀል ተጠርጣሪ በህግ ቁጥጥር ስር ለማዋል ወይም ከእስር በማምለጥ ላይ ያለን ተጠርጣሪ ወይም ፍርደኛ ለማስቆም ከጦር መሳሪያ ዉጪ ያሉ ሌሎች እርምጃዎች በቂ ሆነዉ ሳይገኙ ሲቀሩ ብቻ ነዉ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የጦር መሳሪያ የተጠቀመ የፖሊስ አባል፡-

   ሀ) ጉዳት የደረሰበት ሰዉ አስቸኳይ የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ ማድረግ፣

ለ) ስለተፈጠረዉ ሁኔታ ለሚመለከተዉየበላይ ኃላፊ ወዲያዉኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## GAFA TONNE

## Babbaxxitewo Gaddado

### 50. Qara Gaddado

Aye poolisete miili Bayriidi Seera, Mangistete poolisee, koomishiinete lallawa, wodhonna tittirshu wodho afate, afisiisate, ayirrisate, ayirrisiisate, wonshatenna wonshishiishate gaddado noosi.

### 51. Uduunnu Amadooshshenna Ho'roonsi'ra Lainohunni

1. Ayno poolisete miili uduunnu amadooshshinna ho'roonsira aana mangistete fushshitinohu seeru agarammo gedeenni hee'reenna, uynoonnisiha mangistete jironna uduunne garunni agarate, dadda'lenna garunni amade ho'roonsi'ratenna gaammoonnisi alaamira calla hosiisate gaddado noosi.
2. Kunni quwira gufo (1) ofoshshiinshoonnihu agarammo gedeenni hee'reenna, deerra deerraho no sooreeyye uduunnu amadooshshinna agarooshshi gara ha'runsanna qorqorate gaddado noonsa.

### 52. Asalunni Xa'mamate Gaddado

1. Aye poolisete miili looso ha'risate uynoonnisi jironna uduunne garunni amadate gaddado noosi.
2. Kunni quwira gufo (1) ofoshshiinshoonnihu agarammo gedeenni hee'reenna, aye poolisichino uynoonnisi jironna uduunni aana iillishanno hunora woy gawajjora xa'mama dandaannohu huno woy gawajjo iillitinohu afenna hede woy dunneessatenni assasinni ikkirooti.

### 53. Wole Looso Loosa Lainohunni

1. Aye poolisete miili uurrinshte aanno owaante xeisannohu woy aye garinnino loosanno loosi adhamannosikkihu woy poolisimmate ayirrinyisinna loosisi ledo ha'rawo akati noosikkihu aye loosono wole loosa dinosi.

## ክፍል አስር

## ግዴታዎች

### ፶.መሰረታዊ ግዴታ

ማንኛውም የፖሊስ አባል ሕገ-መንግስቱን፣የመንግስት ፖሊሲዎችን፣የኮሚሽኑን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን የማወቅ፣የማሳወቅ፣የማክበር፣የማስከበር፣የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

### ፶፩.የንብረት አያያዝና አጠቃቀም

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ስለንብረት አያያዝና አጠቃቀም በመንግስት የወጡ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የተሰጠውን የመንግስት ሃብትና ንብረት በአግባቡ የመጠበቅ፣ በቁጠባና በእንክብካቤ የመጠቀም እና ለተመደበለት ዓላማ ብቻ የማዋል ግዴታ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው ያለ አመራር የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ሁኔታን የመከታተልና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

### ፶፪.በዕዳ የመጠየቅ ግዴታ

፩.ማንኛውም የፖሊስ አባል ለሥራው ማከናወኛ የተሰጡት ሃብትና ንብረት በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ፖሊስ የተሰጡት ሃብትና ንብረት ላይ በሚያደርሰው ጥፋት ወይም ጉዳት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጥፋቱ ወይም ጉዳቱ የደረሰው ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የፈፀመው እንደሆነ ነው፡፡ አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፶፫. ሌላ ሥራ ስለ መሥራት

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ለተቋሙ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም በማናቸውም አኳኋን ከሥራዉ ጋር የሚቃረን ወይም ከፖሊስነት ክብሩና ተግባሩ ጋር የማይጣጣም ማንኛውንም ሌላ ሥራ መሥራት የለበትም፡፡

2. Kunni quwira gufo (1) ofoshshiinshoonniti agarantewo gedeenni heedheenna aye miilino uurrinshate afisiise tirfe yannasinni wole looso loosa dandaanno.

## 54. Xaginateho Shiqa

1. Aye poolisete miili, HIV/AIDS laisiisi'ra agurranna, loosu ledo amadaminohunni ikkadu korkaatinni xaginate laisiisi'rawo (buuxo assiirawo) gede xa'minisiro shiqe laisiisi'rate gaddado noosi.
2. Kunni quwira gufo (1) garinni assinanni fayyinate laisiisi'rate(buuxooshshi) hasiissanno fulo uurrinsha dandiitanno.

## 55. Wodhote Uddano

1. Aye poolisete miili:
   a) Loosu aana no woyte xurtinokki wodhote uddano guuta uddi'ratenna wodhote uddano aana fajjinoonnisiha suusu malaate wodhate; woy
   b) Loosi gaamooshshisi korkaatinni wodhote uddano uddi'rawokkiha ikkiro, ise darga uddi'rara uynoonnisi uddano uddi'rate gaddado noosi.
2. Aye poolisete miili uynoonnisita wodhote uddanonna qodho wolu manchira argisa, hiranna ba'raasa didandaano.
3. Aye poolisete miili wodhote uddano uddi'rawo woyte, adhamate cuue(cuuicho) agurranna seesu uduunne (callenna woloota) wodha dinosi.

## 56. Garunni Amadooshshe Assinay Mannire Lainohunni

Aye poolisete miilira qaaqquulle woy meento woy geerranna bisu xe'ne no manna macciishshamawonsakki garinni garunni amadate (kaa'late) gaddado noosi.

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል ለተቋሙ አሳውቆ በትርፍ ጊዜው ሌላ ሥራ መስራት ይችላል፡፡

## ፶፬.ለሕክምና ምርመራ ስለመቅረብ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ከኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ በስተቀር ከስራው ጋር በተያያዘ በበቂ ምክንያት የሕክምና ምርመራ እንዲያደርግ በተቋሙ ሲጠየቅ ለምርመራ የመቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚደረገው የሕክምና ምርመራ የሚያስፈልገው ወጪ በተቋሙ ይሸፈናል፡፡

## ፶፭.ስለደንብ ልብስ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) በስራ ላይ በሚሆንበት ወቅት ንጽህናዉ የተጠበቀ የደንብ ልብሱን አሟልቶ የመልበስና በደንብ ልብሱ ላይ የተፈቀደለትን የማዕረግ ምልክት የማድረግ፣

ለ) በስራ ምድቡ ምክንያት የደንብ ልብስ የማይለብስ ከሆነ በምትኩ የተሰጠዉን ልብስ የመልበስ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛዉም የፖሊስ አባል የተሰጠውን የደንብ ልብስና ትጥቅ ለሌላ ሰው ማዋስ፣ መሸጥና በስጦታ መስጠት አይችልም፡፡

፫. ማንኛዉም የፖሊስ አባል የደንብ ልብሱን ሲለብስ ከጋብቻ ቀለበት ዉጪ ጌጣ ጌጥ ማድረግ የለበትም፡፡

## ፶፮.በእንክብካቤ መያዝ ስለሚገባቸዉ ሰዎች

ማንኛውም የፖሊስ አባል ህጻናትን ወይም ሴቶችን ወይም አረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞችን ስሜታቸው በማይነካ ሁኔታ በእንክብካቤ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

## 57. Xa’mama

Ayno poolisete miili afaa hee’re seera sae muranno muronni woy assino assooshshi korkaatinni iillishanno gawajjora xa’mamannoha kkanno.

## GAFA TONAA MITTO
## Disippiliinete (Amanyootu) Qaafonna Koffeenyu Shiqisha

## 58. Amanyootu Qorichi Alaami

Aye poolisete miilino loosino disippiliinete/amanyootu/ hunonni gaabbe albillicho rosicho adhe/eemarame/ ikkado poolisete miila ikkanno gede assa woy woyyaawa hooge leelliha ikkiro poolisete miilimmanni geegissammanno.

## 59. Shota Disippiliinete/Amanyootu/ Huno

Konni woroonni aane nohunote assooti giddo mitto loosinohu poolisete miili shota amanyootu hunonni xa’mamaancho ikkanno:

1. Wodhote uddanno suusu malaati ledo wonshe uddira hooga woy baaje woy badooshshu kiiro wodha hooga;
2. Suusunni roorannosihu poolisete miilira wottaadaru keere (salamta) aa hooga;
3. Worosiinni no miilla su’ma hunanna huuteessa;
4. Aliidi sooreessasi ayirrisa hooga, geeqa woy waajjishiisha;
5. Loosu baycho/basera/ goxe loosoho fula hooga;
6. Loosu saatera gamba ye hasaawa;
7. Wolu Poolisete miili amanyootu xe’ne loosinota afanni heere la’anno kifilera egensiisa hooga;
8. Umosi xurre keeraanchimma agadha hooga;
9. Wodhote uddano uddire hasiisannokki basera leella;
10. Dunneessatenni xiyyita dhoosa / tokkosa/;
11. Ikkadiweelu korkaatinni woy fajjiweelo lamala sa’inokki/roortinokki/ aante no barrubba loosunni gata;

## ፶፯.ተጠያቂነት

ማንኛዉም የፖሊስ አባል ሆን ብሎ ህግን በመጣስ በሚወስነዉ ዉሳኔ ወይም በሚፈጽመዉ ድርጊት ምክንያት ለሚያደርሰዉ ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አስራ አንድ
## የዲሲፕሊን እርምጃዎችና የቅሬታ አቀራረብ

## ፶፰.የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ

ማንኛውም የፖሊስ አባል በፈጸመው የዲሲፕሊን ጥፋት ተፀጽቶ ለወደፊቱ ታርሞ ብቁ የፖሊስ አባል እንዲሆን ማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ከፖሊስ አባልነት ማሰናበት ነው፡፡

## ፶፱.ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች

ከሚከተሉት ድርጊቶች አንዱን የፈፀመ የፖሊስ አባል በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡-

፩. የደንብ ልብስ ከነማዕረግ ምልክቱ አሟልቶ አለመልበስ ወይም ባጅ ወይም የመለያ ቁጥር አለማድረግ፣

፪. በማዕረግ ለሚበልጠዉ የፖሊስ አባል ሰላምታ አለመስጠት፤

፫. ከስሩ ያሉ አባላትን ማንቋሸሽና ማሸማቀቅ፤

፬. የበላይ ኃላፊዉን አለማክበር፣ ማንጓጠጥ ወይም ማስፈራራት፤

፭. በሥራ ቦታ ተገኝቶ ወደ ስራ አለመሰማራት፤

፮. በሥራ ሰዓት ተሰብስቦ ማውራት፤

፯. የፖሊስ አባል የዲሲፒሊን ጉድለት መፈፀሙን እያወቀ ለሚመለከተው ክፍል አለማሳወቅ፤

፰. የግል ንጽህናን ያለመጠበቅ፤

፱. የደንብ ልብስ ለብሶ አልባሌ ቦታ መገኘት፤

፲. በቸልተኝነት ጥይት ማባረቅ፣

፲፩. ያለበቂ ምክንያት ወይም ያለፈቃድ ከሰባት ለማይበልጡ ተከታታይ ቀናት ከስራ መቅረት፤

12. Loosoho barrisire ea woy fulote saate illitukkinni balaxe fula;
13. Hajamaano ikkado ikkinokki korkaatinni tootayyeessa;
14. Amanyootu qaafo adha woy kisse shiqishate sooreessimma fula hooga;
15. Konni quwira tittirroonniri ledo taalo ikkinoha wole amanyootu huno assa.

## 60. Kaajjado Amanyootu Huno

Aantanno assootubbanni mitte bunshe loosinohu poolisete miili kaajjado disippiliine/Amanyootu/ hunonni xa'mamaancho ikkanno:

1. Shota amanyootu hunonni lame aleenni hige marro loose qorichama;
2. Hajajo ayirrisa hoogatenni woy cee'matenni woy dunneessatenni woy loosu amanyoote sa''atenni loosu aana xe'ne leellisha;
3. Miillate loosu mittimma diigganno millimmora beeqqa;
4. Afaa heereenni looso loonsayikki gede assa(canco kalaqa) woy gufissannori ledo halama;
5. Aante aantete lamalu barri aleenni ikkadiweelu korkaatinni loosunni gata;
6. Loosu basera gibbo kalaqa woy ganama;
7. Rosantino dimba woy gawajjitanno mu'ro amalinni amadame looso huna/baddala/;
8. Loosu basera woy loosu base gobbaanni dagate mooraalera busha ikkino assoote assa;
9. Kaphunniha fayyimmate fajjo adha;
10. Riqiwo uynisikki uurrinshu ikkitore tuqu xaadooshshira xawishsha aa;
11. Loosu baycho/basera/ amma'note hasaawa/hajo/ ha'risa woy amma'no labbanno faarso woy seejjo(hasaawa) macciishshiisha woy misilla xalla;

፲፪. ወደ ስራ አርፍዶ መግባት ወይም የመዉጫ ሰዓት ሳይደርስ ቀድሞ መውጣት፤

፲፫. ባለጉዳይን ተገቢ ባልሆነ ምክንያት በቀጠሮ ማጉላላት፤

፲፬. የዲሲፒሊን እርምጃ የመዉሰድ ወይም ክስ የማቅረብ ኃላፊነትን አለመወጣት፣

፲፭. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለዉ ሌላ የዲሲፕሊን ጥፋት መፈፀም፡፡

## ፷. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች

ከሚከተሉት ድርጊቶች አንዱን የፈፀመ የፖሊስ አባል በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡-

፩. በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ከሁለት ጊዜ በላይ በመደጋገም ፈጽሞ መቀጣት፣

፪. ትዕዛዝ ባለማክበር ወይም በመለገም ወይም በቸልተኝነት ወይም የአሠራር ሥነ-ሥርዓትን በመጣስ በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤

፫. የአባላትን የስራ አንድነት በሚያናጋ እንቅስቃሴ መሳተፍ፤

፬. ሥራ እንዳይሰራ ሆን ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

፭. በተከታታይ ከሰባት ቀን በላይ ያለበቂ ምክንያት ከሥራ መቅረት፤

፮. በሥራ ቦታ ፀብ መጫር ወይም መደባደብ፤

፯. በልማዳዊ ስካር ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በመመረዝ ስራን መበደል፣

፰. በስራ ቦታ ወይም ከስራ ቦታ ውጪ ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፤

፱. የሀሰት የሐኪም ፈቃድ መዉሰድ፤

፲. ውክልና ሳይሰጠው ስለተቋሙ ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ መስጠት፤

፲፩. በሥራ ቦታ የሀይማኖት ስብከት ማካሄድ ወይም ሀይማኖት ነክ መዝሙሮችን ወይም ስብከቶችን ማሰማት ወይም ምስሎችን መለጠፍ፤

12. HIV/AIDS buuxooshshe agurranna wole loosu ledo xaadinoha fayyimmate buuxooshshe/mirmara/ assate sumuu yaa hooga;
13. Yoote mini hajajo ayirrisa hooga, yoo aate ha’rinsho gufisa woy agarooshshu basenni ba’’a;
14. Wodhote uddano, arma/sumuda/, ayimmate egenshiisha, baaje woy olu uduunnicho hasiisannikki manchira aa woy argisa;
15. Qodhinoha olu uduunnicho garimale amada woy huna;
16. Olu uduunnichinni loosu miillasi woy keeraano manna waajjishiisha woy reewa ;
17. Qoropho nookki amadooshshinni olu uduunnichi xiyyita dhoosatenni/tokkosatenni/ manchu bisi, heeshsho woy jajji aana gawajjo iillisha;
18. Seerimalu/higgaweelu/ loosi loosamanna la’’anni sa’’atenni ogimmate gaddado fula hooga;
19. Umosi danote reqecci assikkinni poolisaawete gaddado/giddaaje/ aana madirinoha poolisete miila kaa’la haasiissannosi woy kakkalaminoha poolisete miili reeshsha kaysate dandaanni here agurinohu;
20. Mannimmate qoosso kisatenni woy bayriidi seeri ledo xaadannokki assoote woy gumulo aa;
21. Gaddadote aaninni xooqa;
22. Loosu baycho woy loosu baychi gobbaanni koo-tee gawajjo iillisha;
23. Gubbo adha, gubbisa/muishsha aa/ woy aannosi gede xa’ma;
24. Aye baychono mooru, ammana xeisate woy awaawurshu assoote assa;
25. Uurrinshu jajji aana afanni hee’re woy de’netenni(balalletenni) gawajjo iillisha;

፲፪. ከኤች አይ ቪ /ኤድስ ምርመራ በስተቀር ከሥራው ጋር በተያያዘ የጤና ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ ያለመሆን፤

፲፫. የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለማክበር የፍርድ አሰጣጥ ሂደትን ማስተጓጎል ወይም ከጥበቃ ቦታ ላይ መጥፋት፤

፲፬. የደንብ ልብስ፣አርማ፣መታወቂያ፣ባጅ ወይም የጦር መሳሪያ ለማይገባው ሰው መስጠት ወይም ማዋስ፤

፲፭. የታጠቀውን የጦር መሳሪያ አለአግባብ መያዝ ወይም መጣል፤

፲፮. በጦር መሳሪያ የሥራ ባልደረቦቹን ወይም ኃላፊዎቹን ወይም ሰላማዊ ሰዎችን ማስፈራት ወይም መዛት፤

፲፯. ጥንቃቄ በጎደለዉ አያያዝ የጦር መሳሪያ ጥይት በማባረቅ በሰው አካል፣ሕይወት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፤

፲፰. የሕግ ጥሰትን እያየ በማለፍ የሙያ ግዴታን አለመወጣት፤

፲፱. ራሱን ለአደጋ ሳያጋልጥ በፖሊሳዊ ግዳጅ ላይ የቆሰለን የፖሊስ አባል መርዳት ወይም የተሰዋን የፖሊስ አባል አስከሬን ማንሳት ሲችል የተወ፤

፳. የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈፀም ወይም ሕገ-መንግስቱን የሚጻረር ድርጊት መፈጸም ወይም ውሳኔ መስጠት፤

፳፩. ከግዳጅ መሸሽ፤

፳፪. በሥራ ቦታ ወይም ከሥራ ቦታ ውጪ ፆታዊ ጥቃት መፈፀም፤

፳፫. ጉቦ መቀበል፣በመስጠት ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

፳፬. በማንኛዉም ቦታ የስርቆት፣የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም፤

፳፭. በተቋሙ ንብረት ላይ ሆንብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤

26. Biilloonye doogimale ho’roonsira;
27. Fojeessinannita ikkitino mashalaqqe fushsha;
28. Uurrinshunnita woy hajamaanote sanade maaxa, wole gaamora sayse aa, lawisiise qixxeessa, huna woy ho’rote gobbanni assa;
29. Qaxaramanno woyte woy qaxaramihu gedensaanni kaphu rosu woy loosu rosichi taje shiqisha;
30. Uurrinshu sanadda, cheekke, sumuda(maattama), titere, uurrinshu sumuda/arma/ amaddino borronninna suudinni woy ayimmate woraqattanni awaawurshu assoote assa woy assate wo’naala;
31. Aye poletiku paarte miila ikke leella woy poletiku paarte irkisa woy giwe millisa;
32. Konni quwira tittirroonniri ledo kuri labbannota wole amanyootu bunshe/huno/ loosa.

## 61.Shota Disippiliinete/amanyootu/ Qorcha

Ayno poolisete miili tenne wodho quwira 59 gufo (1) kayse (10) geeshsha worroonni huno giddonni mitte woy hattee lawanno assoote assiha ikkiro afuu qorophishiishsha uynannisi.

1. Ayno poolisete miili:
   a) Konni quwira gufo (1) garinni qorichami gedensaanni marro hinge xawinsoonni ittishshi giddo no hunonni mitto woy togooricho assinoha ikkiro;
   b) Tenne wodho quwa 59 gufo (11) kayse (14) geeshsha worroonni huno giddo mitte woy togoota labbanno huno umi yannara huniha/assiha/ ikkiro borrote qorophishiishsha uynannisi.

፳፮. በስልጣን አለአግባብ መጠቀም፤

፳፯. ምስጢር የሆኑ መረጃዎችን ማዉጣት፤

፳፰. የተቋሙን ወይም የባለጉዳይን ሰነድ መደበቅ፣ለሌላ ወገን አሳልፎ መስጠት፣ አስመስሎ ማዘጋጀት፣ማጥፋት ወይም ማበላሸት፤

፳፱. በሚቀጠርበት ወይም ከተቀጠረ በኋላ ሐሰተኛ የትምህርት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ ማቅረብ፤

፴. በተቋሙ ሰነዶች፣ቼኮች፣ማህተሞች፣ ቲተሮች፣የተቋሙን አርማ በያዙ ህትመቶችና ቅፆች ወይም በመታወቂያ ወረቀቶች የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም ወይም ለመፈጸም መሞከር፤

፴፩. የማንኛዉም ፖለቲካ ፖርቲ አባል ሆኖ መገኘት ወይም የፖለቲካ ፓርቲን መደገፍ ወይም በመቃወም መንቀሳቀስ፤

፴፪. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለዉ ሌላ የዲሲፕሊን ጥፋት መፈጸም፡፡

## ፷፩.የቀላል ዲሲኘሊን ቅጣት

፩. ማንኛዉም የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ በአንቀጽ (፶፱) ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፲) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪. ማንኛዉም የፖሊስ አባል፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከተቀጣ በኋላ በድጋሚ በተጠቀሰዉ ገደብ ዉስጥ ካሉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን የፈፀመ እንደሆነ፣
   ለ) በዚሁ ደንብ አንቀጽ (፶፱) ከንዑስ አንቀጽ (፲፩) እስከ (፲፬) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

## 62.Kaajjado Amanyootu Qoricha

1. Tenne wodhonni quwa 60gufo (1) kayse (12) geeshsha worroonni amanyootu xe'ne giddonni mitte woy wole tenne labbanno xe'ne/huno/ umi yannara hunihu poolisete miili disippiliinete kisse shiqqeennasi hunaancho ikke leelliha ikkiro mittu agani geeshshi damooza iillannoha(ikkannoha) woxu qorcha qorichamanno;
2. Ayno poolisete miili:
   a) Tenne wodho quwa (60) gufo (1) garinni qorichami gedensaanni marro hige yinoonni ittishshi giddo no hunonni mitte woy tenne labbannota huno huniha iikiro;
   b) Tenne wodho quwa (60) gufo (13) kayse (19) geeshsha ofoshshiinshoonni huno giddonni mitte woy wole mittu gari huno umi yannara huniha ikkiro, disippiliinete kisse shiqqeennasi hunaancho ikke leelliro lamu diri geeshsha ikkitanno yanna keeshshannoha mitto dirima suusunninna damoozunni woffi ye woy konisitaabilete dirimira nooha ikkiro suusu lophora keeshshanno yanna lamu diri geeshsha ikkitanno yanna keeshshanno gede assine qorichinshanni.
3. Ayno poolisete miili:
   a) Konni quwira gufo (2) garinni qorichami gedensaanni wirro(marro) higge xawinsoonni ittishshi yanna giddo no huno giddonni mitto woy wole mittu gari huno qole loosiha ikkiro;
   b) Tenne wodhora quwa (60) gufo (20) kayse (31) geeshsha worroonni huno giddonni mitto woy wole mittu gari huno umi yannara huniha ikkiro, amanyootu kisse shiqqeennasi hunaancho ikke leelliha ikkiro loosunni geegiissamanno gede assinanni.

## ፷፪.ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት

፩. በዚህ ደንብ በአንቀጽ (፷) ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፲፪) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ የፖሊስ አባል የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ አንድ ወር ደመወዝ የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪. ማንኛዉም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከተቀጣ በኋላ በድጋሚ በተጠቀሰዉ ገደብ ዉስጥ ካሉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን የፈፀመ እንደሆነ፣

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ (፷) ከንዑስ አንቀጽ (፲፫) እስከ (፲፱) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ፣ የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ ሁለት ዓመታት ለሚደርስ ጊዜ የሚቆይ አንድ ደረጃ ከማዕረግ እና ከደመወዝ ዝቅ እንዲል ወይም በኮንስታብል ደረጃ የሚገኝ ከሆነ የማዕረግ ዕድገት መቆያ ጊዜዉ እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ እንዲዘገኝ በማድረግ ይቀጣል፡፡

፫. ማንኛዉም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከተቀጣ በኋላ በድጋሚ በተጠቀሰዉ ገደብ ዉስጥ ካሉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን የፈፀመ እንደሆነ፣

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ (፷) ከንዑስ አንቀጽ (፳) እስከ (፴፩) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ፣የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከስራ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

4. Konni quwira gufo (2) garinni suusunninna damoozu diriminni woffi assineenna qorichaminohu poolisete miili qorichu yannasi gudiro qorichamara albaanni amadino suusanna damooza qolle uynannisi.

## 63. Loosu Aaninni ba''a woy Kadda''a

1. Ayno poolisete miili e'noha owaantete gaddado sheemaate gudikkinninna poolisimmate ayimma egenshiishshanna suusa, olu uduunne, wodhote uddano, sumudanna/arma/ woloota Jajjubba qolikkinni loosunni 21 barri aleenni saysiro tenne wodho quwa (64) gufo (5) xawinsoonni garinni gatino korkaata xawisannota ammansiissanno taje shiqisha hoogiro amanyootu kissenni uynannisi gumulo agarantino gede ikkiteenna loosu aaninni baino gede kiirameenna jaddotenna fitihabiherete seerinni xa'mamanno.
2. Konni quwira gufo(1) worroonnihu agaramino gedeenni ikke hereenna, loosu aaninni bainohu poolisete miili umisi fajjonni sheemaate uurrisinoha ikkasinni yoote mini widoonni usurame keeshshiro woy anga haaraanchunni/woowetenni/ fuliro damooza dibaantannisi.
3. Loosunni ba'asinni yoote mini qorichu gumulo uyro aye yannaranno loosoho higa didandaanno.

## 64. Amanyootu Qaafo Adhinanni Gara

1. Aye pooliseno aana amanyootu qoricha adhate albaanni loosino yinannita amanyootu xe'ne borrotenni afanno gede assine umosi gargadhanno kaayyo uyiinannisi;
2. Afuunni uyinanni qoropho kisse shiqishatenna gumulate qitse aana xawinse xa'mamaanchu miili malaatiseenna umisi mahidere/fayle/ giddo ofollanno gede assinanni.

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከማዕረግና ከደመወዝ ደረጃ ዝቅ እንዲል ተደርጎ የተቀጣ የፖሊስ አባል የቅጣት ጊዜዉን ሲያጠናቅቅ ከመቀጣቱ በፊት ይዞት የነበረዉ ማዕረግ እና ደመወዝ ተመልሶ ይሰጠዋል፡፡

## ፷፫.ከስራ ላይ ስለመጥፋት ወይም ከጂነት

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል የገባውን የአገልግሎት ግዴታ ውል ሳያጠናቅቅና የፖሊስነት መታወቂያና ማዕረግ፣ የጦር መሳሪያ፣ የደንብ ልብስ፣ አርማ እና ሌሎች ንብረቶችን ሳይመልስ ከሥራው ከ21 ቀን በላይ ካሳለፈ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፷፬ ንዑስ አንቀጽ ፭ በተገለፀዉ መሰረት የቀረበትን ምክንያት የሚገልጽ አሳማኝ ማስረጃ ካላቀረበ በዲሲፒሊን ክስ የሚሰጠዉ ዉሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሥራው ላይ እንደጠፋ ተቆጥሮ በወንጀል እና በፍትሐብሔር ሕግ ይጠየቃል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከስራዉ ላይ የጠፋ የፖሊስ አባል በራሱ ፈቃድ ውሉን ያቋረጠ በመሆኑ በፍርድ ቤት ታስሮ ቢቆይ ወይም በዋስ ቢለቀቅ ደመወዝ አይከፈለውም፡፡

፫.ከስራ ላይ በመጥፋቱ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ዉሳኔ ከሰጠ በማንኛዉም ጊዜ ወደ ስራዉ መመለስ አይችልም፡፡

## ፷፬.የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ

፩.በማንኛውም ፖሊስ ላይ የዲሲፕሊን ቅጣት ከመወሰዱ በፊት ፈጸመ የተባለውን የዲሲፕሊን ጉድለት በጽሁፍ እንዲያውቀው ተደርጎ ራሱን የመከላከል ዕድል ጁሰጠዋል፡፡

፪. በቃል የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ በክስ ማቅረቢያና መወሰኛ ቅጽ ላይ ተገልፆ በተጠያቂዉ አባል ተፈርሞ በግል ማህደሩ እንዲቀመጥ ይደረጋል፣

3. Kaajjadda Amanyootu huno la’atenna gumulo aate biilloonyi Qoqqowu, Zoonete, Hawaasi Qichumiranna Poolisete Kolleeje Mannu Jiro Loosu Massago Dayrekitoreetenna Divizhiinera ikkitanno. Tittirote jeefishshi wodhote tittirshi garinni gumulamanno.
4. Shota amanyootu hunora hunaancho ikke leellino poolisichira gumulo aannohu muli sooreessasi ikkanno.
5. 21 barri aleenni aantete ikkadiweelu ikkado ikinokki korkaati loosunni gatino poolisete miilira/poolisichira/ 5(onte)barra keeshshanno egenshiishshi 3(sase)hige aante aantete fulihu gedensaanni shiqa hoogiro looso agure baino gede kiiranni.
6. Suusunni woy damoozunni woffi assatenni woy geegissotenni/ha’risatenni/ kado shiqqurono shiqa hoogurono sanade qoqqowu poolisete komishiine kado macciishshate komitera shiqqe la’antanno.
7. Poolisete miillara loosunni geegiissamanno woy suusunni woy damoozunni woffi assate gumulo uyniro gumulo komishiineri komishiineretenni kaajja/guutisama/ noose; gumulono goofimarchunnita ikkitanno.
8. Kaajjado amanyootu kissera gumulote ha’rinsho aana seeru/higgete/ so’ro no yineenna koffeenyu shiqiro qoqqowu poolise koffeenya macciishshate komitenni la’amanno.
9. Amanyootu qoricha aye yoo mini gumulono agarrikkinni woy ha’runsinikkinni gumula dandiinanni.

## 65. Loosunni Ittisa

1. Mitto poolisete miila loosunni ittinse keeshshiisha dandiinannihu;
   a) Huluullammoonni hajo ledo xaadooshshe noonsa tajubba ho’rote gobbaanni assatenni, maaxatenni woy hunatenni qorto gufisanno, woy

፫. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን የማየትና ውሣኔ የመስጠት ስልጣን በክልል፣ በዞን፣ በሀዋሳ ከተማ፣ በፖሊስ ኮሌጅ የሰዉ ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬትና ዲቪዥን ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬. ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ውሳኔ የሚሰጠው ዲሲፕሊን □ኛተኛ ሆኖ በተገኘዉ ፖሊስ የቅርብ ኃላፊው ይሆናል፡፡

፭. ከ21 ቀን በላይ በተከታታይ ያለበቂ ምክንያት ከስራዉ ቀሪ የሆነ ፖሊስ ለ5 ቀን የሚቆይ ማስታወቂ□ ለ3 ተከታታይ ጊዜ ከወጣ በኋላ ካልቀረበ ስራዉን ጥሎ እንደጠፋ ይቆጠራል፡፡

፮. ከማዕረግ ወይም ከደመወዝ ዝቅ ማድረግ ወይም የስንብት ዉሳኔ ይግባኝ ቢቀርብም ባይቀርብም ሰነዱ ለክልሉፖሊስ ኮሚሽን ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴቀርቦ ይታያል፡፡

፯. የፖሊስ አባሉ ከሥራ የማሰናበት ወይም ከማዕረግ ወይም ከደመወዝ ዝቅ የማድረግ ውሳኔ ከተሰጠዉ ዉሳኔዉ በኮሚሽኑ ኮሚሽነር መጽደቅ ይኖርበታል፤ ውሳኔውም መጨረሻ ይሆናል፡፡

፰. በከባድ ዲሲፒሊን ክስ የዉሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ ቅሬታ ከቀረበ በክልሉ ፖሊስ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይታያል፡፡

፱. የዲሲፕሊን ቅጣት የማንኛውም ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል፡፡

## ፷፭.ከሥራ ስለማገድ

፩. አንድን የፖሊስ አባል ከሥራ አግዶ ማቆየት የሚቻለው፡-

ሀ) ከተጠረጠረበት ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም በማጥፋት ምርመራውን ያሰናክላል፣ ወይም

b) Uurrinshate loosinna Jajji aana lede wole hunonna gawajjo iillishanno yine hendiro;

c) Kassasamino huno kaajjilli garinni wolootu miilla woy loosaasine mooraale kissannoha woy owaante afidhanno dagara uurrinshate aana no ammana hunanno(xeisanno),woy

d) Loosino yinoonni huno loosunni hunsiisanno yine hendirooti.

2. Tenne quwara gufo(1) garinni mitto poolisete miila loosunninna damoozunni ittise keeshshiisha dandiinannihu lame agana roortannokki yanna geeshshaati.

3. Mittu poolisete miili loosunni ittisamino korkaatanna ittishshu keeshshanno yanna borrotenni xawinsannisi woy teessosi afa hoogatenni woy wolu korkaatinni ittishshu hajajo miilaho aa dandaa hoongiro gaamame loosannokifilewa egenshiishshu saleedi aana xallineenna tonne barra keeshshanno gede assinanni.

4. Poolisete miili kassasamino huno korkaatinni loosunni geegisamanno gede gumulloonniha agurranna (ikka hoogiro) ittishshu yannara baantisikkinni gatino damooza qallo nookkiha baantannisi.

## 66. Ittisate Biloonyi

Mittu poolisete miili jaddotenni huluullame woy amanyootu humo/xe'ne/ loose loosunninna damoozunni ittisameenna hajo buunxaantanno gede komishiinete komishiinerichi, Sidaamu Poolisete Kolleeje qaru dayrekiterichi, Zoonete woy Hawaasi Quchimi poolisete Biddishshi sooreessi hajajonni ittisame keeshshanno gede assinanni.

ለ) በተቋሙ ሥራ እና ንብረት ላይ ተጨማሪ በደልና ጉዳት ያደርሳል ተብሎ ሲገመት፣

ሐ) ከተከሰሰበት ጥፋት ክብደት አንጻር የሌሎች አባላትን ወይም ሠራተኞችን ሞራል የሚነካ ወይም ተገልጋዩ ሕብረተሰብ በተቋሙ ላይ ያለውን እምነት ያዛባል ወይም

መ) ተፈፀመ የተባለው ጥፋት ከሥራ ያስወግዳል ተብሎ ሲገመት ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አንድን የፖሊስ አባል ከስራና ደመወዝ አግዶ ማቆየት የሚቻለዉ ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል፡፡

፫. አንድ የፖሊስ አባል ከስራ ሲታገድ የታገደበት ምክንያትና ዕግዱ የሚቆይበት ጊዜ በጽሁፍ ይገለጽለታል፤ ወይም አድራሻ ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት የማገጃ ትዕዛዝ ለአባሉ መስጠት ካልተቻለ ትዕዛዙ ተመድቦ በሚሠራበት ክፍል ማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ተለጥፎ ለአስር ተከታታይ ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

፬. የፖሊስ አባሉ በተከሰሰበት ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግድ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

## ፷፮.የማገድ ሥልጣን

አንድ የፖሊስ አባል በወንጀል ተጠርጥሮ ወይም የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከስራና ከደመወዝ ታግዶ ጉዳዩ እንዲጣራ በኮሚሽን በኮሚሽነሩ፣በሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅ በዋና ዳይሬክተሩ፣በዞኑ ወይም በሀዋሳ ከተማ □ሊስ በመምሪ□□ ሀላ□ ታግዶ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

## 67. Kado Shiqisha

1. Shota amanyooti qorchi gumulo gumulloonnihu aye poolise miilino gumulote koffi yiiro, gumulo uynohu muli sooreessinni mitto dirima luphi yiino sooreessira 7/lamalu/ barri giddo kado shiqishira dandaanno. Kadote gumulora sumuu yaa hoogiro koffeenyasi dirimunni luphi yiinohura shiqishira dandaanno, konni deerrinni uynanni gumulo goofimarchunnita ikkitanno.
2. Komishiinete kassasaanchunnino ikko kassasamaanchunni shiqqannoti ayetino kaajjado amanyootu gumulo kado woy Zoonetenni, Hawaasi, Quchuminni, woy Sidaamu Poolisete Kolleejenni shiqqanno geegiissote woy suusunni woy damoozunni woffi assate gumulora kado komishiinete layinki komishiine jeneraalichi gamba assatenni babbaxxino loosu ha'rinshubbanninna kifillanni mitte meyati poolisete miila noowa 5(onte) miilla noorinni tantanatanno komitera kado shiqqara dandiitanno. Tittirshu jeefishshi wodhote tittirshinni/jirtetenni /gumulamanno.
3. Geegiissatenni woy suusunni woy damoozunni woffi assate gumulo aggurranna shiqqannore wloota wodho Zoonennihu, Hawaasi Quchumi poolisete hajajaanchi woy Sidaamu Poolisete Kolleejehu qaru dayrekiterichi gamba assatenni/gambisaanchimmanni/ babbaxxino loosu ha'rinshubbanninna mitte meyati poolisete miila noowa 5(onte) miilla noorinni tantanatanno komitera kado shiqqara dandiitanno. Gumulono goofimarchunnita ikkitanno.
4. Ayno kaajjado amanyootu kisse uynoonnihu poolisete miili gumulo iillitusihunni tonaa ontu barri giddo kado shiqishira dandaanno.

## 68. Yannate Danna/Gadawe/

1. Shota amanyootu qoricha qorichishiishshanno huno loosinohu huno afantu barrinni hanafe lewu agani geeshsha no yanna giddo qorichama hoogiro amanyootu kissenni dixa'mamanno.

## ፷፯.ይግባኝ ስለማቅረብ

፩. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ማንኛውም የፖሊስ አባል በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ውሳኔውን ከሰጠው የቅርብ ኃላፊ አንድ ደረጃ ከፍ ለሚለው ኃላፊ በ7 ቀን ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ በይግባኝ ዉሳኔዉ ካልተስማማ ቅሬታዉን በደረጃዉ ከፍ ላለዉ ለሚመለከተዉ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፣በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፪. በኮሚሽኑ በከሳሽም ሆነ በተከሳሽ የሚቀርብ ማንኛዉም የከባድ ዲሲፒሊን ዉሳኔ ጹ□ባኞችን ወይም ከዞን፣ ከሀዋሳ ከተማ፣ በሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅና ፖሊስ የሚቀርቡ የስንብት ወይም ከማዕረግ ወይም ከደመወዝ ዝቅ የማድረግ ዉሳኔ ይግባኞችን በኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ጄነራል ሰብሳቢነት ከተለያዩ የሥራ ሂደቶችና ክፍሎች አንዲት ሴት የፖሊስ አባል የምትገኝበት 5 አባላት ላሉት የሚቋቋም ኮሚቴ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. የስንብት ወይም ከማዕረግ ወይም ከደመወዝ ዝቅ የማድረግ ዉሳኔ በስተቀር የሚቀርቡ ሌሎች ይግባኞችን በዞን፣ በሀዋሳ ከተማ ፖሊስ አዛዥ ወይም በፖሊስ ኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር ሰብሳቢነት ከተለያዩ የሥራ ሂደቶች አንዲት ሴት የፖሊስ አባል የምትገኝበት 5 አባላት ላሉት የሚቋቋም ኮሚቴ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ውሣኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፬. ማንኛዉም የከባድ ዲሲፕሊን ክስ ዉሳኔ የተሰጠዉ የፖሊስ አባል ዉሳኔዉ በደረሰዉ በአስራ አምስት ቀን ዉስጥ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፷፰.ስለይርጋ ጊዜ

፩. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የፖሊስ አባል የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ካልተቀጣ በዲሲፕሊን ጥፋት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

2. Jaddono gattukkinni xa’misiissannota kaajjado dissippiliinete huno loosinohu poolisete miili togoo danijaddora kisse shiqishate jaddote seeri/higge/ aana worroonnihu kisse shiqishate yanna danni giddo amanyootu kisse shiqa hooggusiro amanyootunni dixa’mamanno.
3. Joddotennino xa’missiissannota kaajjado amanyootu huno loosinohu poolisete miili hunosi afantu barrinni hanafe mittu diri yanna giddo kassasama hoogiro amanyootunni dixa’mamanno.
4. Konni quwira worroonnihu yannate danni hee’rirono hunoloosasi afanteenna kisse hanafantuhu gedensaanni kisse buuxatenna gumulote guma xawisate ha’rate(ha’rinshote) adhino yanna dilendanni.
5. Konni quwira worroonnihu yannate danni no gede heerirono hajo la’annosihu poolisete sooreessi:
   a) Shota amanyootu huno/xe’ne/ loosantuta afihunni mittu agani yanna giddo qorichu qaafo adha hoogiro;
   b) Kaajjado amanyootu huno loosantinota afanni hee’re sasu aganni yanna giddo amanyootu kisse hanafantanno gede assa hoogiro; tenne wodho quwira (59) gufo (14) garinni dissippiliinetenni xa’mamaancho ikkanno.

## 69. Amanyootu Huno Rikkerde

Mittu poolisete miili amanyootunni qorichamihu gedensaanni qorichu rikkerdimmatenni amadama dandaannohu:

1. Shota dissippiliinete/amanyootu/ huno ikkituro qorichu gumulami barrinni hanafe mittu diri geeshsha;
2. Kaajjado amanyootu huno ikkituro qorichu gumulami barrinni hanafe lamu diri geeshsha ikkanno.

፪. በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት የፈፀመ የፖሊስ አባል ለእንደዚህ ዓይነት ወንጀሎች ክስ ለማቅረብ በወንጀል ህጉ በተደነገገዉ የክስ ማቅረቢያ ይርጋ ጊዜ ዉስጥ የዲሲፒሊን ክስ ካልቀረበበት በስተቀር በዲሲፒሊን ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፫. በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት የፈፀመ የፖሊስ አባል የጥፋቱ መፈፀም ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ካልተከሰሰ በዲሲፒሊን ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ቢኖርም ጥፋት መፈጸሙ ታውቆ ክስ ከተመሠረተ በኋላ ክሱን ለማጣራት እና የዉሳኔዉን ዉጤት ለመግለጽ ለጉዞ የሚወስደውን ጊዜ አይጨምርም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ የተደነገገዉ የይርጋ ጊዜ ቢኖርም የሚመለከተዉ የፖሊስ ኃላፊ፡-

ሀ) ቀላል የዲሲፒሊን ጥፋት መፈፀሙን ባወቀ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ የቅጣት እርምጃ ካልወሰደ፣

ለ) ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት መፈፀሙን እያወቀ በሦስት ወር ጊዜ ዉስጥ የዲሲፒሊን ክስ እንዲመሰረት ካላደረገ በዚህ ደንብ አንቀጽ (፶፱) ንዑስ አንቀጽ (፲፬) መሰረት በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፷፱.የዲሲፒሊን ጥፋት ሪከርድ

አንድ የፖሊስ አባል በዲሲፒሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊጠቀስበት የሚችለዉ፡-

፩. ቀላል የዲሲፒሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ፣

፪. ከባድ የዲሲፒሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ይሆናል፡፡

# GAFA TONAA-LAME

## Owaante Uurrisanna Seedisa Lainohunni

### 70. Meessi(Umisi) Fajjonni Looso Agura

1. Lamalu diri gaddaddote owaantesi gudinohu poolisete miili lamu aganiha borrote qorophishsha aatenni loososi umisi fajjonni agura dandaanno.
2. Kunni quwi gufo (1) aana ofoshshiinshoonnihu agarammo gedeenni hee’reenna Koomishiine babbaxxitino gumulo aa hooggu geeshsha agurate xa’mosi fajjo afidhewo gede assine kiirranni.
3. Lamu aganiha balaxe-qorophishsha uyikinni woy uynoti qorophishshu yanna gooffukkinni owaantesi agurinohu poolisete miili jaddote seerinni xa’mamannoha ikkanno.
4. Agurate xa’mosi shiqqinohu wiinamu lallawa lallanboy yannaranna seera agarsiisate addi soqqansho uynoonni yanna giddo ikkiro, wiinamu yanna lallawi ka”a geeshsha woy baxxitewo soqqanshosi gooffawo yanna geeshsha agurasi xa’mo dihaarantanno; ikkirono wiinamu yanna lallawi ka”ay hee’reenna woy addi soqqansho gooffay heedheenna lamu agani qorophishshisi yanna kiirama hanafanno.
5. Kunni quwiti gufo (3) aana ofoshshiinshoonniti agarantewo gedeenni heedheenna lamalu diri gaddadote owaante yannasi jeefisikkinni umisi fajjonni looso agurannohu poolisete miili owaante uynokki yanna shallangeenna qajeelshaho fultino fulo baatate gaddado noosi.
6. Qaxaramino loosi gobbaanni ikke roso woy qajeelsha afi’rinohu poolisete miili tenne wodho garinni owaante aate yanna gooffukkinni fulate xa’mo shiqishi’riro, owaante uynokki yanna shallange rosoho woy qajeelshaho fultino fulo sbaatanno gede assinanni.

# ክፍል አስራ ሁለት

## አገልግሎት ስለማቋረጥና ስለማራዘም

### ፸.በገዛ ፈቃድ ስራን መልቀቅ

፩. የሰባት ዓመት የግዴታ አገልግሎቱን የፈፀመ የፖሊስ አባል የሁለት ወር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሊለቅ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ የተለያዩ ዉሳኔ እስካልተሰጠ ድረስ የመልቀቂያ ጥያቄው እንደተፈቀደ ይቆጠራል፡፡

፫. የሁለት ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ወይም የሰጠው ማስጠንቀቂያ ጊዜ ሳያልቅ አገልግሎቱን ያቋረጠ የፖሊስ አባል በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬. የመልቀቂያ ጥያቄው የቀረበው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ወቅትና ሕግን ለማስከበር ልዩ ተልዕኮ በተሰጠበት ጊዜ ውስጥ ከሆነ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እስከሚነሳ ወይም ልዩ ተልዕኮው እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ የመልቀቂያ ጥያቄዉ ተቀባይነት አይኖረዉም፤ሆኖም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንደተነሳ ወይም ልዩ ተልዕኮዉ እንደተጠናቀቀ የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜዉ መቆጠር ይጀምራል፡፡

፭. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰባት ዓመት የግዴታ አገልግሎት ዘመኑን ሳያጠናቅቅ በራሱ ፍቃድ ስራ የሚለቅ የፖሊስ አባል አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ ለስልጠና የወጣዉን ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፮. ከመደበኛ ስራ ውጪ ሆኖ ትምህርት ወይም ሥልጠና ያገኘ የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ መሰረት ማገልገል ያለበትን ጊዜ ሳያጠናቅቅ መልቀቂያ የጠየቀ እንደሆነ አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ ለትምህርት ወይም ለስልጠናዉ የወጣውን ወጪ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

7. Qaxaramino loosi aana hee’re roso woy qajeelsha adhinohu poolisete miili tenne wodho garinni owaante aa noosi yanna gudikkinni looso agura xa’mi’noha ikkiro, owaante uynokki yanna shallange rosoho woy qajeelshaho fultino fulo taalo beenkeenna (boco) baatanno gede assinanni.

## 71. Xissote Woy Loosu Aana Iillitanno Gawajjo Koorkaatinni Owaante Uurrisa

1. Ayno poolisete miili xissotenni woy loosu aana iillanno korkaatinni uynoonnisiti fajjote yanna gooffu gedensaanni loosisi’ra higa dandaa hoogasi xagisaanote bordenni buuxanturo owaante uurritanno gede assinanni.
2. Kunni quwira gufo (1) ofoshshiinshoonnihu agarammo gedeenni hee’reenna, loosu aana iillitino gawajjo kiiso mangistete loosaasinera fultanno wodhonna seerubba garinni gumulamannoha ikkanno.
3. Kunni quwira gufo (1) garinni owaante uurritinohu poolisete miili loosu aana hose noori xuratu seerinna wodhuwa garinni qoossosi agarantannosi.
4. Loosu aana iillitanno gawajjo iillitinosihu filamaanchu poolisete qajeelaanchi gata dandaannokki gawajjo iillitewosita ikkasi xagisaanote boordenni buuxameenna ha’rinsannisi woyte, qajeelshu aana hee’reenna baantannasi nooti mittu diri qajeelshuyti barru hoshshonna hodhishshu fulo baantesi ha’rinsanni (fushshinanni).

## 72. Dandoote Anje Korkaatinni Loosunni Huna (Hoola)

1. Ayno poolisete miili gaamamino loosira noosi egennonna dandoo ho’roonsi’re loosate wolqasi fajjitusi geeshsha wo’naalanna (buxxuu’lanna) loosu gumulshisi keeno gumi lamu aantete no diriti mereerima bixxille woroonni ikkiro, loosunni hoolle ha’rinsanni.

፯. በመደበኛ ስራ ላይ ሆኖ ትምህርት ወይም ሥልጠና ያገኘ የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ መሰረት ማገልገል ያለበትን ጊዜ ሳያጠናቅቅ መልቀቂያ የጠየቀ እንደሆነ አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ ለትምህርት ወይም ለስልጠናዉ የወጣውን ወጪ ግማሽ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## ፸፩. በሕመም ወይም በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት አገልግሎትን ማቋረጥ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል በህመም ወይም በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት የተሰጠዉ የፍቃድ ጊዜ ካበቃ በኋላ ወደ ስራዉ መመለስ አለመቻሉ በሀኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ካሳ ለመንግስት ሰራተኞች በሚወጡ ድንጋጌዎች መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የፖሊስ አባል አግባብ ባላቸዉ የጡረታ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መብቱ ይጠበቅለታል፡፡

፬. በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት የደረሰበት ምልምል የፖሊስ ሰልጣኝ ሊድን የማይችል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጦ ሲሰናበት በስልጠና ላይ እያለ ይከፈለዉ የነበረዉ የአንድ ዓመት የስልጠና አበልና የመጓጓዣ ወጪ ተከፍሎት ይሰናበታል፡፡

## ፸፪. በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል በተመደበበት ሥራ ያለውን ዕውቀትና ችሎታ ተጠቅሞ ለመስራት የተቻለውን ጥረት እያደረገ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ በተከታታይ ለሁለት ዓመት ከአማካይ ነጥብ በታች ከሆነ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

2. Kunni quwira gafa (1) ofoshshiinshoonnihu hee'rirono, sai aantete no ontu aganira luphi yino loosu gumulshi guma afi're sainohu polisete miili loosu gumulshi keeno gumi sa'u yannara aantete no sasu diri gumi mereerima bixxille woroonni ikka hoogi geeshsha loosunni dishorramanno.
3. Kunni quwira gafa (1) woy (2) garinni mitto poolisete miila loosunni shorra dandiinannihu:
    a) Loosu madawe amadewotera hasiisanno qajeelsha uyneeti; woy
    b) Amadewohu loosu dirimi ledo taalo ikkinonna loosara dandaannowa wole loosu madawera qolatenni (saysatenni) mitto diro ajjannokki yanna loosawo gede assineenna dandoosi woyyeessi'ra dandiinokkiha ikkironna mittu agani qorophishsha balanxe uyne ikkanno.

## 73. Amanyootu Korkaatinni Loosunni Shorrama Lainohunni

Ayno poolisete miili tenne wodho giddo worroonni garinni kaajjado amanyootu hunonni kassasame loosunni shorramawo gedejeefote gumulo uynoonnisiha ikkiro owaante uurritanno.

## 74. Diru Korkaatinni Owaante Uurrisa

1. Aye poolisete miili owaante Qoqqowu Poolisete Koomishiine Uurrishshi Lallawi quwa (23) gufo (2) nna tenne wodho gufo (77) garinni seeda hoogiro, xurata fulate diri iillinowiinni jeefote barrinni hanaffe owaante uurritanno gede assinanni.
2. Poolisete miili xurata fulara lewu agani albaanni borrotenni afawo gede assinanni. goofimarchunniha lamu agani damoozisi ledo fajjo adhanno gede assinanni.

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ቀደም ባሉት ተከታታይ አምስት ዓመታት ከፍተኛ የሥራ አፈጻጸም ውጤት ሲያገኝ የነበረ የፖሊስ አባል የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ በተከታታይ ለሶስት ዓመታት ከአማካይ ነጥብ በታች ካልሆነ በስተቀር ከስራ አይሰናበትም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት አንድን የፖሊስ አባል ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው፡-

ሀ) ለያዘው የሥራ መደብ የሚያስፈልገውን ሥልጠና በመስጠት፣

ለ) ከያዘው የሥራ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ በሆነና ሊሰራው ወደሚችለው ሌላ የሥራ መደብ በማዛወር ከአንድ ዓመት ለማያንስ ጊዜ እንዲሰራ ተደርጎ ብቃቱን ማሻሻል ያልቻለ ከሆነና የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይሆናል፡

## ፸፫.በዲሲፕሊን ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

ማንኛውም የፖሊስ አባል አግባብ ባላቸዉ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት በከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት ተከሶ ከስራ እንዲሰናበት የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

## ፸፬. በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ

፩. የማንኛውም የፖሊስ አባል አገልግሎት የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ (፳፫) ንዑስ አንቀጽ (፪) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ (፸፯) መሰረት ካልተራዘመ በስተቀር የመጦሪያ ዕድሜው ከደረሰበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

፪. የፖሊስ አባሉ ጡረታ ከመውጣቱ ከስድስት ወር በፊት በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 75. Reyote Korkaatinni Owaante Uurrisa

1. Ayno poolisete miili rey barrinni hanafe owaante uurritanno.
2. Owaantesi rewote korkaatinni uurritinohu poolisete miili reyno aganihu wo'mu damoozisi borreessantewo galtesira woy galte hooggusiro seeru (higgete) ragiraasinera baantanni.
3. Xuratu seeri fulinohu agaramino gedeenni hee'reenna, reyootenni baxxinohu poolisete miilira galte heedhusiro woy hooggusiro seeru ragiraasinera baantanni.

   a) Reynohu gaddadote aana hee're kakalamasi karkaatinni ikkiro 12 agani damoozasi,

   b) Reynohu wolu korkaatinni ikkiro 6 agani damoozasi mitte hinge baantannisi gede assinanni.

## 76. Loosu Rosichi taje Aa Lainohunni

1. Ayno poolisete miili loosu aana hee're woy owaantesi uurritu gedensaanni loosu rosichi taje xa'mi'riro, loosanni sainoha loosu dana, owaantete diro, baantannasi saino damoozanna xa noo gara xawissannota loosu rosichi taje uynannisi. .
2. Kunni quwira gufo (1) aana ofoshshiinshshoonnihu hee'rirono loosunni ba''atenni woy kaade loosunni shorramino miili asalunni fayyo ikka hoogiro loosu rosichi taje diuynannisi.

## 77. Owaante Seedisa lainohunni

Qoqqowu Poolisete Koomishiine Uurrishshi lallawu kiiro 7/2012 quwa 23 gufo (2) garinni mittu poolisete miili owaantete yanna xuratu diri gedensaani seedisa dandiinannihu:

## ፸፭. በሞት ምክንያት የአገልግሎት መቋረጥ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል ከሞተበት ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ ይቋረጣል፤

፪. አገልግሎቱ በሞት ምክንያት የተቋረጠ የፖሊስ አባል የሞተበት ወር ሙሉ ደመወዝ ለተመዘገበ የትዳር ጓደኛ ወይም የትዳር ጓደኛ ከሌለዉ ለህጋዊ ወራሾቹ ይከፈላል፡፡

፫. አግባብ ባለዉ የጡረታ ህግ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሞት የተለየ የፖሊስ አባል የትዳር ጓደኛ ወይም የትዳር ጓደኛ ከሌለዉ ህጋዊ ወራሾቹ፡-

ሀ) የሞተዉ በግዳጅ ላይ እያለ በመሰዋቱ ምክንያት ከሆነ የ12 ወር ደመወዙ፣

ለ) የሞተዉ በሌላ ምክንያት ከሆነ የሥድስት ወር ደመወዙ በአንድ ጊዜ እንዲከፈላቸዉ ይደረጋል፡፡

## ፸፮. የሥራ ልምድ ማስረጃ ስለመስጠት

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል በስራ ላይ እያለ ወይም አገልግሎቱ ከተቋረጠ በኋላ የሥራ ልምድ ማስረጃ ሲጠይቅ ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓይነት፣የአገልግሎት ዘመን፣ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ እና አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ የሚገልጽ የሥራ ልምድ ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገዉ ቢኖርም ከስራ በመጥፋት ወይም በክደት ከስራ የተሰናበተ አባል ከዕዳ ነፃ ካልሆነ የስራ ልምድ ማሳረጃ አይሰጠዉም፡፡

## ፸፯. አገልግሎት ስለማራዘም

የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፯/፪፻፲፪ አንቀጽ (፳፫) ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የአንድን ፖሊስ አባል አገልግሎት ዘመን ከጡረታ ዕድሜ በኋላ ማራዘም የሚቻለዉ፡-

1. Miilu rosi, egenno, baxxitino ogimma, loosu rosichinna dandoo uurrinshate horo uytannota ikkituro;
2. Riqiwamaancho miila shotu garinni afi'ra dandiinannikkita buunxiro;
3. Miilu fayyinati xaginatu(fayyimmate) tajenni buuxamiro;
4. Miilu owaantesi sufisate sumuu yiironna
5. Owaantete seedisama Koomishiinete Koomishiineer Jeneraale fajjiturooti.
6. Lendanni coyibba(bixxillubba) tittirshu wodhonni gumulamantanno.

## GAFA TONAA-SASE

## Kassasammo Poolisete Miila Lainohunni

### 78. Loosu Ledo Amadantino Jaddonni Kassasammo poolisete Miila

Koomishiine mittu poolisete miili jaddotenni kassasaminohu loosu sooreessimmasi fulate yaanni assino assooshshi korkaatinni ikkasi ammanturo:

1. Yootenni goofimarchu gumulo uynanni geeshsha umisiha seeru ogeessa gaa'me mullunni ayyaayyamate(xawaqu) owaante afi'rawo gede assitanno;
2. Yekkeerama ha'rinshote aana heedheenna poolisete miili hasami yannara yoote minira shiqishate dandaanno gede anga haadhannosi;
3. Anga haa'rate qoosso ayirrisantusiro, loosu aana hee're damoozasi afi'ranni yekkeeramawo gede assitanno;
4. Yooote mini shilooti onte kiilo meetire ale xeerti'rawoha ikkiro, qaxarote barra shiqate dandaanno gede hodhishshu fulonna barru hoshsho baattannosi.

፩. የአባሉ ትምህርት፣ ዕውቀት፣ ልዩ ሙያ፣ የሥራ ልምድና ችሎታ ለተቋሙ ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፣

፪. ተተኪ አባል በቀላሉ ለማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

፫. የአባሉ ጤንነት በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

፬. አባሉ አገልግቱን ለመቀጠል ሲስማማ እና

፭. የአገልግሎቱ መራዘም በኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀነራል ሲፈቀድ ነው፡፡

፮. ተጨማሪ መስፈርት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አስራ ሦስት

## ስለተከሰሰ የፖሊስ አባል

### ፸፰.ከስራ ጋር በተገናኘ ወንጀል ስለተከሰሰ የፖሊስ አባል

ኮሚሽኑ አንድ የፖሊስ አባል በወንጀል የተከሰሰው የስራ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሲል በፈፀመው ድርጊት ምክንያት መሆኑን ሲያምን፡ ፡

፩. በፍርድ የመጨረሻ ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የራሱን የህግ ባለሙያ በመመደብ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፣

፪. ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ የፖሊስ አባሉ በተፈለገበት ጊዜ ፍ/ቤት ለማቅረብ እንዲችል ዋስ ይሆንለታል፡፡

፫. የዋስ መብቱ ከተከበረለት በሥራው ላይ ሆኖ ደመወዝ እያገኘ ክርክሩን እንዲያካሂድ ያደርጋል፡፡

፬. የፍርድ ቤቱ ችሎት ከአምስት ኪሎ ሜትር በላይ የሚርቅ ከሆነ በቀጠሮው ቀን ለመቅረብ እንዲችል የመጓጓዣ ወጪና የውሎ አበል ይከፍለዋል፡፡

5. Anga haa’rate qoossosi agarantusikkinni usuramiha ikkiro:
   a) Goofimrachu gumulo uynannisi geeshsha damoozasi uynann(baantannisi);
   b) Jaddonni fayyo fulasinni woy jaddote kisse ka’eenna usuruni tidhamiha ikkiro, loosisira higanno;
   c) Kassasamino jaddonni hunaancho ikkasi buuxanteenna onte diro sainokkiha usuru qoricha gumulloonnisiha guxxe fuli gedensaanni sasu agani yanna giddo loosoho higeemmo yee borrotenni xa’mirironna poolisete wodhonna loosu aana hosiisate garinni widoonni la’neenna koomishiine ammanturo loosoho higanno. Ikkirono usuru aana keehshsino yanna damooza dibaantannisi;
   d) Kassasamino jaddora hunaancho ikkasi buuxanteenna 5 diro sa’ino yanna usurunni qorichishamawo gede goofimarchu gumulo uynoonnisiha ikkiro, gumulo uyni barrinni hanafe poolisete miilimmanni xeinsanni, yoosi gude fulirono loosisira dihiganno.

## 79. Loosu Ledo Xaaddannokki jaddonni Kassasamino Poolisete Miila Lainohunni

Ayno poolisete miili jaddotenni kassasaminohu loosu sooreessimmasi fulate ledo xaadooshshu nookki garinni assino assooshshi korkaatinni ikkiro, tenne wodho garinni adhinasira dandiinanniti amanyootu gumulo agarantino gedeenni heedheenna:

1. Woowetenni fuliro loosu aana hee’renni damoozasi afi’ranni yekkeershasi ha’risanno gede assinanni(ha’risate dandaanno);
2. Poolise buuxo guddu gedensaanni waasete(woowete) qoossosi ayirritusikkinni gatteenna usurame hee’reenna yekkeerosha ha’insiro, damoozasi dibaantanni;
3. Fayyo ikke fulinohura woy jaddote kissesi kaynsoonnihura usurunni tidhamiro loosisira higanno.

፭. የዋስ መብቱ ሳይከበርለት ቀርቶ የሚታሰር ከሆነ፡-
   ሀ) የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ደመወዝ ይከፈለዋል፡፡
   ለ) በነፃ በመለቀቁ ወይም የወንጀል ክሱ በመነሳቱ ከእስር ከተፈታ ወደ ስራ ይመለሳል፡፡
   ሐ)በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ የእስራት ቅጣት ከተወሰነበት ቅጣቱን ከፈፀመ በኃላ በሦስት ወር ጊዜ ዉስጥ ወደ ስራ ልመለስ ብሎ በጽሁፍ ከጠየቀ እና ከፖሊስ ደንብና አሰራር አንጻር ታይቶ ኮሚሽኑ ካመነበት ወደ ስራዉ ይመለሳል፡፡ ሆኖም በእስር ላይ የቆየበት ጊዜ ደመወዝ አይከፈለዉም፡፡
   መ) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ከአምስት ዓመት በበለጠ እስራት እንዲቀጣ የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከፖሊስ ኃይል ይቀነሳል፣ፍርዱን ጨርሶ ቢወጣም ወደ ስራዉ አይመለስም፡፡

## ፸፱. ከስራው ጋር ባልተገናኘ ወንጀል ስለተከሰሰ የፖሊስ አባል

ማንኛውም የፖሊስ አባል በወንጀል የተከሰሰዉ የስራ ኃላፊነቱን ከመወጣት ጋር ግንኙነት በሌለው ሁኔታ በፈፀመዉ ድርጊት ምክንያት ሲሆን በዚህ ደንብ መሰረት ሊወሰድበት የሚችለዉ የዲሲፕሊን ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩. በዋስ ከተለቀቀ ሥራው ላይ ሆኖ ደመወዝ እያገኘ ክርክሩን እንዲያካሂድ ይደረጋል፣
፪. ፖሊስ ምርመራዉን ካጠናቀቀ በኋላ ዋስትና ሳይከበርለት ቀርቶ ታስሮ እያለ ክርክሩ የሚካሄድ ከሆነ ደመወዝ አይከፈለዉም፣
፫. በነፃ በመለቀቁ ወይም የወንጀል ክሱ በመነሳቱ ከእስር ከተፈታ ወደ ስራዉ ይመለሳል፣

**4.** Kassasamino jaddonni hunaancho ikkasi buuxanteenna mitto diro sainokki usuru qoricha gumulloonnisiwiinni qorichasi guxxe fuli gedensaanni loosisira higara yee mittu agani giddo borrotenni xa’miro, kassasamino jaddo seerahonna mooraalete gurcho (guficho) ikkitinokkitanna uurrinshate su’manna macca xursiissawokkiha ikkasi buunxiro loosisira higa dandaanno. Usuru aana keeshshino damooza kayinni dibaantannisi.

**5.** Kassasamino jaddonni hunaancho ikkasi buuxanteeenna mitto diro ale usurunni qorichishamara jeefote gumulo uynoonnisiha ikkiro, gumulo aamantusi barrinni hananfe poolisete miilimmanni xeinsannisi(kayinsannisi), yoo gude fulirono loosisira dihiganno.

## GAFA TONAA-SHOOLE

## Poolisete Miilla Taje

### 80. Allanyu(Annu-annu)Taje-amadaasincho (fayle)

1. Uurrinsha mittu mittunku miilita hasiissawo tajubba amaddannota allanyu(annu-annu) taje-amadaasincho biddi assatenna qorophotenni maareekke worate sooreessimma noose.
2. Poolisete miilita wo’ma taje amadinohu umisi taje-amadaasinchi (mahidere) miilu hee’ranno uurrinsha giddo hee’ranno assinanni. Hattono poolisete miili qaxarama, sheemaate, suusu lophonna mootoonsate tajubba koppe miilu Qoqqowu Poolisete Komishiine deerrinnino maareekkante amadantawo gedeassinanni.
3. Ayno poolisete miili umisi taje-amadaasinchi giddo afantanno tajubba la’’ate woy koppe adhate qoosso noosi.
4. Baalunku poolisete miili 7 dirita giddeetu owaante yannasi gude loosu rosichi taje uynasira xa’miro, afi’rate qoosso noosi.

፬. በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከአንድ ዓመት ያልበለጠ የእስራት ቅጣት ከተወሰነበት ቅጣቱን ፈጽሞ ከወጣ በኋላ ወደ ስራ ሊመለስ ብሎ በአንድ ወር ውስጥ በፅሑፍ ከጠየቀ የተከሰሰበት ወንጀል ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ያልሆነና የተቋሙን ስምና ዝና የማያጎድፍ ሆኖ ከተገኘ ወደ ስራዉ ሊመለስ ይችላል፡፡ በእስር የቆየበት ደመወዝ ግን አይከፈለዉም፡፡

፭. በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከአንድ ዓመት በበለጠ እስራት እንዲቀጣ የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከፖሊስ ኃይል ይቀነሳል፣ፍርዱን ጨርሶ ቢወጣም ወደ ስራዉ አይመለስም፡፡

## ክፍል አስራ አራት

## የፖሊስ አባላት መረጃ

### ፹. የግል ማህደር

፩. ተቋሙ ስለእያንዳንዱ አባል አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የሚይዝ የግል ማህደር ማደራጀትና በጥንቃቄ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. የፖሊስ አባሉን የተሟላ መረጃ የያዘ የግል ማህደር አባሉ በሚገኝበት ተቋም እንዲኖር ይደረጋል፡፡ እንደሁም የፖሊስ አባሉ ቅጥር፣ ዉል፣ የማዕረግ እድገትና የሹመት መረጃዎች ቅጂ በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ጭምር እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡

፫. ማንኛውም የፖሊስ አባል በግል ማህደሩ ውስጥ የሚገኙትን መረጃዎች የመመልከት ወይም ቅጅውን የመውሰድ መብት ይኖረዋል፡፡

፬. ማንኛዉም የፖሊስ አባል የ7 ዓመት የግዴታ አገልግሎት ጊዜዉን ጨርሶ የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጠዉ ከጠየቀ የማግኘት መብት አለዉ፡፡

5. La’annoha gashshootu loosaasincho agurranna uurrinsha baalantera Koomishiinerete woy 2[nki] Koomishiinere Jeneraale woy Sidaamu Poolise Kolleeje Dayrekterichi woy dayrektoreetete-dayrekterichi woy Zoonete, Hawaasi Quchuminna woradu sooreessi fajjikkinni aye poolisete miilita umisi taje-amadaasiincho la”a didandiinanni.
6. Poolisete miili afawo gede assinoonnikkita woy xawinsoonnikkita aye dani tajeno tajesi-amadaasinchi giddo wora didandiinanni.
7. Ayno poolisete miili:
    a) Galte adhawo woy galtesi tirawo woyte adhamate woy tiramate(tidhamate) taje yannatenni kifilesira shiqishe egensiisa noosi.
    b) Ooso ilawo woyte woy manniha(manni ila) lossi’rawo woyte yannantenni kifilesira afisiisa noosi.

## 81. Istaatistikete Tajubba

1. Koomishiine:
    a) Mannu jiro taje fayle biddi assite amaddanno.
    b) Mannu jiro taje adawo mittu garinni loosu aana hosiinsanni gede assitanno.
2. Uurrinsha miilla la’annota istaatistikete tajubba gamba assitanno; qineessitanno; tittirtanno; hasiisanno loosira ho’rote aana hosiisanno.
3. Uurrinsha qoqqowoho tantanantanno mannu wolqa tajubba sa”a(iilla) noonsare yannantenni soyate gaddadantanno.

## 82. Loosu Gumulshi Keeno, Alaamanna Gumulsha

### 1) Alaama

Loosu gumulshi keeno poolisete miillara:

፭. ከሚመለከተዉ የአስተዳደር ሠራተኛ በስተቀር በየተቋሙ በኮሚሽነር ወይም በምክትል ኮሚሽነር ወይም በሲዳማ ፖሊስ ኮሌጅ ዳይሬክተር ወይም በዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም በዞን፣በሀዋሳ ከተማ የፖሊስ ኃላፊ ሳይፈቀድ የማንኛውንም የፖሊስ አባል የግል ማህደር ማየት አይቻልም፡፡

፮. የፖሊስ አባሉ እንዲያውቀው ያልተደረገ ወይም ያልተገለፀለትን ማንኛውንም ዓይነት መረጃ በግል ማህደሩ ውስጥ ማስቀመጥ ክልክል ነው፡፡

፯. ማንኛዉም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) ጋብቻ ወይም ፍቺ ሲፈጽም የጋብቻዉን ወይም የፍቺዉን ማስረጃ በወቅቱ ለክፍሉ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፣

ለ) ልጅ ሲወልድ ወይም ጉዲፈቻ ሲያደርግ በወቅቱ ለክፍሉ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፹፩. ስታትስቲካዊ መረጃዎች

፩. ኮሚሽኑ፡-

ሀ) የሰው ሀብት መረጃ ቋት ያደራጃል፣

ለ) የሰው ሀብት መረጃ ሥርዓት በወጥነት እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

፪. ተቋሙ አባላትን የሚመለከቱ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ለአስፈላጊው ሥራ ጥቅም ላይ ያውላል፡፡

፫. ተቋሙ በክልል ለሚደራጀው የሰው ሀብት መረጃ መተላለፍ የሚኖርባቸዉን መረጃዎች በወቅቱ የመላክ ግዴታ አለበት፡፡

## ፹፪. የሥራ ክንዉን ግምገማ ወይም ምዘና ዓላማና አፈጻጸም

### ፩. ዓላማ

የስራ አፈፃፀም ግምገማ ወይም ምዘና የፖሊስ አባላት፡-

a) Loosonsa hasi’nanni bikkini, islanchimmanni, rankenninna fulonni wonshitanno gede dandiissiisate;

b) kaajjadonna laafa waatensa(midaadonsa) badatenni mixo kaima assinoha dhuka dhaaawate looso loosate dandiissiisate;

c) Albillicho loosu gumulshansa woyyeessitawo gede loosu kakkaooshshensa bowirsate;

d) Abbitinoo guma kaima assino jawaachishsha uynanninsa gede dandiissiisate;

e) Iillinoonni woy afantino taje aana kaima ikkitino gumulo aate dandiissiisate ikkanno.

## 2. Gumulsha

a) Loosu gumulshi(jeefishshi) keeno faajjetenninna loosu la”annonsarinna miilla noowa mittimma gumullanni.

b) Rosu aana no miilira rosannohu rosu mini soyaanno odeesso(rippoorte) keenote odeesso gede assine adhinanni.

# GAFA TONAA ONTE

# Poolisete Ba’raarsha

## 83. Alaama

Baraarshu alaami luphi yiino gumi daanno gede hattono haaruudda kalanqe afi’noonni gumma uurrinshate giddo bowirtanno gede, luphi yitino kaa’lo assitinorinna seeda yanna owaante uytinota poolisete miilla jawaachishatenni komishiinete soqqanshote guma buuxate ikkanno.

ሀ) ስራቸዉን በሚፈለገዉ መጠን፣ጥራት፣ ፍጥነትና ወጪ እንዲያከናዉኑ ለማስቻል፣

ለ) ጠንካራና ደካማ ጎናቸዉን በመለየት በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ስራ ለመስራት የማስቻል፣

ሐ) የወደ ፊት የስራ አፈፃፀማቸዉን እንዲያሻሽሉ የስራ ተነሳሽነታቸዉን የማጎልበት፣

መ) በዉጤት ላይ የተመሰረተ ማትጊያ እንዲሰጣቸዉ ለማስቻል፣

ሠ) በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ ዉሳኔ መስጠት ለማስቻል ይሆናል፡፡

## ፪. አፈፃፀም

ሀ) የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ወይም ምዘና በግልጽና ሥራው የሚመለከታቸው አካላት እና አባላት በተገኙበት በጋራ ይከናወናል፡፡

ለ) በትምህርት ላይ የሚገኝ አባል የሚማርበት ትምህርት ቤት የሚልከው ሪፖርት እንደ ግምገማ ወይም ምዘና ሪፖርት ይወሰዳል፡፡

# ክፍል አስራ አምስት

# የፖሊስ ሽልማቶች

## ፹፫. ዓላማ

የሽልማቱ ዓላማ የላቀ ውጤት እንዲመጣ እንዲሁም አዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራ በተቋሙ ውስጥ እንዲጎለብት፣ የጎላ አስተዋጽኦ ያበረከቱና ረዥም ጊዜ አገልግሎት የሰጡ የፖሊስ አባላትን በማበረታታት የኮሚሽኑን ተልዕኮ ስኬት ለማረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 84. Poolisete Baraarishi dana

1. Komishiine poolisete uytanno baraarshi:
   a) Worbimmate( የጀግንነት)meedaye umi dirima;
   b) Worbimmate meedaye layinki dirima;
   c) Worbimmate meedaye sayikki dirima;
   d) Luphi yiino loosi gumi meedaye ;
   **e)** Poolisete owaante meedaye umi dirima;
   f) Poolisete owaante meedaye layinki dirima;
   g) Poolisete owaante meedaye sayinki dirimanna;
   h) Poolisete owaante rivaaneeti.
2. Koonni quwira gufo (1) worroonni baraarshi dani, suudinna amado jirtetenni woy woodhote tittirshinni gumulamanno.

## 85. Worbimmate Meedaye Umi Dirimi

1. Worbimmate meedaye umi dirimiti duucuchawoyti/wo’mawoyti/ poolisaawete giddajera xa’mannohu aleenni addinta lowo geeshsha naaxxisiisanno worbimmate looso guutisino poolisete miilira, gaamora woy loosu kifilera uynanni baraarshaati.
2. Worbimmatenna meedaye umi dirimi baraarinoha/baraaraancho/ ikkino poolisete miili:
   a) Birra 20 kume mitte hinge bantanni baatooshshenna 25%xibbunni damoozu lexxo uynannisi, reyha/kakkalamiha/ ikkiro higgaawe ragiraanosira birra 25 kume baantanni,
   b) Sidaamu Daqoomu Qoqqowi Mootimma pirezidaatichinni malaatisaminoha tajete woraqata uynanni.
3. Worbimmate meedaye umi dirimita ba’raadhino gaamo woy loosu kifile birra 20 kumenna Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma pirezidaantichinni malaatisaminoha tajete woraqata uynanni. Baraadhino gaamo woy loosu kifile miila ikkinohura mittu mittunku poolisete miilira 25% xibbunni damoozu lexxo uynanni.

## ፹፬. የፖሊስ ሽልማት ዓይነቶች

፩. በኮሚሽኑ ለፖሊስ የሚሰጡ ሽልማቶች፡-
   ሀ) የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፣
   ለ) የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፣
   ሐ) የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፣
   መ) የላቀ ስራ ዉጤት ሜዳይ፣
   ሠ) የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፣
   ረ) የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፣
   ሰ) የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፣
   ሸ) የፖሊስ አገልግሎት ሪቫን ናቸዉ፡፡
፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሽልማቶች ቅርጽና ይዘት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፹፭. የጀግንነት መዳይ አንደኛ ደረጃ

፩. የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የዘወትር ፖሊሳዊ ግዳጅ ከሚጠይቀዉ በላይ እጅግ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈፀመ የፖሊስ አባል፣ቡድን ወይም የስራ ክፍል የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡
፪. የጀግንነትና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-
   ሀ) የብር 20 ሺህ የአንድ ጊዜ ክፍያና የ25% በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፣የተሰዋ እንደሆነ ለህጋዊ ወራሾቹ ብር 25 ሺህ ይከፈላል፣
   ለ) የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
፫. የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የስራ ክፍል ብር 20 ሺህ እና የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ የተሸላሚዉ ቡድን ወይም የስራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም 25% በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

## 86. Worbimmate meedaye Layinki Dirimita

1. Worbu meedaye layinki dirimiti wo'ma woyte Poolisaawete giddaaje/gaddado/ xa'mitannohu aleenni lowo geeshsha naadisiissanno worbimma jeefisino poolisete miilira, gaamora woy loosu kifilera uynanni ba'rarshaati.
2. Worbu meedaye layinki dirimi ba'raaraancho ikkinohu poolisete miili:
   a) Birra 15 kume mitte hinge baantanni baatooshshenna 20% xibbunni damoozu lexxo assinannisi, kakkalamiha/reyha/ ikkiro higgaawe ragiraanora birra 20 kume baantanni.
   b) Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete Komishiine komishiinere Jeneraalichinnimalaatisaminoha tajete woraqata uynanni.
3. Worbimmate meedaye layinki dirimi ba'raaraancho ikkitino gaamo woy loosu kifile birra 15 kumenna Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete Komishiine komishiinere Jeneraalichinni malaatisaminoha tajete woraqata uynanni. Ba'raaraancho gaamo woy loosu kifile miila ikkinohura mittu mittunku poolisete miilirano 20%/xibbunni lemoo anga/ damoozu lexxo uynannisi.

## 87. Worbimmate Meedaye Sayikki Dirimita

1. Worbu meedaye sayikki dirimita wo'ma woyti poolisaawete gaddado xa'mannohu aleenni naadisiissanno worbimma assinohu poolisete miilira, gaamote woy loosu kifilera uyinanni ba'raarshaati.
2. Worbu meedaye sayikki dirimi ba'raaraancho ikkinohu poolisete miili:
   a) 10 kume birra mitte hinge baantanni baatooshshenna 15% (tonaa onte anga) damoozu lexxo uynannisi; Reyha/kakkalamiha/ ikkiro higgaawe/seeru/ ragiraanora birra 15 kume baantanni.
   a) Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete Komishiine komishiinere Jeneraalichinni malaatisaminoha tajo woraqata uynanni.

## ፹፮. የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ

፩. የጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የዘወትር ፖሊሳዊ ግዳጅ ከሚጠይቀዉ በላይ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈፀመ የፖሊስ አባል፣ ቡድን ወይም የስራ ክፍል የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

፪. የጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የብር 15 ሺህ የአንድ ጊዜ ክፍያና የ20% በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፣የተሰዋ እንደሆነ ለህጋዊ ወራሾቹ ብር 20 ሺህ ይከፈላል፣

ለ) በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፫. የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የስራ ክፍል ብር 15 ሺህ እና በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡የተሸላሚዉ ቡድን ወይም የስራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም 20 በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

## ፹፯. የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ

፩. የጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ የዘወትር ፖሊሳዊ ግዳጅ ከሚጠይቀዉ በላይ የሚያኮራ ጀግንነት ለፈፀመ የፖሊስ አባል፣ቡድን ወይም የስራ ክፍል የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

፪. የጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የብር 10 ሺህ የአንድ ጊዜ ክፍያና የ15 በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፣ የተሰዋ እንደሆነ ለህጋዊ ወራሾቹ ብር 15 ሺህ ይከፈላል፣

ለ) በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

3. Worbimmate meedaye sayikki deerri ba’raaraancho ikkitino gaamo woy loosu kifile birra 10 kumenna Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma poolisete Komishiine Komishiinerichi malaatinsoha tajete woraqata uynanni; Ba’raadhino/ba’raarsha afidhino/ gaamo woy loosu kifile miila ikkinohu mittu mittunku poolisete miilirano 15%/xibbunni tonaa onte anga/ damoozu lexxo uynannisi.

## 88. Luphi Yiino Gumi Meedaye

1. Luphi yiino loosi gumi meedaye buqqete loosinni, kalaqatenninna woy aye loosu daninni komishiinete soqqansho wonshate luphi yiino guma afisiisino miilira woy loosu kifilera woy gaamora uynanni ba’raarshaati.
2. Luphi yiino loosu gumi meedaye ba’raaraancho ikkinohu poolisete miilira:
    a) Mittu dirimi suusu lophonna xibbunni 20 anga damoozu lexxo uynanni; Ba’raarsha adhikkinni reyha ikkiro higaawe/seeru/ ragiraasinera birra 8kume baantanni;
    b) Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolisete Komishiine komishiinere Jeneraalichi malaatisinoha tajete woraqata uynanni.
3. Luphi yinoha loosu gumi meedaye ba’raaraancho ikkitino gaamo woy loosu kifile miila ikkinohu mittu mittunku poolisete miilira mitto dirima suusu lophonna xibbunni 20 anga damoozu lexxo uynanni.

፫. የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የስራ ክፍል ብር 10 ሺህ እና በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ የተሸላሚዉ ቡድን ወይም የስራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም 15 በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

## ፹፰. የላቀ የስራ ዉጤት ሜዳይ

፩.የላቀ የስራ ዉጤት ሜዳይ በአዕምሮ ስራ፣ በፈጠራ ወይም በማንኛዉም መስክ የኮሚሽኑን ተልዕኮ ለማሳካት የላቀ ዉጤት ላስገኘ አባል ወይም የስራ ክፍል ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

፪. የላቀ የስራ ዉጤት ሜዳይ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የአንድ ደረጃ የማዕረግ ዕድገትና የ20 በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፣ ሽልማቱን ሳይቀበል የሞተ እንደሆነ ለህጋዊ ወራሾቹ ብር 8 ሺህ ይከፈላል፡፡

ለ) በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፫. የላቀ የስራ ዉጤት ሜዳይ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የስራ ክፍል በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣የተሸላሚዉ ቡድን ወይም የስራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም የአንድ ደረጃ የማዕረግ ዕድገትና የ20 በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

## 89. Poolisete Owaante Meedaye Umi Dirimiha

1. Poolisete owaante meedaye umi dirimihu amanyootunna poolisaawete dissippiliine xe’ne noosikkihanna poolisete miilimmanni lemiina onte diro ajjinokki yanna geeshsha owaatinohura poolisete miilira uynanni ba’raarshaati.
2. Poolisete owaante meedaye umi dirimi ba’raaraancho ikkinohu poolisete miilira shoolu agani damoozisi geeshshi woxe mitte hinge baantannisi.

## 90. Poolisete Owaantete meedaye Layinki Dirimiha

1. Poolisete owaante meedaye layinki dirimiha amanyootunninna poolisaawete disippiliinenni xe’ne noosikkihuranna poolisete miilimmanni lemoo diro ajjinokki yanna owaante uyno poolisete miilira uynanni ba’raarshati.
2. Poolisete owaante meedaye layinki dirimi ba’raaraancho ikkinohu poolisete miilira sasu agani damoozisi geeshshi woxe mitte hinge baantannisi.

## 91. Poolisete Owaantete MeedayeSayikki Dirimiha

1. Poolisete owaante meedaye sayikki dirimiha amanyootunninna poolisaawete disippiliinenni xe’ne noosikkihuranna poolisete miilimmanni tonaa onte diro ajjinokki yanna geeshshi owaante uyno poolisete miilira uynanni ba’raarshati.
2. Poolisete owaante meedaye sayikki dirimi ba’raaraancho ikkinohu poolisete miilira lamu agani damoozisi geeshshi woxe mitte hinge baantannisi.

## ፹፱. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ

፩. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ በስነ-ምግባሩና በፖሊሳዊ ዲሲፒሊኑ እንከን ለሌለበትና በፖሊስ አባልነት ከሃያ አምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የፖሊስ አባል የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

፪. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል የአራት ወር ደመወዙን የሚያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል፡፡

## ፺. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ

፩. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ በስነ-ምግባሩና በፖሊሳዊ ዲሲፒሊኑ እንከን ለሌለበትና በፖሊስ አባልነት ከሃያ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የፖሊስ አባል የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

፪. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል የሦስት ወር ደመወዙን የሚያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል፡፡

## ፺፩. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ

፩. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ በስነ-ምግባሩና በፖሊሳዊ ዲሲፒሊኑ እንከን ለሌለበትና በፖሊስ አባልነት ከአስራ አምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የፖሊስ አባል የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

፪. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል የሁለት ወር ደመወዙን የሚያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል፡፡

## 92. Poolisete Owaante Rivaane

Poolisete owaante rivaane bayriidi seerira ammanamaancho ikkatenni poolisete miilimmanni mittu mittunkura tonnu diri owaantera uynanni rivaaneeti.

## 93. Meedayenna Rivaane Aate Amanyootenna uddira

Tenne wodhora woroonnihu poolisete meedayenna rivaane aate amanyootenna uddira komishiine fushshitanno tittirshu wodho garinni ikkanno.

## 94. Meedayenna Rivaane Qole Adha

1. Meedaye woy Rivaane uynoonnihu kaphu taje aana kaima assine buunxiro;
2. Bayriidi seeri woy bayriidi seeri amanyooti aana loosantanno jaddo, kadda''atenni, shibbire kalaqatenni, gawajjitanno mu'ro doyissatenni woy wole jaddote kissenni kassasameenna yoote mini gumulonni buuxamiro uynoonni meedaye woy rivaane haa'ne hoollanni.

## 95. Meedayete Ba'raarshira Ikkado Assanno Looso Loose Reyno Poolisete Miilira

1. Tenne wodho garinni meedayu ba'raarshira ikkado assanno looso loose reynohu poolisete miilira hassiisannosi meedaye su'misinni borreessinannisi.
2. Meedaye minaamasira/galtesira/ uynanni, minaama/galte/hooggusiro bayru beettisira uynanni, beettu hoogisiro; gara ikkitino doogonni raggete higge kaiminni raggete qoosso noosihura uynanni.
3. Konni quwira gufo (1) garinni reenna worbimmate meedaye su'misinni borreessinoonnisihu poolisete miilira suusu lophono uyneennasi su'misinni borreessamantasira dandiitanno.

## ፺፪. የፖሊስ አገልግሎት ሪቫን

የፖሊስ አገልግሎት ሪቫን ለህገ-መንግስቱ ታማኝ በመሆን በፖሊስ አባልነት ለተሰጠ ለእያንዳንዱ አስር ዓመት አገልግሎት የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡

## ፺፫. የሜዳዮችና ሪቫኖች አሰጣጥ ስርዓትና አለባበስ

በዚህ ደንብ የተመለከቱት ሜዳዮችና ሪቫኖች አሰጣጥ ስርዓትና አለባበስ ኮሚሽኑ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፺፬. ሜዳይና ሪቫን መልሶ ስለመዉሰድ

፩. ሜዳዩ ወይም ሪቫኑ የተሰጠዉ በሀሰት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

፪. በህገ-መንግስቱ ወይም ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ በሚደረግ ወንጀል፣በክዳት፣በአሸባሪነት፣አደገኛ ዕፅ በማዘዋወር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ሲረጋገጥ የተሰጠዉ ሜዳይ ወይም ሪቫን ይወሰድበታል፡፡

## ፺፭. ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ስራ ሰርቶ ስለሞተ የፖሊስ አባል

፩. በዚህ ደንብ መሰረት ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ስራ ሰርቶ የሞተ የፖሊስ አባል አግባብ ያለዉ ሜዳይ በስሙ ይመዘገብለታል፡፡

፪. ሜዳዩ ለባለቤቱ ይሰጣል፣ባለቤት ከሌለዉ ለታላቅ ልጁ ይሰጣል፣ልጅ ከሌለዉ አግባብ ባለዉ የዉርስ ህግ መሰረት ለዉርስ ባለመብቱ ይሰጣል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የጀግንነት ሜዳይ በስሙ የተመዘገበለት የተሰዋ የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገትም ተሰጥቶት በስሙ ሊመዘገብለት ይችላል፡፡

# GAFA TONAA LEE
# ADDI ADDI WODHO

## 96.Koffeenyu Shiqonna Tittirshu amanyoote

Komishiine poolisete miillanni shiqqanno koffeenyubba garunni tirate dandiissannoha koffeenya shiqishanna tirate amanyoote diriirsitanno, tittiro jirtetenni gumulantanno.

## 97.Gaamote Loosonna Loosu Guutishshi Bikka

Komishiine heera hasiissannoha gaamote loossanna annu annu loosi guutisha bikkate loonsanni amanyoote diriirsitanno, tittiro jirtetenni gumulantanno.

## 98.Mannimmate Guuntenna Ispoortete Heewo

Komishiine poolisete millara mannimmate guunte millimmo assitannowanna isipoortete heewo beqqitanno injo kalaqqanno.

**99.Dagate Ledo heeranno Xaadooshshe** Aye poolisete miilino:

1. Dagoomu ledo hee’ranno xaadooshshinni dagoomu balchooma, bude, ammananna ayimma ayirrisa,
2. Dagate ayyaanna ayirrisate aana wodhote uddaanosi uddire leellatenni seeranna amanyoote ayirrisiisate sooreessimma heedhannosi.
3. Daga jaddo gargarate loosira beeqqaasine ikkitanno gede assate loosu amanyoote injeessate looso loossanno.

## 100. Hoolloonni Assooshshubba

Ayno komishiinete poolise miili:

1. Mannimma woy ayirrinye kisanno amadooshshenna assote assa;

# ክፍል አስራ ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፺፮. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

ኮሚሽኑ በፖሊስ አባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በአግባቡ ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት ይዘረጋል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፺፯. የቡድን አሰራርና የስራ አፈፃፀም አለካክ

ኮሚሽኑ ሊኖር የሚገባዉን የቡድን አሠራሮች እና የግል የስራ አፈፃፀም አለካክ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፺፰. የአካል ብቃትና ስፖርታዊ ዉድድር

ኮሚሽኑ የፖሊስ አባላት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርግበት እና በስፖርታዊ ዉድድሮች የሚሳተፍበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## ፺፱. ከሕዝብ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

ማንኛዉም የፖሊስ አባል፡-

፩. ከማህበረሰቡ ጋር በሚኖረዉ ግንኙነት የማህበረሰቡን ወግ፣ባህል፣እምነት እና ማንነት የማክበር፣

፪. በህዝባዊ በዓላት አከባበር ላይ የደንብ ልብሱን ለብሶ በመገኘት ህግና ስርዓት የማስከበር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

፫. ህብረተሰቡ በወንጀል መከላከል ስራ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ የአሰራር ስርዓት በመቀየስ ስራ ላይ ያዉላል።

## ፻. የተከለከሉ ድርጊቶች

ማኛውም የኮሚሽኑ የፖሊስ አባል፡-

፩. ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝና ድርጊት መፈፀም፣

2. Sirchunni, dagatenni, dagoomittetenni, danunni koo-tee”nni”, afuunni, ammanotenni, poletikunni, dagoomittete daanni, jirotenni, ilamatenni woy wolu uurrinshi korkaatinni badooshshe kalaqa woy babbada;
3. Looso uurrisate gano assa;
4. Keeraancho dira/salfe/ assa woy beeqqa;
5. Aye politiki uurrinshi miila woy irkisaancho ikka woy politiku uurrinshubba/paarte/ giwatenni umisi hedo amada;
6. Aye garinni maaxamatenni ikko faajjeetenni politiku kakkayishsha assa;
7. Doorshaho heewisantannota aye politiku uurrisha woy mancho irkisatenni ikko giwatenni kakkaayishsha woy aye politiki uurrinshi sumuda woy doorshaho ho’roosidhanno malaate aye baychono amada woy ho’roosira hoolloonnirichooti.

## 101. Doorshaho Beeqqa

1. Ayno poolisete miili mangiste ha’rissanno doorshubba doorate qoosso heedhannossi; Ikkeennano doorshu heewora beeqqa hasiriha ikkiro garunni tenne wodhora no seerubba agarantinno gedeenni heedheenna balaxe loososi agura noosi.
2. Doorshaho heewisamate loososi agurinohu poolisete miili doorshaho qeelirono qeelamirono wirro hige poolisete miilimmanni qaxarama didandaanno.

## 102. Tittirshu wodho/mammara/ Fushshate Biilloonye

Komishiine tenne wodho jeefisate hasiisannota tittirshu wodho fushshitara dandiitanno.

## 103. Loosu aana hosa Heedhannonsakki Seerubba

፪. በዘር፣በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ማድረግ፣

፫. የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፣

፬. ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ወይም መሳተፍ፤

፭. የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ መሆን ወይም የፖለቲካ ድርጅቶችን በመቃወም አቋም መያዝ፣

፮. በማናቸውም ሁኔታ በስውርም ሆነ በግልጽ የፖለቲካ ቅስቀሳ ማድረግ፤

፯. ለምርጫ የሚወዳደር ማንኛዉም ፖለቲካ ድርጅት ወይም ሰዉ በመደገፍም ይሁን በመቃወም ቅስቀሳ ማድረግ ወይም የማንኛዉንም የፖለቲካ ድርጅት ዓርማ ወይም ለምርጫ የሚጠቀምበትን ምልክት በማንኛውም ቦታ መያዝ ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

## ፻፩. በምርጫ ስለመሳተፍ

፩. ማንኛውም የፖሊስ አባል በመንግስት በሚካሄዱ ምርጫዎች የመምረጥ መብት ይኖረዋል፤ሆኖም በምርጫ ውድድር ለመሳተፍ የሚፈልግ ከሆነ አግባብ ያላቸዉ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በቅድሚያ ስራዉን መልቀቅ አለበት፡፡

፪. በምርጫ ዉድድር ለመሳተፍ ስራዉን የለቀቀ የፖሊስ አባል በምርጫዉ ቢያሸንፍም ቢሸነፍም ተመልሶ በፖሊስ አባልነት ሊቀጠር አይችልም፡፡

## ፻፪. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ኮሚሽኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፻፫. ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ሕጎች

1. Tenne wodho ledo xaaddannokki wodho baala, tittirshu wodho woy rosamino assotinna tenne wodho giddo worroonni hajubba aana loosu aana hosa dinonsa.

## 104. Wodho Kaajjitanno Yanna

Tini wodho Qoqqowu Gashshootu Amaale mini Gumulihunni Maaja-----------2012 M.D hanafe kaajjitinota iikitanno.

**Maaja ----2012 M.D**

**Hawaasa**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma**

**Pirezidaante**

፩. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## ፻፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ፤

ይህ ደንብ በክልል መስተዳድር ም/ቤት ከፀደቀበት ከሐምሌ---------፪፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሐምሌ-----፪፻፲፪ ዓ.ም**

**ሀዋሳ**

**ደስታ ለዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**